# ኃይማኖታዊ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው



አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)

ሚያዝያ ፳፩፣ ፳፻፲፰ ዓ.ም

## መግለጫ

**መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራእየ ዮሐንስ ለተጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጠው ከዚህ ቀጥሎ በፎቶ የምታዩት ይህ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሥኦ መጽሐፍ ነው፡፡**




**መጻሕፍተ ሊቃውንት ላይ ማለትም ፍትሐ ነገሥት፣ ሃይማኖተ አበው፣ መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ድርሳነ ቄርሎስ ወጰላድዮስ፣ ውዳሴ ማርያም፣ ድርሳነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ተግሣጸ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይና የሐዋርያት ሲኖዶስ ላይ እንዲሁም መጻሕፍተ መነኰሳት ላይ ለተጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ መጽሐፍ ደግሞ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሥኦ ቅጽ 2 ነው፡፡**




**እነዚህ ሁለቱ መጻሕፍት የሚገኙት አዲስ አበባ፣ አራት ኪሎ ቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሕንፃ ሥር ኦሜጋ መጻሕፍት መደብር፣ ስልክ ቁጥር 0941555550 ደውላችሁ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡**

# ሃይማኖታዊ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው

**፩. በሥርዓተ ቤተክርስቲያን የሚጋቡ ሙሽሮች በሚቆርቡበት ዋዜማ ወንዱ በዝንየት ቢመታ፣ ሴቷ ደግሞ ያልተጠበቀ ወር አበባዋ ቢከሠት በነጋታው የሚደረገው የጋብቻ ሥነ-ሥርዓት ምን ይደረጋል?**

መልስ፡- ጋብቻ የሚፈጸመው በቍርባን ነው። ሴት ደግሞ በወር አበባዋ ጊዜ መቍረብ አትችልም (ፍት.ነገ.3)። በዘመነ ወንጌል እንኳ ደም አበባ ነው ብሎ ደፍሮ ከቤተክርስቲያን ያገባ ካህን ቢኖር ከሹመቱ ይሻር ተብሏልና (ፍት.ነገ.24፤ አቡሊዲስ 18)። ወንዱም ዘሌዋ.15፥16 ላይ እንደተገለጸው ዝንየት ቢያገኘው በብሉይ ኪዳን ከርኵሰት ይቆጠርበት ነበር። በሐዲስ ግን እንደ የወር አበባ ርኩስ ባይባልም ዕለቱን ከመቍረብ ይከለከላል። [ብዙ ድግስ ተደግሶ ድግሱ ይበላሽብን የለምን የሚል ሰው ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን ቍርባኑን ለሌላ ጊዜ አድርጎ የድግሱን ነገር ደግሞ ከንስሓ አባት ጋር መመካከር ይቻላል የሚል አስተያየት አለኝ]።

**፪. ሕፃናት ልጆችን ያስቀረቡ ባልና ሚስት ከስንት ቀን በኋላ ነው መተዋወቅ የሚችሉት ወይስ እነርሱ እስካልቆረቡ ድረስ ችግር የለውም?**

መልስ፡- ልጃቸውን ክርስትና የሚያስነሡ እናትና አባት ክርስትና ከመነሣቱ ከሁለት ቀን በፊት እና ክርስትና ከተነሣ በኋላ እስከ ሁለት ቀን ከሩካቤ መከልከል ይገባቸዋል። ይህም ስለክብረ መንፈስ ቅዱስ ነው። "ወካልኡ እምነ ተራክቦተ ወላድያኒሁ ለዘነሥእዎ በጥምቀተ ክርስትና፤ ጸጋ ክብር በሚያሰጥ በጥምቀተ ክርስትና ያነሡትን ሰው አባት እናት ከመገናኘት መጽሐፍ መምህራን ከለከሉ። እመኒ በመዓልት ወእመኒ በሌሊት በእንተ ክብረ መንፈስ ቅዱስ" እንዲል (ፍት.ነገ.24)።

**፫. በምሥጢረ ሥላሴ ወላዲ ባሕርይ ተወላዲ ባሕርይ ሠራፂ ባሕርይ ማለት ይቻላል?**

መልስ፡- በእርግጥ ባሕርይ የሚለው ቃል ባለብዙ ትርጉም ስለሆነ ጠያቂው በየትኛው ትርጉም እንደጠየቀ መረዳት አልቻልኩም። ብዙ ጊዜ ግን ባሕርይ የሚባለው የሦስቱ አካላት በአንድነት መገናዘብ ስለሆነ ጥያቄው በዚህ ከሆነ ልመልስ። የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ አንድ ነው። በባሕርይ አንድ ስለሆኑ በዚህ አንድ ባሕርይ ግብር ሦስቱም ይጠሩበታል። ለምሳሌ አብ ፈጣሪ እንደተባለ ወልድም ፈጣሪ ይባላል መንፈስ ቅዱስም ፈጣሪ ይባላል። ምክንያቱም ፈጣሪነት የባሕርይ ግብር ነውና። ወላዲ ባሕርይ ካልን ሦስቱንም አካላት ወላድያን፣ ተወላዲ ባሕርይ ካልን ሦስቱንም ተወላድያን፣ ሠራፂ ባሕርይ ካልን ሦስቱንም አካላት ሠራፅያን ስለሚያሰኝ አያስኬድም። ወላዲነት ሦስቱ አንድ በሚሆኑበት ለመለኮት የሚነገር ሳይሆን በተለየ አካሉ ለአብ የሚነገር ነው። ተወላዲነትም ለወልድ የሚነገር ነው፣ ሠራፂነትም ለመንፈስ ቅዱስ የሚነገር ነው። በአፍኣዊ ግብረ ባሕርይ ለምሳሌ ለእኛ ለምእመናን አባት ወይም ወላዲ

በመባል ግን ሦስቱም ይጠሩበታል። "ወላዲ ውእቱ መንፈስከ፤ ሕይወትህ መንፈስ ቅዱስ ወላዲ ነው" እንዲል (አፈ.መን.35)። ክርስቶስንም አቡነ ዘበሰማያት፣ አበ ዓለም ሐዲስ እንደምንለው ማለት ነው።

**፬. ወንጌላዊ አካላት በሚጠሩበት በአካል ስም ወልድ ሰው ሆነ አላለም ነገር ግን በኩነት በሚለይበት በባሕርይ አንድ በሚሆንበት ቃል ሥጋ ሆነ ነው ያለው ይላል። በባሕርይ አንድ ከሆኑ ሦስቱም ሰው ሆኑ አያሰኝም?**

መልስ፦ አያሰኝም። ምክንያቱም ባሕርይ ወይም መለኮት የሚባለው የሦስቱ አካላት መገናዘብ ነው። "ዘውእቱ  አሐዱ ብርሃን ዘይሠርቅ እምኔሁ ሥላሴ፤ ሦስትነት ከእርሱ የሚገኝ አንድ ብርሃን ነው። አንድም ዘይሠርቅ እምኔሁ ለሥላሴ፤ ከሦስትነት የሚገኝ አንድ ብርሃን ነው" ይላል (ሃይ.አበ.11፥9)። ከሦስትነት የሚገኝ አንድ ብርሃን የሚለው አገላለጽ የሦስቱን አካላት ኩነታት መገናዘብ ያመለክታል። ባሕርይ አንድ ቢባልም ሦስት ከዊን እንዳለው ለመግለጽ ደግሞ ሦስትነት ከእርሱ የሚገኝ አንድ ብርሃን ተብሏል። ስለዚህ ባሕርይ በቃልነት ከዊኑ ሰው ሆነ እንጂ በልብነት ከዊኑ ወይም በእስትንፋስነት ከዊኑ ሰው አልሆነምና ሦስቱም ሰው ሆኑ አያሰኝም። "በእንተ ተዋሕዶተ መለኮት ዘንትናገር በዝየ ዘህልው በወልድ ወአኮ በእንተ አብ ወመንፈስ ቅዱስ፤ መለኮት ከትስብእት ጋር ተዋሐደ ብለን የምንናገርለት በወልድ ያለ ነው ስለአብ ስለመንፈስ ቅዱስ አይደለም" እንዲል (ሃይ.አበ.11፥3)።

**፭. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን መንፈስ ቅዱስ አነጻት ወይስ ጠበቃት?**

መልስ፦ መጻሕፍት አንጽሖ፣ ዐቀባ እየተባለ ተገልጿል የሁለቱም ምሥጢር ግን አንድ ነው። ቅዱስ ያሬድ "አንጺሖ ሥጋሃ ኀደረ ላዕሌሃ" ብሏል። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስም "መንፈስ ቅዱስ ቀደሰ ወአንጽሐ ሥጋሃ ለማርያም፤ የድንግልን ሥጋ አጸና አነጻ" ብሏል (ሃይ.አበ.36፥19)። ይህም ከሰው ሁሉ ልጆች ይልቅ ደግ መሆኗን በመለኮታዊ ዕውቀቱ አስቀድሞ አውቆ ከማሕፀን ጀምሮ ንጹሕ አድርጎ እንደፈጠራት ያመለክታል። አነጻት ማለቱ ከጽንስ ጀምሮ ነው እንጂ ቀድሞ ንጽሕት ሳትሆን ቀርታ በኋላ አነጻት ማለት አይደለም። ጠበቃት [ዐቀባ] የሚለውም ከማሕፀን ጀምሮ በንጽሕና እንደጠበቃት ያመለክታል። "መንፈስ ቅዱስ ዐቀባ እምከርሠ እማ" እንዲል (ውዳ.ማር.ዘረቡ.ትር.)

**፮. እመቤታችን የክርስቶስ የጸጋ እናቱ ወይስ የባሕርይ እናቱ ናት?**

መልስ፦ ባሕርይ ባለብዙ ትርጉም ነው። ባሕርይ መገኛ ተብሎ የሚተረጎምበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ የሰው ልጅ ከአራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ነው ሲል ባሕርያት ያላቸው እሳትን፣ መሬትን፣ ነፋስን፣ ውሃን ነው። በዚህ ጊዜ ባሕርይ መገኛ ማለት ነው። በዚህ አግባብ ካየነው ክርስቶስ በሥጋ ከድንግል ማርያም የተወለደ (የተገኘ) ስለሆነ ድንግል ማርያም የባሕርይ እናቱ ትባላለች። በመለኮቱ ከአብ የተወለደ (የተገኘ) በመሆኑ በመለኮቱ የአብ

የባሕርይ ልጁ ይባላል። ወልድ ከአብ ተገኘ እያሉ መጻሕፍት ሲናገሩ መገኘቱ (ተረክቦው) አባት ቀድሞ ልጅ ሳይከተል ወይም መቀዳደም ሳይኖር ነው። ከድንግል ማርያም ተወለደ ስንል ግን በሥጋ ስለሆነ በሥጋ ደግሞ ድንግል ማርያም ትቀድማለች። ዮሐንስ መጥምቅም "ይመጽእ እምድኅሬየ ብእሲ ዘሀሎ እምቅድሜየ" ብሏል (ዮሐ.1፥15)። እምድኅሬየ ማለቱ በሥጋ ይቀድመዋልና ነው።

፯. ማቴ.1፥18 በመንፈስ ቅዱስ ግብር ፀንሳ ተገኘች ሲል የመንፈስ ቅዱስ ግብር ምንድን ነው?

መልስ፦ ምንም እንኳ የተፈጥሮ ሕግን የሠራም ራሱ እግዚአብሔር ቢሆንም ከተለመደው የተፈጥሮ ሕግ ከፍ ያሉ ጉዳዮችን ደግሞ በተለየ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ (ግብረ መንፈስ ቅዱስ) እያለ ይጠራቸዋል። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እያለ ለይቶ መንፈስ ቅዱስን ይጥራው እንጂ በአምላካዊ ሥራ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ስለሆኑ የአብ ሥራ (ግብረ አብ)፣ የወልድ ሥራ (ግብረ ወልድ) ቢልም አንድ ነው። ስለዚህ ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ያለው ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ስለሆነ ያለወንድ ዘር መፅነስን፣ ያለሩካቤ መፅነስን ነው።

፰. በአብ መሠረትነት ስንል ለምስጢረ ሥላሴ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ አብ መገኛ መሆኑን ለመግለጽ መሠረት ተብሏል። የሀገራችን ሊቃውንት መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ፣ አለቃ ኅሩይና ሌሎችም መገኛነቱን ለመግለጽ በአብ መሠረትነት እያሉ ይገልጻሉ። ይህ መሠረትነት ወይም መገኛነት ግን መበላለጥን አያሳይም። በምሳሌ ዘየሐጽጽ ሙቀትና ብርሃን ከፀሐይ ክበብ ይገኛሉ። ከፀሐይ ክበብ ይገኛሉ ብንልም ሙቀትና ብርሃን ከክበብ የተለዩበትና ክበብ ኖሮ እነርሱ ያልነበሩበት ጊዜ ግን የለም።

፱. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው ለምልአተ ኃጢአት ነው ወይስ ለጥንተ አብሶ?

መልስ፦ ክርስቶስ ተሰቅሎ ያዳነን በሁለቱም ምክንያት ለሁለቱም ምክንያት ነው። ለጥንተ አብሶም ለምልአተ ኃጢአትም ነው። በጥንተ አብሶ ብቻ ቢሆን ኖሮ አዳምንና ሔዋንን ብቻ ለማዳን መጣ ባሉት ነበርና። ወልደ እግዚአብሔር ሰው የሆነው ግን ሰው ሁሉ በኃጢአት ተዘፍቆ ይኖር (ምልአተ ኃጢአት) ስለነበር ሰውን ሁሉ ለማዳንም ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ዕብራውያንን በተረጎመበት ድርሳኑ "ሶበሰ መጽአ በጥንተ አብሶ እምኢኮነ ሞቱ ለቤዛ ብዙኃን" እንዲል (ድርሳን 17)።

፲. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ተቀብላለች ወይስ አልተቀበለችም? ከተቀበለች የልጇን ሥጋ መብላት አይሆንም ወይ? ካልተቀበለች በራስዋ ድናለች ወይ?

መልስ፦ በትውፊት በውዳሴ ማርያም ትርጓሜያችን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደቆረበች ተገልጿል፡፡ ልጇ ሰው ብቻ አይደለም፡፡ አምላክም ሰውም የሆነ አንድ ነው እንጂ፡፡ የልጇ ሥጋ እንደሌላው ሰው ሥጋ አይደለም፡፡ በተዋሕዶተ መለኮት የከበረ የሚያድን የሚፈውስና ዘለዓለማዊ ሕይወትን የሚያጎናጽፍ ነው እንጂ፡፡ ስለዚህ የልጇን ሥጋ ብትበላውም በጸጋ ላይ ጸጋን ይጨምርላታል እንጂ ምንም ችግር የለውም፡፡ ምልእተ ጸጋ አይደለችም ወይ የምን ጸጋ ነው ይጨመርላታል የሚባለው የሚል ካለ ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከፍጡራን ሁሉ በላይ ጸጋ ያላት መሆኗን ለመግለጽ ምልእተ ጸጋ አልናት እንጂ ከዚህ በኋላ ምንም ዓይነት ጸጋን የማትቀበል ናት ማለታችን አይደለም፡፡ በማይቋረጥ ጸጋ (ተወስኮ ዘነሣእያን) ከሁሉ በላይ ሆና ትኖራለች እንጂ፡፡ ተወስኮ ዘነሣእያን ደግሞ አይቆምም፣ አይገታም፣ አያቋርጥምና (ድር.ዮሐ.አፈ.1 ትርጓሜ)፡፡ እንዲሁም "ወኢይጸራዕ ውሒዙ እምተወስኮ፤ ጸጋው ከመሰጠት አያቋርጥም፡፡ እስመ ተወስኮሰ ዘነሣእያን ይእቲ" እንዲል (አረ.መን.33)፡፡ ድንግል ማርያም ምልእተ ጸጋ መባሏ አንጻራዊ ነው እንጂ ከዚህ በኋላ ጸጋ የማያስፈልጋት ከባሕርይ አምላክነት የደረሰች ናት ለማለት አይደለም፡፡

## ፲፩. እግዚአብሔር ወልድ በእመቤታችን ማሕፀን አደረ ወይስ ተዋሐደ? ተዋሐደ ካልን እመቤታችን አምላክ አትባልም ወይ?

መልስ፦ ከዚህ ላይ ምሥጢረ ሥጋዌን በጥቂቱም ቢሆን መረዳት ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር ወልድ በድንግል ማርያም ማሕፀን አደረ ስንል ምን ማለታችን ነው? የሚለውን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ወልደ እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ ተዋሐደ እንጂ ራሷን ድንግል ማርያምን የተዋሐደ አይደለም፡፡ ስለዚህ ድንግል ማርያም የባሕርይ አምላክ አትባልም፡፡ ቅድስተ ቅዱሳን በመሆኗ ግን የጸጋ አምላክ ትባላለች፡፡

## ፲፪. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋው ፍጡር ይባላል ወይስ አይባልም?

መልስ፦ ይባላል፡፡ በዚህ ዙሪያ ቅዱሳን ሊቃውንት ቃል በቃል የተናገሩትን በቅደም ተከተል ከሃይማኖተ አበው እንመልከት፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ "ይብል ዘንተ በእንተ ልደቱ በሥጋ ከመ ውእቱ ፍጡር ወግቡር፤ ቃል የተዋሐደው ሥጋ ፍጡር እንደመሆኑ መጠን በሥጋ ስለተወለደው ልደት ይህን ተናገረ.....ይደሉ ይትበሀል ዝንቱ ትርጓሜ በእንተ ትስብእቱ ለመድኅን እስመ ፍጡር ውእቱ፤ ትስብእት የተፈጠረ ነውና ይህ መድኅን ሰው ስለመሆኑ ይነገራል" ብሏል (ሃይ.አበ.32፥13-18)፡፡ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ "ወዓዲመ ይትበሀል ፍጡረ በእንተ ዘኮነ ሥጋ ወኀደረ ላዕሌነ፤ ወዲህም ሰው ስለሆነ የእኛን ባሕርይ ስለተዋሐደ ፍጡር ይባላል" ብሏል (ሃይ.አበ.35፥6)፡፡ ቅዱስ አቡሊዲስ "መለኮትሰ ኢፍጡር ውእቱ፤ መለኮት ያልተፈጠረ ነው፡፡ ወሥጋሰ ፍጡር ውእቱ፤ ሥጋ ግን የተፈጠረ ነው...ወኢንሬስዮ ለመለኮት ፍጡረ ወኢግቡረ፤ መለኮትን የተፈጠረ ነው አንልም፡፡ ወዓዲ ኢንሬስዮ ለሥጋ ኢፍጡረ፤ ዳግመኛም ሥጋን ያልተፈጠረ ነው አንልም" ይላል (ሃይ.አበ.39፥25-27፤ ሃይ.አበ.40፥23)፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ

አፈወርቅ "እስመ ትስብእቱ ፍጡር ውእቱ፤ የተዋሐደው ሥጋ ፍጡር ነውና" ብሏል (ሃይ.አበ.63፥28)። ቅዱስ ኤጲፋንዮስ "እስመ ሶበ ተሰምየ ፍጡረ በእንተ ትስብእቱ ዓዲ ተሰምየ አንቀጸ፤ ሰው ስለሆነ ፍጡር ቢባል ወዲህም በሎር ተባለ" ይላል (ሃይ.አበ.56፥22)። ቅዱስ ቄርሎስ "ወኢይትበሀል ከመ ሥጋ ተመይጠ ኀበ ህላዌ መለኮት፤ ሥጋ መለኮት ወደ መሆን ተለወጠ ሊሉ አይገባም። ወኢቃል ተመይጠ ኀበ ህላዌ ትስብእት፤ ቃልም ሥጋን ወደ መሆን ተለወጠ ሊሉ አይገባም። እስመ ሥጋ ፍጡር ወግቡር ውእቱ፤ ሥጋ ፍጡር ነውና" ብሏል (ሃይ.አበ.78፥30)። ቅዱስ ቴዎዶስዮስ "ወሶበ ትሰምዕ ከመ ውእቱ ፍጡር ኢተኀሊ ግሙራ ከመ ዝንቱ ይትበሀል በእንተ ቃል ከመ እግዚአብሔር ፈጠሮ በከመ ይቤ አርዮስ ርጉም፤ ፍጡር እንደተባለ ብትሰማ የተረገመ አርዮስ እንደተናገረው ስለቃል የተነገረ አይምሰልህ። አላ ይትበሀል በእንተ ሥጋ ከመ ውእቱ ፍጡር፤ ፍጡር እንደሆነ ስለሥጋ ይነገራል እንጂ። ወውእቱ ዘሐነፀ ሎቱ መቅደሰ እምድንግል ንጽሕት ማርያም፤ ለራሱ ከእመቤታችን ነፍስን ሥጋን ፈጥሮ የተዋሐደ እርሱ ነው" ይላል (ሃይ.አበ.83፥14)። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወሰብእ እንዳልነው ሁሉ ፍጡር ወፈጣሪ እንለዋለን። "ውእቱሰ ፍጡር ወፈጣሪ ውእቱ" እንዲል (ሃይ.አበ.124፥18)። የሃይማኖተ አበው የትርጓሜ መጻሕፍት ፍጡር የሚለውን ቃል በቃል ሲያስቀምጡት ወደ አማርኛ የተረጎሙ ሊቃውንት ደግሞ አንዳንድ ቦታ ሰው እያሉ ተርጉመውታል። ሁለቱም ግን ሐሳቡ አንድ ነው። የሁለቱንም ሐሳብ በደንብ የሚገልጸው "እስመ ሰብእሰ ፍጡር ውእቱ"የሚለው ቃል ነው (ሃይ.አበ.124፥26)። ከላይ ለማሳያ ያህል ጥቂቶቹን ጠቀስን እንጂ ክርስቶስ በሥጋው ፍጡር እንደሚባል ከአራቱ ጉባኤያት በተጨማሪ በርካታ መጻሕፍት ላይ ይገኛል። ፍሬ ነገሩ የክርስቶስ ሥጋ ቅድመ ዓለም የነበረ ሳይሆን የተፈጠረ መሆኑን የሚገልጽ ነው። ፍጡር ማለት የተፈጠረ ማለት ነውና። አንዳንዶች ባለማወቅ ተዋሕዶው ፍጡርነቱን አጥፍቶታል ብለው ሰውነቱን ዘንግተው አምላክ ብቻ (ዕሩቅ ቃል) ለማድረግ ይጥራሉ። ነገር ግን ተዋሕዶው በተዓቅቦ ስለሆነ መጠፋፋት የለበትም። "ኢያፍለሰ ፈጣሪ መለኮቶ ለከዊነ ፍጡር፤ ፈጣሪ ባሕርዩን ፍጡር ወደ መሆን አልለወጠውም። ወኢደምሰሰ ትስብእቶ ፍጡረ ለከዊነ ፈጣሪ፤ የተፈጠረ ሥጋንም ፈጣሪ ወደ መሆን አልለወጠውም" እንዲል (ሃይ.አበ.36፥24)።

## ፲፫. መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ሲወርድ ለእመቤታችን ወርዷል ወይስ አልወረደም? ወርዷል ካላችሁ እመቤታችን መጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ አላደረባትም ወይ?

መልስ፦ መንፈስ ቅዱስ ለእመቤታችንም ወርዷል ከሐዋርያት ጋር ነበረችና (የሐዋ. ሥራ 1፥14)። ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶ አያልቅም። ስለዚህ ምንም እንኳ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቀድሞም ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ያደረባት የነበረች ቢሆንም በነበራት ሀብት ላይ እግዚአብሔር ባወቀ ተጨማሪ ሀብት ተሰጥቷታል ማለት ነው።

፲፬. መንፈስ ቅዱስ ሕይወት ነው ከተባለ አንዱ ያለ አንዱ መኖር አይችልም ወይ?

መልስ፦ በምሥጢረ ሥላሴ ሦስቱ አካላት ተገነዛዝበው ይኖራሉ እንጂ ያለተገናዝቦ በራሳቸው ብቻ አይኖርም። መንፈስ ቅዱስም በአብ ልብነት ሳያስብ በወልድ ቃልነት ሳይናገር በሕይወትነቱ ብቻ መኖር አይችልም። አብም በወልድ ቃልነት ሳይናገር በመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት ሕያው ሳይሆን በልብነቱ ብቻ መኖር አይችልም። ወልድም በአብ ልብነት ሳያስብ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ሕያው ሳይሆን በቃልነቱ ብቻ መኖር አይችልም። መገነዛዘባቸው ባሕርያዊ ስለሆነ በዘመን ብዛት የሚለወጥ ወይም ሊጠፋ የሚችል አይደለም።

፲፭. በቅረቡ በአንድ ቦታ ቅዳሴ እያስቀደስኩ ካህናት ሥጋ ወደሙን ሲከለክሉ አየሁ ስጠይቃቸው የማናውቀውና ወጣት ከሆነ ወይም ከሆነች አናቆርብም አሉኝ። ልጂቱን ለምን ከለከላችኋት ስላቸው እናውቃታለን እሷ ሥጋ ወደሙን መቀበል አትችልም አሉኝ ለምን ስላቸው ኃጢአተኛ ናት እናውቃታለን አሉ። ንሥሓ ገብታ እንደሆነስ ስላቸው አይቻልም እያወቅን አንስጥም አሉኝ። ሥጋውን ደሙን አትከልክሉ እሚል መጽሐፋ አምጣ አሉኝ። መልሱ እንዴት ነው?

መልስ፦ ማንኛውም ሰው ኃጢአት ሊሠራ ይችላል። ቢሆንም ግን ንስሓ ገብቶ ሥጋውን ደሙን ይቀበላል። ስለዚህ ንስሓ የገባን ሰው ከቁርባን መከልከል አይገባም። ምናልባት የከለከሉት ሰው ያለንስሓ እንዲሁ እቀበላለሁ ብሎ አስቦ ከሆነ መከልከላቸው መልካም ነው። ሳይገባው ቢቀበል ይጎዳበታልና (1ኛ ቆሮ.11፥29)። ንስሓ የገባውን ሰው አልቀበልም አላቆርብም ብሎ የከለከለ ካህን ካለ ግን ይሻር ተብሏል። "ኃጥኡን አልቀበልም የሚል ኤጲስ ቆጶስ ቄስ ቢኖር ይሻር" ተብሏል (ፍት.ነገ.5)።

፲፮. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋው አላዋቂ ነው ማለት እንችላለን ወይ?

መልስ፦ ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ክብር ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋው አላዋቂ ነው የሚል ተጽፎ እስካሁን አላገኘሁም። በተፈጥሮም ቢሆን እግዚአብሔር ለሰው ልጅ አዋቂነትን ሰጥቶ ፈጥሮታል እንጂ አለማወቅን ሰጠው አልተባለም። ስለዚህ እንኳንስ ክርስቶስ ማንኛውም ሰው በሥጋው አዋቂ ነው። የሰው ልጆች ዕውቀት ግን ከሰው ሰው ይለያያል። ዕውቀታቸው የጸጋ ስለሆነ ማለት ነው። ክርስቶስ ግን ራሱ የባሕርይ አምላክ ስለሆነ በዕውቀቱ መከፈል የለበትም (የማያውቀው ዕውቀት) የለም።

፲፯. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ በሥጋው መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ ይባልለታል ወይ? አያይዘው ክርስቶስ ለራሱ ቆርቦ እንዳቆረባቸው ይነገራል። የመቁረቡ ጥቅሙ ምንድን ነው?

መልስ፦ አዎ ክርስቶስ ሥጋዉን ደሙን ቀምሶ እንዳቀመሳቸው በትርጓሜ ተገልጿል (ማቴ.26፥26 ትርጓሜ)። እርሱ ራሱ መቅመሱ ለአርአያነት ነው እንጂ እርሱ ራሱ የሚጠቀምበት ሆኖ አይደለም። በዮርዳኖስ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ ተብሎም ተጽፏል (ሃይ.አበ.79፥61)። በጥምቀት መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ ማለቱ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ አምላክነቱን መግለጡን ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስን የባሕርይ ሕይወቱ ያደረገው ሥጋ ቃልን በተዋሐደ ጊዜ በማሕፀን ነው። እኛ በስሙ አምነን ስንጠመቅ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን እንደምንቀበል ለማሳወቅ በዮርዳኖስ ለአርአያነት መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ። መቀበሉ ግን እርሱ እጠቀም ብሎ ወይም የተጠቀመበት ሆኖ አይደለም። በጥምቀቱ እኛን አከበረበት እንጂ እርሱ አልከበረበትም። መንፈስ ቅዱስን በዮርዳኖስ በአምሳለ ርግብ በመቀበሉም እኛን አከበረበት እንጂ እርሱ አልከበረበትም። "ተጠምቀ በዮርዳኖስ ወኢተጠምቀ ከመ ይኩን ንጹሐ፤ ለራሱ እጠቀም ብሎ አልተጠመቀም" እንዲል (ሃይ.አበ.117፥5)።

፲፰. በቅድስት ሥላሴ አስተምህሮ መሠረት ኩነት አካላዊ ነው ወይስ ባሕርያዊ? ከዚሁ ጋር ተያይዞ አብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ከተባለ፣ ወልድ የአብ የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ከተባለ፣ መንፈስ ቅዱስ የአብ የወልድ ሕይወታቸው ከተባለ ፍጹም አካል የላቸውም አንዱ ለአንዱ የአካሉን ጉድለት የሚሞላለት ነው አያሰኝም?

መልስ፦ ኩነት ከአካል ያልተለየ ስለሆነ አካላዊ ይባላል። ራሱ አካል ግን አይደለም። ኩነት የሚባለው መሆን ሲሆን የአካል መሠረት በመገናዘብ ባሕርይ የሚባል ነው። አብ ራሱ ልብ ሆኖ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው። ወልድ ራሱ ቃል ሆኖ የአብ የመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው። መንፈስ ቅዱስ ራሱ ሕይወት ሆኖ የአብ የወልድ ሕይወታቸው ነው (ሃይ.አበ.40፥8)። ልብነት፣ ቃልነት፣ እስትንፋስነት ግን ኩነታት ስለሆኑ አካላዊ ናቸው እንጂ አካላት አይደሉም። ስለዚህ አካላት በኩነታት ስለተገነዛዘቡ ፍጹምነታቸውን አጠያያቂ አያደርገውም። ሕጸጹ ቢጎላም ለምሳሌ አንድ ሰው በጽጌረዳ አበባ መካከል ሲያልፍ የጽጌረዳ አበባው መዓዛ ይሸተዋል። ሰውየው መዓዛውን ስላሸተተ ለሰውየው የጨመረለት ወይም ጎዶሎውን የሞላለት አካላዊ ነገር የለም። ጽጌረዳውም መዓዛውን ሰው ስላሸተተው ከአካሉ አይጎድልም። ሁለቱም በየአካላቸው ፍጹማን ሆነው ይኖራሉ እንጂ። ስለዚህ በከዊን መገነዛዘባቸው ፍጹምነታቸውን ጥያቄ ውስጥ አያስገባውም።

፲፱. አንድምታ ትርጓሜ መጻሕፍት ላይ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ቃላት በብዙ ምስጢራት ሊተረጎሙ እንደሚችሉ የታወቀ ቢሆንም ትርጓሜያቸው አንድ ብቻ ብያኔ የሆኑ በተለይ ታሪካዊ ሁነቶች ላይ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ የሚመስሉ አንድምታዎች አሉ። ለምሳሌ የማቴዎስ ወንጌል ትርጓሜ ላይ የዮሐንስ ምግቡ አንበጣ የሚለውን "አንቦጣ የሚባል ቅጠል" አንድም "በቁሙ አንበጣ" ይላል። ሰብአ-ሰገል የገበሩት እጅ መንሻ እንዴት ከእነርሱ እንደደረሰ አንድ ብያኔ ከመስጠት ይልቅ list of hypothesis ማስቀመጥ አለ። መዝሙረ ዳዊት ላይ

"ዳዊት ይህን የተናገረበት ጊዜ አልታወቀም አንድም ታውቋል" የሚሉ አገላለጾች ብዙ መጻሕፍት ላይ አሉ። ሊቃውንቱ በእግዚአብሔር ተመርተው ከተረጎሟቸው እንዴት መላምታዊ የሚመስሉ አተረጓጎሞች ተጻፉ?

መልስ፦ የትርጓሜ ስልቱን በመጽሐፍ መልኩ በጥልቀት እያዘጋጀሁት ስለሆነ ጥልቅ ጉዳዩን በዚያ የምገልጸው ይሆናል። ከትርጓሜ ስልቶች አንዱ ታሪክ ነው። ታሪክ ሲተረክ ደግሞ ሁሉም በየደረሰበት መረጃ ይናገራል። መተርጉማኑም በጉዳዩ ዙሪያ ልዩ ልዩ ሊቃውንት የተናገሯቸውን መሠረት አድርገው የሁሉንም ሐሳብ አንድ በአንድ እየገለጹ እገሌ እንዲህ ይላል፣ እገሌ ደግሞ እንዲህ ይላል እያሉ የተቀመጡትን ሐሳቦች ያስቀምጣሉ። ሙሉ ማስረጃ የተገኘለትን ጉዳይ "ይህስ አይደለም እንዲህ ነው" ብለው ደምድመው ይናገራሉ። ማስረጃ የሌለውን ጉዳይ ግን የሁለቱንም ሐሳብ አቅርበው ለጥናት ክፍት አድርገው ይተውታል። የዶግማ ሐተታዎች ግን አይለወጡም። ታሪክን፣ ቀኖናን መሠረት ያደረጉ ሐተታዎች ግን እንደዘመኑ ሊታተቱ ይችላሉ። መተርጉማን ከእነርሱ በፊት የተጻፉ ጽሑፎችን፣ በዘመናቸው የሚባሉ አባባሎችን ተጠቅመዋል። እግዚአብሔር ገልጾላቸው የጻፉ መተርጉማን ይኖራሉ፣ በአንጻሩ የቀደሙ አባቶች የጻፏቸውን ጽሑፎች በማደራጀት የጻፉም ይኖራሉ። ስለዚህ ትርጓሜውን ራሱ መመርመር ይገባል። ሌላው አብነት የሚባል አለ። ይህ አብነት የዘርና የትርጓሜ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። በዘር አብነት የዮሐንስን ምግብ አንበጣ ያለውን እንቦጣ ብለው የጻፉ ስለነበሩ የእነርሱን ሐሳብ ለማስቀመጥ የበረሃ ማር ብለውታል። ዮሐንስ የበረሃ ማርንም ይበላ ስለነበር ሐተታው መልካም ነው። መደበኛው ግን ዮሐንስ መጥምቅ አንበጣ ይበላ ነበር የሚለው ነው። ወንጌል የምግብ ሕግ አይደለችምና አንድም ለንጹሓን ሁሉ ንጹሕ ነውና ተብሎ በሐተታ የታተተ ለዚህ ነው። የዘር አብነት እንዳለ ማስረጃውም በሰሎሞን መጽሐፍ ቃለ ጠቢብ የሚልና ቃለ ጥበብ የሚል መገኘቱ ነው። በሌሎችም ይህንን የመሰለ ይገኛል። "የትርጓሜ ውበት" ከሚባለው መጽሐፌ በጥልቀት በመጽሐፍ ስለሚወጣ ሰፊውን ጉዳይ ከዚያ ይጠብቁ።

፳. አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ውጭ ሀገር በኦኃት አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ የሚኖር ሆኖ በእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት የሚፈጸሙ ሥርዓቶች (ቁርባን ፣ ጥምቀት፣ ወዘተ) ላይ መሳተፍ ይችላል?

መልስ፦ አዎ ይችላል። ኦኃት አብያተ ክርስቲያን ምንም እንኳ በአንዳንድ የቀኖና አሰጣጥና የሥርዓት አፈጻጸም የተለያየን ብንሆንም በዶግማ ወይም በመሠረተ እምነት አንድ ነንና።

፳፩. በዚህ ወቅት ማለትም በበዓለ ኀምሳ ንስሓ መግባት ይቻላል?

መልስ፦ አዎ ይቻላል። የሰው ልጅ ኃጢአትን ከሠራ ከነሠራው ኃጢአት መሞት የለበትም። ሞት ደግሞ በማናቸውም ቀን ሊመጣ ይችላል። በበዓለ ኀምሳ የሚሞትም

ይኖራልና፡፡ "እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፡፡ ጠብቀውም ንስሐም ግባ፡፡ እንግዲያስ ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም" እንዲል (ራእ.3፥3)፡፡ ነገር ግን የቀኖናው ዓይነት ሊለያይ ይችላል፡፡ ለምሳሌ በበዓለ ኀምሳ መስገድ፣ መጾም እንደማይገባ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጊዜ ንስሓ ለሚገባ ሰው ምጽዋት፣ ጸሎት ወይም ሌላ ነገር ሊታዘዝ ይችላል፡፡

**፳፪. በበዓለ 50 ረቡዕ እና አርብ ጨምሮ ከትንሣኤ ማግስት ጀምሮ ባልና ሚስት መተዋወቅ ይችላሉ ወይስ አይችሉም?**

መልስ፡- ፍትሐ ነገሥት ባልና ሚስት ከግንኙነት እንዲርቁ የሚያዝዘው ቅዳሜ፣ እሑድ፣ በጌታ በዓላት፣ በአጽዋማት ነው፡፡ በአጽዋማት ደግሞ በተለይም በሰሙነ ሕማማት፣ በረቡዕና ዓርብ ጾም አልተፈቀደም፡፡ "አሌ ሎቱ ለዘይገብራ ለዛቲ ኃጢአት በሰሙነ ሕማማት ቅድስት= በሰሙነ ሕማማት ይችን ኃጢአት ለሚሠራ ሰው ወዮለት" ተብሏል (ፍት.ነገ.24)፡፡ በሌሎች አጽዋማት ግን ጾር ተነሥቶባቸው ከሌላ የሚያደርሳቸው ከሆነ የሚፈቀድበት አግባብ ይኖራል፡፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ትርጓሜ ላይ "ከዐቢይ ጾም በቀር በቀሩት አጽዋማት ከመዓልቱ ሦስት ሰዓት፣ ከሌሊቱ ሦስት ሰዓት ስድስት ይሆናል፡፡ በዚህ ከሩካቤውና ከምግቡ የወደደውን ያስቀድማል" ተብሏል፡፡ የቻለ ግን ሙሉ አጽዋማትን ቢከለከል የበለጠ መንፈሳዊ ዋጋን ያገኝበታል፡፡ ሌላው በወር አበባ ጊዜ፣ በአራስነት ጊዜ፣ በቆረቡ ጊዜ ግንኙነት አይፈቀድም፡፡ በበዓለ ኀምሳ ያሉ ረቡዕና ዓርብ ግን ጾም የለባቸውም፡፡ ጾመ ድኅነት የሚጀምረው ከጰራቅሊጦስ ቀጥሎ ካለው ረቡዕ ጀምሮ ነውና፡፡ ስለዚህ በበዓለ ኀመሳ ከቅዳሜ ከእሑድ፣ ከጌታ በዓላት፣ ከእመቤታችን በዓላት ውጪ ባሉት ዕለታት ከሰኞ እስከ ዓርብ አልተከለከለም፡፡

**፳፫. እመቤታችን ንጹሐ ባሕርይ ከሆነች ለምን ሞተች?**

መልስ፡- በሐዲስ ኪዳን በሥጋ መሞትና ንጹሐ ባሕርይነት የሚቃረኑ ነገሮች አይደሉም፡፡ በእርግጥ ሞት የኃጢአት ውጤት ሆኖ እስከ ዘመነ ሥጋዌ ድረስ ሰውን ሁሉ ወደ ሲኦል የሚሸኝ ሆኖ ይኖር ነበር (ዘፍ.2፥17)፡፡ ይህ የሞት መርገም ግን በክርስቶስ ሞት ተሽሯል፡፡ የኃጢአት ውጤት የነበረው ሞትም ለጻድቃን ወደ በለጠ ዕረፍት መሸጋገሪያ ሆኗል፡፡ ሞቶሙሰ ለጻድቃን ዕረፍቶሙ ውእቱ እንዲል፡፡ ስለዚህ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሞት መከራና ችግር ከበዛበት ከዚህ ዓለም ተለይታ ሕይወት ዕረፍት ወዳለበት ዓለም መሸጋገሪያ ሆኗታል፡፡ የሞት ርግማን የሞት ሞቱ በሆነ በክርስቶስ ተሽሯል፡፡

**፳፬. አሐዱ ነዳይ ዘክሕደ ሃይማኖቶ የሚለው የማሕሌተ ጽጌ ድርሰት ከነገረ ድኅነት አስተምህሮ አንጻር እንዴት ይታያል?**

መልስ፦ ከዚህ ዘክሕደ ሃይማኖቶ ማለቱ የቀደመ ግብሩን ለመግለጽ ነው። ከዚህ የተጠቀሰው ሰው እግዚአብሔርን ክዶ የነበረ ሰው ነው። ድንግል ማርያምን ግን ከጽንዐ ፍቅሩ የተነሣ አልክድም ብሏል። ድንግል ማርያምም በምልጃዋ እግዚአብሔር ሁለተኛ የመኖር እድልን እንዲሰጠው አድርጋ ያ ሰው እንደገና እግዚአብሔርን አምኖ ምግባር ትሩፋት ሠርቶ ድኗል። እግዚአብሔርን የካደ ሰው አይድንም። ይህ ሰውም የዳነ የቀድሞ ክሕደቱን ትቶ በእግዚአብሔር አምኖ መልካም ሥራን ስለሠራ ነው።

፳፫. በሰሙነ ሕማማት የበዓለ ወልድ ይሰገዳል? አዎ ከሆነ መልስዎ ጎንደር በአታ፣ ዙር አባ፣ አክሱም ቤተልሔም አይሰገድም። በማኅሌት በኩል ሥርዓት ከእነዚህ ትልልቅ አድባራት ውጭ እንዴት ነው?

መልስ፦ አዎ ይሰገዳል። ሰሙነ ሕማማት ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት አንዱ ነው። ፍትሐ ነገሥት በጌታ በዓላት፣ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም በዓላት፣ ቅዳሜና እሑድ ስግደት እንዳይሰገድ ተገልጿል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14)። ይህ ግን ከሰሙነ ሕማማት ውጭ ነው። ሰሙነ ሕማማት የሚከበረው በስግደት ነው። ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት ደብሮች የማይሰገድ ከሆነ ቢሰገድባቸው መልካም ይሆናል። የክርክር ምንጭ ሆኖ የሚቀጥል ከሆነ ደግሞ ሲኖዶስ ጉዳዩን አይቶ ወጥ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ ይገባል።

፳፬. ጌታ ተሰቅሎ ሲሞት ሥጋ ብቻ ነው የሞተው ወይም መለኮት ከሥጋ ፍጹም ስለ ተዋሐደ ሞተ ያሰኛል?

መልስ፦ ከዚህ ላይ ተጠንቅቆ መናገር ይገባል። መለኮት ፈጽሞ የማይሞት ነው። መለኮት ሞተ የምንል ከሆነም ሥላሴ ሞቱ ያሰኛል። "ለእመ ትቤ ከመ መለኮት ሞተ አንተ ትከውን ቀታሊሆሙ ለሥሉስ ቅዱስ፤ መለኮት በባሕርዩ ታመመ ሞተ ብትል ሥላሴ ሞቱ ያሰኝብሀል" እንዲል (ሃይ.አበ.11፥13)። መለኮት በሥጋ ሞተ ግን እንላለን። ይኸውም በተዋሕዶ ገንዘብ ባደረገው ሥጋ ሞተ ማለት ነው። በተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ስለሆነ በሥጋ የሆነው ሁሉ የቃል ገንዘቡ ነውና። "በባሕርዩ ሕማም ሞት ሳይኖርበት የሥጋ ሕማም ለቃል ተነገረለት" እንዲል (ሃይ.አበ.96፥35)።

፳፭. "አብ አብ መባሉ አብ ስለሆነ ነው እንጂ ወላዲ አሥራፂ ስለሆነ አይደለም ማለትም ወልድን ከወለደ መንፈስ ቅዱስን ካሠረጸ ዘንድ የወጣለት ስም አይደለም በአካላዊ ተጸውዖ ስሙ ጥንቱን አብ ነው እንጂ። ወልድም ወልድ የተባለው ከአብ ስለተወለደ አይደለም የአካላዊ ተጸውዖ ስሙ ጥንቱን ወልድ ነው እንጂ። መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ መባሉ ከአብ ስለ ሠረጸ አይደለም የአካላዊ ተጸውዖ ስሙ ጥንቱን መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ" የሚሉ አሉ። ሃይ.አበ.98፥4 ላይ ደግሞ አብን አብ ብንለው ወልድን የወለደ መንፈስ ቅዱስን ያሠረጸ ስለሆነ ነው። ወልድንም ወልድ ብንለው ከአብ ስለተወለደ ነው። መንፈስ ቅዱስንም መንፈስ ቅዱስ

**ብንለው ከአብ ስለ ሠረጸ ነው ለአብ ለወልድም እስትንፋሳቸው ስለሆነ ነው ይላል። እንዴት ነው?**

መልስ፦ አካለ አብ አብ፣ ወላዲ፣ ልብ ሊባል ይችላል። ወላዲ ሲባል ግብሩን፣ ልብ ሲባል ከዊኑን፣ አብ ሲባል አካሉን ያመለክታል። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ የአካላት ስም እንደሆኑ "ወናሁ ንቤ ካዕበ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ዳግመኛም እነሆ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ናቸው እንላለን። ወአኮ እሉ አስማት ዘቦኡ ላዕሌሆሙ ድኅረ፤ እሊህ ስሞች አካላት ተቀድመው ተገኝተው ኋላ የተጠሩባቸው አይደሉም። አላ እሙንቱ አካላት፤ አካላት ሲገኙ የተገኙ ናቸው እንጂ" እንዲል (ሃይ.አበ.13፥4)። በተጨማሪም በምሥጢረ ሥላሴ አካላት ቀድመው ግብር የሚከተል ሳይሆን ግብሩም አካሉም በአንድ ጊዜ የነበሩ ስለሆኑ አካለ አብ አካለ ወልድን ያለጊዜ መቀዳደም ወልዶታል። በመውለዱ ወላዲ ይባላል። ወልድም በመወለዱ ተወላዲ ይባላል። ወላዲ መባል አብ ከመባል፣ ተወላዲ መባል ወልድ ከመባል ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ ብዙ ቦታ ላይ ስለወለደ አብ ተባለ ሲልም ይገኛል። ሁለቱንም አስተባብሮ በአካል ስምነትም በግብር ስምነትም መጠራት እንደሚችል የሚገልጽልን የሃይማኖተ አበው ክፍል "ወአስማቲሆሙ ለአካላት አኮ ግብር ከንቱ፤ የአካላት ስማቸው በሐሰት የተጠሩበት አይደለም። ሶበ ንሰምዮ ለአብ አበ በእንተ ዘኮነ ወላዴ፤ አብን አብ ብንለው ስለወለደ ነው። ወወልድኒ ወልደ በእንተ ዘተወልደ እምአብ፤ ወልድን ወልድ ብንለው ስለተወለደ ነው" ብሏል (ሃይ.አበ.98፥4)።

**፳፰. ሥጋ ከመለኮት ጋር ሲዋሐድ ሙሉ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ተዋሕዷል? ሥጋ በቃል ገንዘብ አብን መንፈስ ቅዱስን አህሏል። በአካል ወይስ በኩነት ለአብ እና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው የሆነ? ሥጋ በቃል ርስት ዓለም ከመፈጠር በፊት ኖሯል?**

መልስ፦ አዎ ሥጋ ቃልን ሲዋሐድ ብርሃን በመስኮት ተከፍሎ እንደሚገባው ተከፍሎ የተዋሐደ አይደለም። በምልአት ተዋሕዷል እንጂ። "ወኢተዋሐደ በመን*ፈ/ቀ ህላዌ፤ ከባሕርይ ክፍሎ አልተዋሐደም" እንዲል (ሃይ.አበ.47፥32)። ሥጋም በቃል ገንዘብ አብን መንፈስ ቅዱስን አህሏል። ሥጋ በቃል ገንዘብ በኩነት ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ሆኗል። ርስት የሚነገረው ከተዋሕዶ በኋላ ነው። ከተዋሕዶ በፊት የነበረው ዕሩቅ ቃል ነው። ሥጋ ቅድመ ዓለም የነበረውን ቃል ገንዘብ አደረገ እንጂ ቅድመ ዓለም አልኖረም።

**፳፱. ካህናት አባቶች ማዕድ ባርከው ቡራኬ ሲሰጡን መጀመሪያ ደረቁን ብቻ (ወጥ ሳይነካው) ለምን እንበላለን?**

መልስ፦ ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻ ያለው ትውፊት ነው። "እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ" እንዲል (ማቴ.14፥19)። አሁንም ሰው ሲበዛ ካህናት ለዲያቆናት ሰጥተው ዲያቆናት ደግሞ ተቀብለው ለሕዝቡ ያደርሳሉ። ለጊዜው ጌታ ደረቅ እንጀራን ባርኮ ስለሰጠ በደረቅ እንጀራ ይደረጋል።

፴. አርጋኖን የሰኞ ምዕራፍ 9 ቁጥር 16 ላይ "ሱራፌልና ኪሩቤል ይሰግዱልሻል" ይላል፡፡ ምን ማለት ነው? መላእክት እንዴት ለፍጡር ሊሰግዱ ይችላሉ? አርጋኖን የማክሰኞው ምዕራፍ 9 ቁጥር 2 "እግዚአብሔር ሁሉን ለድንግል ማርያም አስገዛላት" ሲልስ ምን ማለት ነው?

መልስ፦ ለቅድስት ድንግል ማርያም ኪሩቤል የሚሰግዱላት ስግደት የጸጋ ወይም የአክብሮት ስግደት ነው፡፡ ይኸውም አምላካቸውን በሥጋ ስለወለደችላቸውና ንጽሕት በመሆኗ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ለድንግል ማርያም አስገዛላት ማለትም ከፍጡራን በላይ ሁሉ አደረጋት ማለት ነው፡፡ ሁሉ በጸጋ ለእርሷ የሚሰግድ መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ በክብር ከፍጡራን ሁሉ በላይ ትበልጣለችና፡፡

፴፩. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ እንዴት ታወቀ? ማረጋገጫውስ ምንድን ነው?

መልስ፦ እግዚአብሔርን ቃል በቃል የተናገሩ ቅዱሳን ነቢያት ጻፉት ተብለው የጻፉት በመሆኑ፣ ከጻፉት መካከል ለምሳሌ ሙሴን ብንመለከት ያ የተናገረው እግዚአብሔር ለመሆኑ ማስረጃ አምላካዊ ተአምራትን አሳይቶታልና (ዘፀ.4፥4)፡፡ ይህ ተአምር ደግሞ በሙሴ ሳይወሰን ለሕዝቡም ታይቷል፡፡ በሕዝቡ ሳይወሰን ለአሕዛብም ታይቷል (ዘፀ.10፥22)፡፡ በአሁኑ ዘመን ያለን ሰዎች በዚያ ዘመን ስላልነበርን ያንን ያወቅነው ደግሞ በቅዱስ ቅብብሎሽ ነው፡፡ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ ማረጋገጫው በውስጡ የተጻፉ ትንቢቶች በመፈጸማቸው ነው፡፡ ለምሳሌ ድንግል በድንግልና ፀንሳ ልጅ እንደምትወልድ ከተነገረ ከ700 ዓመት አካባቢ በኋላ ክርስቶስ መወለዱ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት ያረጋግጥልናል (ኢሳ.7፥14)፡፡ የነቢያት ቃል፣ የኦሪት መጻሕፍት ትክክል ለመሆናቸው ደግሞ ጭቃን ወፍ አድርጎ በመፍጠር ፈጣሪነቱን ለሁሉ ያሳወቀ ክርስቶስ አረጋግጦልናል (ማቴ.5፥17)፡፡ አሁን ላይ ያለን ሰዎች ትላንትን ማወቅ የምንችለው ደግሞ በታሪክ ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ቸር ስለሆነ አሁንም ልባችንን አንጽተን ቀድሞ የተከናወኑ ድርጊቶችን ብቻ ሳይሆን የድርጊቶች ባለቤት እግዚአብሔርንም እስከማየት የምንደርስበትን እድል ሰጥቶናል (ማቴ.5፥8)፡፡

፴፪. በምሥጢረ ሥላሴ መወለድ እና መሥረጽ ልዩነቱ ምንድን ነው?

መልስ፦ መሥረጽ የሚባለው ከአብ የመንፈስ ቅዱስ መውጣት ነው፡፡ መወለድ የሚባለው ከአብ የወልድ መውጣት ነው፡፡ ወጣ መባል ለወልድም ለመንፈስ ቅዱስም ይነገራል፡፡ ለወልድ ሲነገር "ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ" ይላል (ዮሐ.16፥28)፡፡ ለመንፈስ ቅዱስ ሲነገር "ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ" ይላል (ዮሐ.15፥26)፡፡ የሁለቱ አወጣጥ ግን ይለያያል፡፡ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስን ሆኖ ስለወጣ ሠረጸ ሲባል ወልድ ቃልን ሆኖ ስለወጣ ተወለደ ተብሏል፡፡

፴፫. ምልጃ በሕይወተ ሥጋ እያለን ድካነታችንን እንድንፈጽም ያግዘናል እንጂ ከሞትን በኋላ የቅዱሳን ምልጃ አለ ማለት የክርስቶስን ቤዛነት እንደመተካት ነው የሚሉ አሉና የቤተክርስቲያናችን አስተምህሮ ስለዚህ ምን ይላል?

መልስ፦ የክርስቶስን ቤዛነት ማንም አይተካውም። በክርስቶስ ቤዛነት የምንተካው ብቻ ሳይሆን ከክርስቶስ ቤዛነት ጋር የምናስተካክለው ምንም ነገር የለም። ይህ የሌላ እምነት ሰዎች እኛን በሐሰት የሚከሱበት ውሸት ነው። የቅዱሳን ምልጃ እግዚአብሔር ለባለሟልነታቸው የሰጣቸው ጸጋ ነው። ቅዱሳን ራሱ በክርስቶስ ቤዛነት የዳኑ ናቸው። በተሰጣቸው ባለሟልነት እንዲለምኑልን ግን ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። ቅዱስ ጴጥሮስ በሥጋዊ ሞት ከተለየም በኋላ እንደሚማልድ በመልእክቱ ጽፏል። "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተኝ ከዚህ ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንዲሆን አውቃለሁና። ከመውጣቴም በኋላ እነዚህን ነገሮች እንድታስቡ በየጊዜው ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ" እንዲል (2ኛ ጴጥ.1፥14-15)።

፴፬. ከጥምቀት በፊት የሞቱ ሕፃናት ለምሳሌ 40 ቀን ወይም 80 ቀን ያልሞላቸው ሕፃናት መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ? ሌላው የውርስ ኃጢአት በክርስቶስ ተሽሯል ተብሏል። ነገር ግን ያልተጠመቁ ሕፃናት የውርስ ኃጢአት አለባቸው የሚል መጽሐፍ አንብቤ ነበር እና ግራ ተጋባሁ። የውርስ ኃጢአት ምንድን ነው? ሌላው ሕፃናቱን ከ40 እና 80 ቀን በፊት ማጥመቅ ይቻላል ወይ?

መልስ፦ መንግሥተ ሰማያት የሚገባውንና የማይገባውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ 40 ቀን ወይም 80 ቀን ያልሞላቸው ሕፃናት መንግሥተ ሰማያት ይገቡ ወይም አይገቡ አናውቅም። ያልተጠመቀ እንደማይድን ጌታ የተናገረው ቃል ሙሉ በሙሉ እውነት እንደሆነ እናውቃለን (ማር.16፥16)። ነገር ግን ጥምቀት በውሃ ብቻ ሳይሆን በደም፣ በእሳት፣ በእንባ የሚፈጸምባቸው መንገዶች ስላሉ ስለሕፃናት የምናውቀው ነገር የለንም። ምናልባት ለጥምቀታችን አድርሰን እያሉ አልቅሰው ይሆን ወይም አይሆን የምናውቀው ነገር የለም። እኛ ግን ቀናቸው ሳይደርስ ይሞታሉ ብለን የምንሰጋቸው ሕፃናት ካሉ 40 ቀን ወይም 80 ቀን ሳይደርስ በፊትም በሞግዚት ማጥመቅ እንደሚገባን በፍትሐ ነገሥት ተገልጿል (አንቀጽ 3)። ጥንተ አብሶ እና የውርስ ኃጢአት በክርስቶስ ሞት ተሽሯል። ስለዚህ ከዚህ በኋላ ሰው በኃጢአት ተይዞ ቢገኝ እንኳ በጥንተ አብሶ ወይም በመርገም ምክንያት ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔር አድርግ ያለውን ባለማድረጉ የሠራው ኃጢአት ነው። በመሠረቱ ኃጢአት አይወረስም። መርገሙን የውርስ ኃጢአት እያሉ መግለጽ ልማድ ስለሆነ እንጂ።

፴፭. በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነት ምን ያህል ነው? ለምሳሌ የሆነ ነገር ከተፈጠረ መጥፎም ይሁን በጎ እግዚአብሔር እንዳደረገው በምን እናውቃለን? እግዚአብሔር የሠራው እስከ ምጽአት የሚሠራ ሲስተም ነው ወይስ እርሱ ነው አሁንም የሚሠራው?

መልስ፦ እግዚአብሔር ቀድሞም ይሠራል አሁንም ይሠራል። ሲስተም ዘርግቶ የተወን አይደለም። በየጊዜውና በየሰዓቱ ፍጥረታትን ሁሉ የሚመግብ እርሱ ራሱ ነው እንጂ። "አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል። እኔም ደግሞ እሠራለሁ" እንዲል (ዮሐ.5፥17)። የእግዚአብሔርን ሥራ ለራሱ መተው ነው እንጂ እኛ አናውቀውም። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ነጻነትን ሰጥቶታል። ስለዚህ ሰው በራሱ ነጻነት በሚሠራው ሥራ ሙሉ ተጠያቂው ራሱ ሰውየው ነው። ሰው ነጻነቱን ተጠቅሞ ሌሎችን ሊጎዳ ሲል ወይም ራሱን ሊጎዳ ሲል ደግሞ እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ በብዙ መልኩ ወደ በጎ ሐሳብ ይመለስ ዘንድ ረድኤቱን ሊሰጥ ይችላል። ስለዚህ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ላይ የበጎ ጣልቃ ገብነትን ሊገባ ይችላል። ይህም በእኛ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው። እኛ በጸሎትና በሌሎችም መንገዶች ስንጠይቀው ከችግራችን ያወጣናል።

፴፮. ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገው በግዘፍ አካል (በሥጋ) ነው? ከአካል ህልውና አንጻር፣ ከግብር አንጻር፣ ከኩነት አንጻር ድኅረ ዕርገትን አብራሩልኝ?

መልስ፦ ከተዋሕዶ በኋላ ሥጋ ውሱንነቱን ሳይለቅ ምሉእ ሆኗል። ቃልም ምልአቱን ሳይለቅ ተወስኗል። ይህ ተዋሕዶ ደግሞ ዘለዓለማዊ ነው እንጂ በዘመን ብዛት የሚቀር አይደለም። ስለዚህ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ የነበረውን፣ በመቃብር ተቀብሮ የነበረውን፣ ከትንሣኤ በኋላ ቶማስ የዳሰሰውን ግዙፍ ሥጋን ይዞ ወደ ሰማይ ዐርጓል። በዚህ ምድር ምንም እንኳ ረቂቅ ነፍስ ብትኖረንም በግዙፍ ሥጋ እየተያየን እንደምንኖር ሁሉ በትንሣኤ ደግሞ ግዙፍ ሥጋ ሳይጠፋ በነፍስ መደበኛነት በዐይነ ነፍስ በርቀት [ቀ ይጥበቅ] እየተያየን እንኖራለን። ክርስቶስም ረቂቅም ግዙፍም ሆኖ ሳለ በዚህ ምድር በግዘፍ እንደታየ ከትንሣኤ በኋለ ደግሞ ግዘፉን ሳይለቅ በርቀት ይኖራል ማለት ነው። ከግብር አንጻር ከትንሣኤ በኋላ ባለመራብ፣ ባመጠማት፣ መከራ ባለመቀበልና በመሳሰለው ግብር ጸንቶ ይኖራል። ከኩነት አንጻር የሚለወጥ ነገር የለም። በፍጹም ሰውነቱ በፍጹም አምላክነቱ በተዋሕዶ ጸንቶ ይኖራል።

፴፯. ክርስቶስ ገና ሳይሰቀል ስለምን ሥጋዉን ደሙን እንደሰጣቸው፤ ለምን ከበሉ በኋላ እንዳቆረባቸው፤ ለምንስ በኅብስት እና በወይን አምሳል ቁርባኑን እንደሰጣቸው ቢያብራሩልን?

መልስ፦ ሥጋውን ሳይሰቀል በፊት ለምን እንደሰጣቸውና ከበሉ በኋላ ለምን እንዳቆረባቸው የሚያውቀው ራሱ ክርስቶስ ነው። መጽሐፍ ላይ ለምን ይህንን እንዳደረገ የሚገልጽ ምክንያት እስካሁን አላገኘሁም። በኅብስትና በወይን ያደረገበትን ምክንያት ግን መተርጕማን በብዙ መልኩ ገልጸውታል። ስንዴ ስብ ይመስላል። አማናዊውን ሥጋ ይመስል ዘንድ በስንዴ ሆኗል ብለዋል። ወይንም ደምን ስለሚመስል ነው። በተጨማሪም ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ነው (መዝ.4፥7)።

፴፰. "ሰላም ለኪ እመቤቴ ኪዳነ ምህረት ሆይ! ሰላምታ ላንቺ ይገባል፥ አለኝታ ተስፋ አንቺ ነሽና ሰላምታ ላንቺ ይገባል፥ ኃጥአንን አማልደሽ ለምታጸድቂ ላንቺ ሰላምታ ይገባል፥ ከዘጠናው

በጎች ተለይቶ የጠፋ በግ አዳምን የምትፈልጊ ለአንቺ ሰላምታ ይገባል" ይላል:: እና ማቴ.18፥11-13 ካለው ጋር አይጋጭብንም?

መልስ፦ አይጋጭም:: የጠፋውን አዳም የፈለገውና ያዳነው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱ የነሣው ሥጋ ደግሞ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተገኘ ስለሆነ ስለእርሱ ለመናገር በመገኛው ገልጾት ነው:: በአዳም ሁሉንም ሰው መናገርም ነው:: የጠፋውን ሰው በምልጃዋ የምታድን በመሆኗ ነው:: አንቺው ነሽ ተስፋው ለአዳም እንደሚለው ይተረጎማል:: ተስፋውን ይዛ ስለመጣችለት የተስፋውን ተስፋ ተስፋ እንዳላት ማለት ነው::

፴፱. በዳግም ምጽአት የሰው ልጅ የሆነ ሁሉ ለፍርድ ይቆማልን? እንደዚህ ከሆነ ማመን አለማመን ሳይሆን የሚጠየቁትን ስድስቱን ቃላት የፈጸመ ሁሉስ በቀኝ ይቆማል ወይ?

መልስ፦ አዎ በዳግም ምጽአት ጊዜ የሰው ልጅ ሁሉ ለፍርድ ይቆማል (ማቴ.25፥32):: በጌታ ቀኝ ለመቆም ማመን ግዴታ ነው:: ያላመነ አይድንምና (ማር.16፥16):: ስድስቱ ቃላት ከማመን በተጨማሪ ሰው ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች ናቸው:: ነገር ግን ሰው እምነት ሳይኖረው በጎ ሥራ ቢሠራ አይድንም::

፵. በቅዱሳን ገድል፣ ድርሳንና ሌሎችም መጻሕፍት ሙሉ በሙሉ የመቀበል ግዴታ አለብን ወይ? ካለብንስ በውስጥ ቤተክርስቲያንን የማይመጥኑ ጽሑፎች በውስጥ አሉ:: ለምሳሌ በገድለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ላይ (ከምዕራፍ 26-28) አንድ አንድ ገድል ላይ 26 ላይ ከደብረ ሊባኖስ ዕትም ላይ 28 አለና:: የብሔር ጥለቻ የሚመስሉ ነገሮች ይታያሉ:: ለአገው ሕዝቡ ሳይገባው ነው 333 ዓመት የገዛው ይላል:: ስለዚህ ባይገባስ ለምን ቤተክርስቲያን ታቦት ቀርጸ ቅዱስ ላሊበላ ብላ ሥራዉን ታከብራለች? ይህ እንዴት ይታያል? ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአቡነ መብዓ ጽዮን ገድልም አገው ሕዝብ ድባን የሚባል ጣዖት አምላኪ ነበር ይላል:: ይህ ደሞ ትክክል አይደለም:: ለምን ቢባል በቋንቋቸዉ ድባን ማለት እግዚአብሔር ነው አሁንም ቢሆን እየጠሩት የሚገኙት አጠቃቀም ነው:: ስለዚህ ይህን እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

መልስ፦ ቅዱሳት ገድላትን ሙሉ በሙሉ የመቀበል ግዴታ አለብን:: ነገር ግን በቅዱሳት ገድላት ግለሰቦች የራሳቸውን ጥላቻ የመጽሐፉ እያስመሰሉ የጻፉትና ያሳተሙት ብሔርን ከብሔር የሚያጋጭ መልእክት ያላቸው ሐሳቦችን በባለፈው ቅዱስ ሲኖዶስ ገድለ ዮሐንስ መጥምቅ ላይ የነበሩ አስተምህሮን የሚጥሱ ቃላትን መርምሮ ውድቅ እንዳደረጋቸው ሌሎችንም እየመረመረ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የማይሄዱትን ተከታትሎ የማረም ግዴታ አለበት:: ከላይ የተጠቀሱ ታሪኮችንና ሌሎችንም ቤተክርስቲያን በሊቃውንት ጉባኤ አማካኝነት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የሚቃረኑትን የማረም ኀላፊነት አለባት:: አዋልድ መጻሕፍት አባታቸውን መጽሐፍ ቅዱስን መስለው ይጻፋሉ እንጂ ከእርሱ ተቃራኒ ሆነው አይጻፉምና::

## ፵፩. ጥሬ ሥጋ መብላት ተፈቅዷል ወይስ አልተፈቀደም?

መልስ፦ ጥሬ ሥጋ መብላት በብሉይ ኪዳንም በሐዲስ ኪዳንም የተከለከለ ነው። በብሉይ ኪዳን "ጥሬውን በውኃም የበሰለውን አትብሉ። ነገር ግን ከራሱ ከጭኑ ከሆድ ዕቃው ጋር በእሳት የተጠበሰውን ብሉት" ይላል (ዘፀ.12፥9)። ይህንንም መተርጉማን ሲተረጉሙ ብርንዶውን አትብሉ ማለት ነው ብለው ተርጉመውታል። ብርንዶ ማለት ደግሞ ጥሬ ሥጋ ማለት ነው። ይህ በሐዲስ ኪዳንም የተከለከለ ነው። "ነገር ግን ከጣዖት ርኵሰትና ከዝሙት ከታነቀም ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው እቆርጣለሁ" እንዲል (የሐዋ.ሥራ 15፥20)። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ላይ ከደም መራቅን ከብርንዶ (ጥሬ ሥጋ) መራቅ እንደሆነ ገልጾታል።

## ፵፪. አዋልድ መጻሕፍትን ከትክክለኛ ቦታ መቀዳተቸውን በምን ማረጋገጥ እንችላለን? ኃላፊነቱስ የማን ነው?

መልስ፦ አዋልድ መጻሕፍት የሚባሉት በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረትነት የሚጻፉ የዶግማ፣ የሥርዓት፣ የዜማ፣ የጸሎት፣ የታሪክና የመሳሰሉ መጻሕፍት ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በየዘመናቱ የሠራቸው ታላላቅ ሥራዎች ተጽፈዋል። ወደፊትም እግዚአብሔር እስከ ዕለተ ምጽአት በደጋግ ሰዎች እያደረ መልካም ሥራን እየሠራ ይኖራል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈ በኋላ የሠራቸውን ሥራዎች ከዚያ በኋላ የተነሡ ሰዎች እየጻፉልን በገድላት፣ በድርሳናትና በመሳሰሉት መንገዶች እየጻፉ አድርሰውናል። ስለዚህ አዋልድ መጻሕፍት ከትክክለኛ ቦታ መቀዳታቸውን የምናረጋግጠው አባታቸውን መጽሐፍ ቅዱስን መስለው በመጻፋቸው ነው። ይህንን እየገመገመ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚያስገባ ደግሞ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። በገድላት ስም የሚጻፉ በውስጣቸው ጥላቻን፣ ክሕደትን የያዙ መጻሕፍት ካሉ ደግሞ ክትትል በማድረግ የማስተካከል ኃላፊነት የቅድስት ቤተክርስቲያን ነው። አዋልድ መጻሕፍት ከትክክለኛ ምንጭ መቀዳታቸውን የምናረጋግጠው በይዘታቸው ነው። ከፍ ባለ የመንፈሳዊነት ደረጃ በመድረስም [በብቃት] ማረጋገጥ ይቻላል።

## ፵፫. የአሕዛብ ሁሉ አንድነት (All Nations Acknowledge One God)። በዘካ.14፥9 እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ እንደሚነግሥና ስሙም አንድ እንደሚሆን ይናገራል። ዛሬ ግን ዓለም በብዙ ሃይማኖቶች ተከፋፍላለች። ይህ ትንቢት በኢየሱስ በኩል ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል?

መልስ፦ ይህንንና ከዚህ ቀጥለው በተከታታይ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ለመመለስ መጀመሪያ ስለትንቢት ምንነት በጥቂቱ መረዳት ያስፈልገናል። ትንቢት ያለፈውን ዘመን ሁኔታ፣ የአሁኑን ዘመን ሁኔታና የወደፊቱን ዘመን ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት አውቆ መናገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ካሉ ትንቢቶች ደግሞ ባለብዙ ትርጉም ያላቸው አሉ። አንዳንዶች በዘመናቸው ላለ ሁኔታ ተነግረው በተጨማሪ በኋላ ዘመን

የሚደረገውን የሚገልጹ አሉ። ለምሳሌ ዘፀ.12፥46 ላይ የበጉን አጥንት አትስበሩ ተብለው ለጊዜው እስራኤላውያን ለሚያርዱት በግ የተነገረ ግን ደግሞ ለኋለኛው ዘመን የሆነ ትንቢት አለ። ይህ ትንቢት በተጨማሪ ስለክርስቶስ የተነገረ እንደሆነ ደግሞ "ከእርሱ አጥንት አይሰበርም" የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው ተብሎ ተገልጿል (ዮሐ.19፥36)። ከዚህ ከትንቢተ ዘካርያስ (ዘካ.14፥9) የተገለጸውም ትንቢት እንደመሆኑ ዓረፍተ ነገሩ አንድ ቢሆንም ስለብዙ ጉዳዮች የተነገረ ነው። ለጊዜው እስራኤልን አሕዛብ እነ አንጥያኮስ እንደሚያጠፏት ጥቂቶች ከጥፋት እንደሚድኑና በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር በረድኤት እንደሚጠብቃቸው የሚገልጽ ነው። እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ይነግሣል ማለቱ ለጊዜው የእስራኤልን ጠላቶች አጥፍቶ አሕዛብም አምላክነቱን ተረድተው ይኖራሉ ማለት ነው። እግዚአብሔር ቀድሞም በምድርም በሰማይም ነግሦ የሚኖር አምላክ ነው። ነግሦ የሚኖረውን ይነግሣል ማለቱ ስለምን ነው ከተባል ለጊዜው ለብዙ ሰዎች ረድኤት መስጠቱን ያመለክታል። ሌላው ስለወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ይገልጻል። ወልደ እግዚአብሔር ሰው ሲሆን ሕዝብንና አሕዛብን አንድ አድርጓልና። ሌላው ስለምጽአት ይተረጎማል። በዕለተ ምጽአት ሁሉም የእግዚአብሔርን ንጉሥነት ያምናልና እግዚአብሔር ይነግሣል ተብሏል። ስለዚህ ከዚህ ትንቢት በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ አለ። በምጽአት የሚፈጸም አለ። ከአሕዛብ ነገሥታት ከነአንጥያኮስ አድኖ እነርሱን ሰላም ባደረገበት የሚተረጎምበት ሁኔታም አለ።

፶፬. የዘር ሐረግ እና የድንግል መውለድ (The Lineage of David)። መሲሑ የዳዊት ዘር መሆን ያለበት በአባት በኩል እንደሆነ የአይሁድ ሕግ ይናገራል። ኢየሱስ ግን ከድንግል ከተወለደ (ያለ ምድራዊ አባት) እንዴት የዳዊት የሥጋ ዘር ሊባል ይችላል? ዮሴፍ አሳዳጊው እንጂ የወለደው ካልሆነ የዘር ሐረጉ እንዴት ይተላለፋል? ዘኍ.1፥18።

መልስ፦ መሲሑ የዳዊት ዘር መሆን ያለበት በአባት በኩል ነው የሚል መጽሐፍ እንኳ የለም። ኢየሱስ ክርስቶስን የአብርሃም ልጅ ነው፣ ከዳዊት ዘር የተገኘ ነው የምንልበት ምክንያት ግን እናቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከዳዊት ዘር ስለተወለደችና እርሱ ክርስቶስም ከእርሷ ስለተወለደ ነው። ዮሴፍና ድንግል ማርያም ሁለቱም ከዳዊት ዘር የተወለዱ ናቸው። የዘር ሐረጋቸው እስከ ዳዊት ሲቆጠርም ተመሳሳይ ነው። የትውልድ ሐረግ የሚጽፉት ግን በወንድ ስለሆነ ሐረጋቸው ሲቆጠር ተመሳሳይ ከሆነ የሚያመጣው ለውጥ ስለሌለ በባህላቸው ለመቁጠር በአሳዳጊ አባቱ በዮሴፍ ተቆጥሯል።

፶፭. ዓለም አቀፍ ሰላም (Universal World Peace)። በኢሳ.2፥4 ላይ መሲሑ ሲመጣ ሕዝቦች ሰይፋቸውን ማረሻ ለማድረግ እንደሚቀጠቅጡና ጦርነት እንደማይኖር ይናገራል። ነገር ግን ባለፉት 2,000 ዓመታት ዓለም በጦርነት ተሞልታለች። ይህንን እንዴት ታዩታላችሁ?

መልስ፦ በዚህ በኢሳይያስ ትንቢት የተገለጸውም ለጊዜው በደጋግ ነገሥታት በሕዝቅያስ፣ በኢዮስያስ፣ በዘሩባቤል የሚደረገውን ደግ ዘመን ለመግለጽ የተነገረ ነው። እስራኤላውያን ጣዖት እያመለኩ ለብዙ ዘመናት በአሕዛብ መከራ ደርሶባቸዋል። ከዚህ በጠቀስኳቸው

ነገሥታት ግን አምልኮተ እግዚአብሔር ስለነበረ አንጻራዊ ሰላም ነበረ። ይህንን ለመግለጽና ዘመኑ ከሌላው በተሻለ ሰላም መሆኑን ለመግለጽ ሰይፋቸውን ማረሻ ያደርጋሉ ተብሏል። ሰይፍን ማረሻ ማድረግ ትእምርተ ሰላም (የሰላም ምልክት) ነውና። በተጨማሪ ስለክርስቶስ የተነገረ ነው። በዚህ ጊዜ አሕዛብ የሚለው በአጋንንት ይተረጉማል። ከክርስቶስ በፊት በመርገም ምክንያት አጋንንት ሰውን በመቆራኘት ኃጢአት ሲያሠሩት ይኖሩ ነበር። ክርስቶስ ሲመጣ ግን መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን አጥፍቷልና ሰላም ይሆናል ማለቱ ስለዚህ ነው። ጦርነት አይኖርም መባሉ ለጊዜው ከላይ በጠቀስናቸው ነገሥታት ጦርነት ብዙ እንደማይኖር ያመለክታል። እንጂ ባለፉት 2000 ዓመታት ስለተደረጉ ሥጋዊ ጦርነቶችና ወደፊትም ሊደረጉ ስለሚችሉት ሥጋዊ ጦርነቶች የተነገረ አይደለም።

፵፮. የእስራኤል ልጆች መሰብሰብ (The Gathering of Israel)። በኢሳ.11፥12 ላይ መሲሑ የተበተኑትን የእስራኤልን ልጆች ከዓለም ዳርቻ እንደሚሰበስብ ተጽፏል። ኢየሱስ ሲመጣ ግን አይሁድ ይበልጥ ተበተኑ እንጂ አልተሰበሰቡም። ይህ ትንቢት እንዴት ተፈጸመ ትላላችሁ?

መልስ፦ ይህ ትንቢትም ለጊዜው ወደ ባቢሎንና ወደ ሌሎች ሀገሮች በምርኮና በልዩ ልዩ ምክንያቶች ተማርከው ሄደው የነበሩ እስራኤላውያን በዘሩባቤል ጊዜ ከምርኮ ድነው ለ70 ዓመት ጠፍታ ወደነበረችው ኢየሩሳሌም ይመለሳሉ ማለት ነው። ፍጻሜው ግን ስለእስራኤል ዘነፍስ የተነገረ ነው። በአዳም በደል ምክንያት ወደ ሲኦል ተጉዘው የነበሩ ነፍሳት በኢየሩሳሌም ወደ ተመሰለችው ገነት በክርስቶስ አማካኝነት ይመለሳሉ ማለት ነው። ሁለቱም ማለትም እስራኤል ዘሥጋ በዘሩባቤል እስራኤል ዘነፍስ በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽመዋል።

፵፯. የመቅደሱ መታደስ (Rebuilding the Temple)። በሕዝ.37፥26-28 መሠረት መሲሑ መቅደሱን ለዘለዓለም በመካከላቸው እንደሚተክል ይናገራል። ኢየሱስ በመጣ በ70 ዓ.ም ግን የነበረው መቅደስ ፈረሰ። ይህ ከትንቢቱ ጋር እንዴት ይስማማል?

መልስ፦ በብሉይ ኪዳን ዘለዓለም የሚሉት ቃላት ፍጻሜ የሌለውና ፍጻሜ ያለው ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ፍጻሜ ያለው ዘለዓለም ብዙውን ለመግለጽ ይነገራል። ለምሳሌ ሰሎሞን ለዘለዓለም እንደሚነግሥ ተነግሯል (2ኛ ሳሙ.7፥12-13)። ከዚህ የተጠቀሰው ዘለዓለም ፍጻሜ ያለው ዘለዓለም ነው። ዘለዓለም ለእግዚአብሔር ሲነገር ደግሞ ፍጻሜ የሌለው ይሆናል (መዝ.146፥10)። በትንቢተ ሕዝቅኤል የተነገረው የመቅደስ መታደስም ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ታላቁ ቤተመቅደስ እንደሚሠራ ያመለክታል። በዚህ ሲተረጎም የተጠቀሰው ዘለዓለም ፍጻሜ ያለው ነው። ፍጻሜ በሌለው መቅደስ ሲተረጎም ለሰው ይነገራል። በሐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚባል የሰው ሰውነት ነውና (1ኛ ቆሮ.3፥16)። ሰማይና ምድር ሲያልፍ ሰው ግን እግዚአብሔር አድሮበት፣ የእግዚአብሔር መቅደስ ሆኖ፣ የጸጋ አምላክ ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል። ለክርስቶስ ሲነገር በዚህ ፍጻሜ በሌለው ዘለዓለም ይተረጎማል።

**፺፰. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባቶች አገልጋዮች ትላልቅ በሚባሉ ሰዎች የሚጸለዩ ጸሎቶች ቱላዳን፣ ባርቶስ፣ መልክአ ራጉኤል ባለጠልሰም እየተባሉ የሚጠሩ መጻሕፍት እውነተኛ የጸሎት መጻሕፍት ናቸው ማለት እንችላለን?**

መልስ፦ ጠልሰም የሚባለው በብራና ወይም በወረቀት የተሳለ ሥዕል ነው። ስለዚህ ባለጠልሰም ሲባል ባለሥዕል ማለት ነው። ይህ በራሱ ችግር የለበትም። ችግሩ ጠልሰም እየተባለ ኦርቶዶክሳዊ ትምህርትን በማይወክል መልኩ ግለሰቦች ሥዕል እየሣሉ/እያሣሉ በቅዱስ ሲኖዶስ ማዕከላዊነት ያልተዘጋጁ መሆናቸው ላይ ነው። ከላይ የተጠቀሱ መጻሕፍትም በማዕከላዊነት በቅዱስ ሲኖዶስ የተፈቀዱ ይሁኑ ወይም አይሁኑ መረጃው የለኝም። ይዘታቸውንም ስላላየሁት ምንም ማለት አልችልም። በፍትሐ ነገሥት እንደተገለጸው ግን ሁሉም ምእመናን እንዲሁም ሊቃውንት እንዲጸልዩት የታዘዘ አቡነ ዘበሰማያት፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ውዳሴ ማርያም ነው። ከእነዚህ የሚበልጥ ጸሎት የለም። ስለዚህ ሌሎች ያልተረጋገጡ መጻሕፍት ላይ ከምናተኩር በተጻፈልን ብንጸልይ እላለሁ።

**፺፱. የስቅለት ዕለት ቀኑን ሙሉ ግብረ ሕማማትን የሚያክል መጽሐፍ ሲነበብ ውሎ አንድ የበራ ጧፍ መቋሚያ ላይ አስረው በመርገም መድመደም ወፍኖቶሙሰ ለኃጥአን ትጠፍእ ብሎ ማጠናቀቅ አያስነቅፍም?**

መልስ፦ አረዳዳችንን ማስተካከልና አፈጻጸሙን በተረጋጋ መልኩ ማድረግ እንጂ አያስነቅፍም። ወፍኖቶሙሰ ለኃጥኣን ትጠፍእ ብለው ጧፉን ማጥፋታቸው ተግባራዊ ትምህርት ነው። ኃጥኣን ክፉ ሥራን ቢሠሩ እንደሚጠፉ ማስረጃ መንገድ ነው። ነገር ግን መቋሚያ እስኪሰበር በታላቅ ግርግርና ጨዋታ ማድረግ አይፈቀድም። ቤተክርስቲያን የጸሎት፣ የጸጥታ፣ የትምህርት ቦታ እንጂ መቋሚያ የሚሠብሩባት፣ የሚሳለቁባት አይደለችምና (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 1)።

**፻. በወላጆች ንስሓ አባት ልጅ መቀጠል አለበት ወይስ የራሱን አባት መያዝ አለበት? መያዝ ካለበት ከዕድሜም ሆነ ሌላ መስፈርት ካለ መቼ ነው የራሱን አባት መያዝ ያለበት?**

መልስ፦ በወላጆች ንስሓ አባት ልጅ መያዝ አለበት የሚል አላገኘሁም። ሁሉም ሰው ንስሓ አባት መያዝ እንዲገባው እንጂ የሁሉም አንድ አባት ካልሆነ የሚል አስገዳጅ ሥርዓት የለም። በማናቸውም ዕድሜ ያለ ሰው ንስሓ አባትን መያዝ ይገባዋል።

**፻፩. ድርሳነ ኡራኤል ገጽ 138 የየካቲት መጨረሻ ተአምር ላይ ሁለቱም አፍ ለአፍ ገጥመው ተሳሳሙ። ያን ጊዜ በመንገድ ያገኘቻት ሴትዮ የፀነሰች ስለነበረች የፀነሰችው ሴት ምራቅ ባልፀነሰችው ሴት አፍ ገባና ከወንድ ጋር ሳትገናኝ በዚሁ ብቻ ፀነሰች ይላል። አፍና አፍ ገጥሞ መሳሳም ይቻላልን? ከወንድ ሳትገናኝ በምራቅ እንዴት ይፀነሳል?**

መልስ፦ መሳሳም የመዋደድ (የፍቅረ ቢጽ) ምልክት ነው። "በአፉ መሳም ይሳመኝ" እንዲል (መኃ.መኃ.1፥2)። በፍትሐ ነገሥትም አዲስ ኤጲስ ቆጶስ ሲሾም ራሱ ሿሚው ጳጳስ አፉን ይሳመው ተብሏል (ፍት.ነገ.5)። በዘመናችን ግን የፍትወት መገለጫ ሆኖ እንዲሳል መደረጉ እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው። በዘመናችን ይህ ምልክት የፍትወት ምልክት ተደርጎ ከተሳለ ግን መሰናክል ላለመሆን ይህንን መተው ይገባል። ልጅቷ በምራቅ ፀነሰች የሚለው አገላለጽም ተአምር ስለሆነ እኛ አስተያየት ልንሰጥበት የምንችለው አይደለም። ምክንያቱም ተአምር ማለት ራሱ በተፈጥሮ ሕግ ከተለመደው ሕግ ውጭ የሚደረግ ኃይለ እግዚአብሔር የሚገለጥበት ነውና።

፶፪. አዳም ነጻ ሆኖ ከተፈጠረ ለምን ይቀጣል?

መልስ፦ ለአዳም የተሰጠው ነጻነት ብቻ ሳይሆን ኃላፊነትም ጭምር ነው። ነጻ ፈቃዱን ተጠቅሞ መልካም ካደረገ መልካም እንደሚያገኘው፣ ነጻ ፈቃዱን ተጠቅሞ ክፉ ነገርን ካደረገ ክፉ ነገር እንደሚያገኘው ተነግሮታል። ስለዚህ ቅጣቱን የማስቀረትና የመቀጣት ሥልጣኑ በአዳም ላይ የተመሠረተ ነው። ስለዚህ የተቀጣው በራሱ ምርጫ ስለሆነ ከነጻነቱ ጋር የሚጋጭ ነገር የለውም።

፶፫. ሙዚቃ ሁሉ ኃጢአት ነው ወይ? መጽሐፍ ቅዱስ ዘፈንና ዘፋኝነትን ሲቃወም ምን ዓይነት ዘፈንን ነው የሚለው ጥያቄ አይሆንም? እዚሁ ጋር ተያይዞ ሌላኛው ደግሞ ያው ብዙ ጊዜ እንደሚነሳው በግሪኩ "ከመጠን ያለፈና ሥርዓት የሌለው ጭፈራ/ግብዣ" የሚለው በአማርኛው የተተረጎመው ግን "ዘፋኝነት" ይላል እርሱስ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ዘፈን ኀጢአት እንደሆነ በብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጿል። ለምሳሌ ምእመናን ወደዘፈን እንዳይሄዱ በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11 ተገልጿል። በሐዋርያት ሲኖዶስም "ለክርስቲያን ዘፈንን፣ መሰንቆን፣ መለከትን ይሰማ ዘንድ አይገባውም" ተብሏል (ዲድስ.27፥3)። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም "የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ ምኞትም በስካርም በዘፈንም ያለ ልክም በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና" ብሏል (1ኛ ጴጥ.4፥3)። መጻሕፍት መዝሙርን ዘፈን እያሉ የሚገልጹበት አግባብም አለ። መክ.3፥4 ላይ "ለመዝፈንም ጊዜ አለው" እንዲል። በዘፈንና በመዝሙር መካከል ያለው ልዩነት አንደኛው የይዘት ነው። ይኸውም የመዝሙር ይዘቱ እግዚአብሔር የሚመሰገንበት፣ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ የሚነገርበት፣ የቅዱሳን ተጋድሎ የሚወሳበት ነው። ሁለተኛው ዜማው ነው። በሀገራችን የቅዱስ ያሬድን ዜማ መሠረት ያደረገ መሆኑ ነው። የሆነ ሆኖ በጅምላ ከላይ ያልናቸውን ነገሮች ብንገልጽም ከድምፅ አወጣጥ፣ ከዜማው ስልት፣ ከግጥሙ ይዘትና ከመሳሰለው እንዴት መለየት እንዳለብን ዝርዝር ጉዳይ ተጽፎ አላገኘሁም።

**፶፬. ኃጢአትም ጽድቅም ያልሆነ ነገር አለ ወይ? ለምሳሌ አንድ ክርስቲያን ከእርሱ የሚጠበቁ ነገሮችን የሚያደርግበትን ሰዓት በማይጋፋ መልኩ (የጸሎት ጊዜውን ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ያለበትን ሰዓት) ስፖርት ቢሠራ፣ ልብ ወለድ ቢያነብ፣ ኳስ ቢጫወት ወይም ፊልም ቢያይ (ከመንፈሳዊው ጋር የማይጋጭ ግን ዓለማዊ የሆነ) ችግር አለው?**

> መልስ፦ ኃጢአትም ጽድቅም ያልሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ስፖርት መሥራት ጽድቅም አይደለም፣ ኃጢአትም አይደለም። ግብርና፣ ምሕንድስና፣ ሕክምና፣ በጠቅላላው የሳይንስ ዕውቀቶች በዚህ ምድር ሳለን የሚያገለግሉን እንጂ ለዘለዓለማዊው ሕይወት የሚያገለግሉን አይደሉም። በአሠራራችን ግን እነዚህን ወደ ጽድቅ ወይም ወደ ኃጢአት ልንወስዳቸው እንችላለን። ግብርና ጽድቅም ኃጢአትም አይደለም። በዕለተ እሑድ ቢያርሱ ግን ኃጢአት ይሆናል። አርሰው ካገኙት ቢመጸውቱ ደግሞ ጽድቅ ይሆናል። የእግዚአብሔርን ሕግ የማያስሽሩ ፊልሞችን ማየት፣ መንፈሳዊ አገልግሎታችንን ሳናቋርጥ ኳስ ብንጫዎት፣ ልብ ወለድ መጻሕፍትን ቢያነብ፣ የሳይንስ መጻሕፍትን ቢያነብ ምንም ችግር የለውም።

**፶፭. በምሴተ ኀሙስ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሐዋርያት ጋር ነበረች ወይስ አልነበረችም?**

> መልስ፦ በምሴተ ኀሙስ ድንግል ማርያም ከሐዋርያት ጋር ትኖር ወይም አትኖር እስካሁን ባነበብኳቸው መጻሕፍት አላገኘሁም። ስለዚህ የዚህን ጥያቄ መልስ አላውቀውም።

**፶፮. የእመቤታችን ትንሣኤ እንዴት ነበር? ማለት ለምሳሌ አልዓዛር መግነዝ ተፈቶለት በር ተከፍቶለት ነው። የእመቤታችንስ?**

> መልስ፦ ስለመግነዝ የተጻፈ ነገር አላገኘሁም። ነገር ግን የአልዓዛር ትንሣኤና የድንግል ማርያም ትንሣኤ ይለያያል። የአልዓዛር ትንሣኤ መልሶ ሞት ያለበት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ቢያስነሣውም በዚህ ምድር ትንሽ ቆይቶ መልሶ ሞቷል። የእመቤታችን ትንሣኤ ግን እንደክርስቶስ ትንሣኤ ዳግመኛ ሞት የሌለበት ትንሣኤ ነው። ለእርሷ ትንሣኤ በኵሩ ክርስቶስ ነው። እርሱ ደግሞ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል እንደተነሣ ሌላውም በኵሩን መስሎ ስለሚነሣ መግነዝ ፍቱልኝ እንደማይል የታወቀ ነው። ራሱ እግዚአብሔር ባወቀ ያስነሣዋል እንጂ።

**፶፯. እመቤታችን አዳም በገነት ይዞት የነበረውን ሥጋ ንጽሕና ነው በምድር የያዘችው? እኛስ ከትንሣኤ በኋላ የሚኖረን ሥጋ አዳም በገነት በነበረ ጊዜ የያዘውን ነው የምንይዘው?**

> መልስ፦ እመቤታችን አዳም በገነት ይዞት የነበረውን ንጽሕና ብቻ ሳይሆን የነበራት ከአዳም የበለጠ ንጽሕና ነበር። ከትንሣኤ በኋላ የሚኖረን ሥጋ መሞት፣ መራብ፣ መጠማት የማይስማማው ሥጋ ነው። የአዳም ሥጋ ግን እነዚህ ነገሮች ይስማሙት

የነበረ ሥጋ ነው። ስለዚህ ከትንሣኤ በኋላ የሚኖረን ሥጋ አዳም በገነት ሳለ ከነበረው ሥጋ የተለየ ሥጋ ነው።

፶፰. "ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬ ወደ አምላካችሁ" ሲል እንልና ወደ አባቴ አለ የባሕርይ አባቱ ስለሆነ ወደ አባታችሁ አለ የጸጋ አባታችን ነውና ካልን በኋላ ወደ አምላኬ የሚለውን "ሰው ስለሆነ፥ በሥጋ ይፈጥረዋልና" እንላለን (ማቴ.27፥46 አንድምታ)። አብ (አምላኬ የተባለው አካል) ለክርስቶስ የባሕርይ አምላኩ ነው?

መልስ፦ አብ ለክርስቶስ አምላኩ ነወይ የሚለው በሥጋ አዎ። በመለኮቱ ግን ሥጋውን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የፈጠረ ነው። በሥጋው አምላኩ እንደሚባል ግን በሃይማኖተ አበው ተገልጧል። ቅዱስ ኤጲፋንዮስ "እግዚአብሔር አብ አምላኩ ለወልድ ውእቱ በእንተ ትስብእቱ፤ እግዚአብሔር አብ ለወልድ በሰውነቱ አምላኩ ይባላል። ወአቡሁ ውእቱ በእንተ መለኮቱ ቀዳማዊ፤ በመለኮቱ ግን አባቱ ይባላል" ይላል (ሃይ.አበ.54፥9)።

፶፱. ድርሳነ መድኃኔዓለም ዘቀዳሚት መጨረሻ ገጽ 96 ይህ መስቀል እንደ እግዚአብሔር የከበረ እንደ ድንግል ማርያም ከፍ ያለ ነው። ሦስትነታቸው ትክክል የሚሆን እንደ አብ እንደ ወልድ እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ የማይለይ ነው ይላል። መስቀሉ እንዴት ከሥላሴ ጋር ይነጻጸራል?

መልስ፦ መስቀል እንደ እግዚአብሔር የከበረ ነው ማለት እግዚአብሔር በባሕርዩ ክቡር እንደሆነ መስቀል ደግሞ የክርስቶስ ደም ስለፈሰሰበት በጸጋ የከበረ ነው ማለት ነው። ይህን የመሰለ ንጽጽር በመጽሐፍ ቅዱስም ይገኛል። ለምሳሌ "እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል" ሲል ይገኛል (ዮሐ.17፥22-23)። አሁን በዚህ የሐዋርያት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን ከአብና ከወልድ አንድነት ጋር ተነጻጽሮ ቀርቧል። ቢቀርብም ግን የአብና የወልድ የባሕርይ አንድነት፣ የሐዋርያትና የእግዚአብሔር ደግሞ የጸጋ አንድነት መሆኑ ይታወቃል። የመስቀሉም በዚህ አግባብ የሚታይ ነው።

፷. ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ሰአሊ ለነ ቅድስት ብሎ ልመናስ ከዚህ በኋላ እንኳን በእርሷ በሌሎችም የለባቸውም በቀድሞ ልመናዋ የምታስምር ስለሆነ እንዲህ አለ እንጂ ይላል። ቅዱሳን አሁን ስለኛ አይጸልዩምን? ቅዱስ ጴጥሮስ ከማዳሪያየ ከወጣሁ በኋላም ስለናንተ እጸልያለሁ ብሏል። አይቃረንም?

መልስ፦ አይቃረንም። ውዳሴ ማርያም ላይ እንደተገለጸው በሰማይ እየወደቁ እየተነሡ መለመን የለም። በመጻሕፍት ቅዱሳን ይለምናሉ እየተባለ መገለጹ በምድር በሠሩት

መልካም ሥራ እግዚአብሔር በገባላቸው ቃል መሠረት በስማቸው የተማጸነውን ስለሚረዱ ነው። ያሳሰበ እንዲሰማ በስማቸው የተለመነው ይሰማላቸዋል ማለት ነው።

፷፩. አንድ ወንድ የንስሐ አባቱን ልጅ (በሥጋ) ቢወዳትና ቢፈላለጉ መንፈሣዊ ዝምድና ከሚለው ጋር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 እንደተገለጸው ጋብቻን የሚከለክሉ ዝምድናዎች አራት ናቸው። እነዚህም የጋብቻ ዝምድና፣ የክርስትና እናትና አባት ዝምድና (መንፈሳዊ ዝምድና)፤ የአሳዳጊ ዝምድና እና ሥጋዊ ዝምድና ናቸው። አንድ ሰው የንስሓ አባቱን ልጅ ከማግባት የሚከለክለው ሥርዓት ግን የለም። ስለዚህ ማግባት ይችላል።

፷፪. ፍትሐ ነገሥት 47፥1676 ላይ ሰውን የመታ ሰው ቢሞትም ስለእርሱ ፈንታ ይግደሉት ይላል። ፍትሐ ነገሥት 45፥1572 ላይም በሬ ሰው ወግቶ ቢገድል በሬውን ይውገሩት ሥጋውንም አይብሉት ባለበሬውም ይዳን። በሬው ትናንትና ከትናንትናም በፊት የሚዋጋ ቢሆን ባለቤቱም ቢያዳኙበት ባይጠብቀውም በሬው በድንጋይ ይወገር። ባለቤቱንም ደግሞ ይግደሉት ይላል። በሐዲስ ኪዳን ከተጻፈ እንዴት እንዲህ ይላል?

መልስ፦ ይህ ፍትሕ ሥጋዊ ነው። በፍትሕ መንፈሳዊ ሰውን መግደል ፈጽሞ አልተፈቀደም። ሰው አጥፍቶ ከተገኘ ንስሓ ገብቶ ቀኖና ይሰጠዋል። ከጥፋቱ አልመለስም ካለ ደግሞ ተወግዞ ይለያል እንጂ አይገደልም። በፍትሕ ሥጋዊ ግን ነገሥታት ያጠፋውን ያሥሩ ይገርፉ ዘንድ፣ እንደ ሀገሩ ሕግ መገደል የሚገባውን ይገድሉ ዘንድ ተፈቅዶላቸዋል። ይህም ሠለስቱ ምእት ለጊዜው ቆስጠንጢኖስ ይመራበት ዘንድ የሰጡት ሥጋዊ መመሪያ ነው። የሞት ፍርድ የተፈረደበት ወንጀለኛ ቢኖር ቤተክርስቲያን ያ ሰው ከነኃጢአቱ ሞቶ ወደሲኦል እንዳይገባ ንስሓ ገብቶ፣ ቀኖናውን ጨርሶ፣ ሥጋውን ደሙን ተቀብሎ እንዲያርፍ መጠየቅ ትችላለች።

፷፫. በበዓለ ኀምሳ ስግደት እንደማይፈቀድ ያዝዛል። የጸሎት ስግደትንም ጨምሮ ነው? ጸሎት አድረስን መስገድ አይቻልም?

መልስ፦ የጸሎት ስግደት በማንኛውም ቀን የሚሰገድ ነው። እሑድ ቀንም ወደ ቤተክርስቲያን ስንገባ ሦስት ጊዜ ሰግደን እንገባለን። ጸሎት ስንጀምርም ሦስት ጊዜ ሰግደን እንገባለን። የተከለከለው ንስሓ ተቀብለን የምንሰግደው የቀኖና ስግደት ነው።

፷፬. ከትንሣኤ በኋላ በበዓለ ኀምሳ ጊዜ አርብም፣ ረቡዕም በማንኛውም ጊዜ የፍስክ ምግቦች ይበላሉ። ምክንያቱ ምንድን ነው?

መልስ፦ ዘመነ ትንሣኤ (በዓለ ኀምሳ) በመንግሥተ ሰማያት ለምንኖረው ኑሮ ምሳሌ ነው። በመንግሥተ ሰማያት ደግሞ ድካም፣ ኀዘንና የመሳሰሉት ነገሮች የሉም። ፍጹም

ዕረፍት፣ ፍጹም ደስታ አለ እንጂ። ፋሲካ ደግሞ በግ አርዶ ከመብላት ጋር የተያያዘ ነው (ዘፀ.12፥21)። ይህም በሀገራችን የደስታ መግለጫ ሆኖ የኗላውን ፍጹም ዕረፍት እናስብበት ዘንድ ይደረጋል።

**፷፫. እንደየ አካባቢው የተለያየ ባህል ይኖራል። በመሆኑም ባህሉን እንደ ሃይማኖት በመቁጠር የሚከናወን ድርጊት ስለሚኖር መለኪያችን ምን ይሁን?**

መልስ፦ የባህል መለኪያው ሃይማኖት (ኦርቶዶክሳዊ አስተምህሮ) ነው። አንድ ባህል ሃይማኖታዊ አስተምህሮን እስካልተቃወመ ድረስ ሊነቀፍ አይችልም። በሀገራችን ያሉ ባህሎች ብዙዎች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች ጋር የሚመሳሰሉ ደጎች ናቸው። አንዳንድ ባህሎች ግን ከሃይማኖት የሚቃረኑ ሆነው ሲገኙ መቃወም ይገባል።

**፷፬. በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ይህም ለዘላለም ይሆናል እያለ የሚጠቅሳቸው ሐሳቦች በሙሉ እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚሄዱ ናቸውን?**

መልስ፦ ዘለዓለም ሁለት ዓይነት ነው። ብዙ ዘመንን ዘለዓለም ሲል ይገኛል። ለምሳሌ ሰሎሞን ለዘለዓለም ይነግሣል ሲል ብዙ ዘመን ይነግሣል ማለት ነው። እግዚአብሔር ለዘለዓለም ይነግሣል ሲል ደግሞ ፍጻሜ ለሌለው ዘመን ነግሦ ይኖራል ማለት ነው።

**፷፭. በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ታዝዘው የነበሩ ነገር ግን አሁን በሐዲስ ኪዳን ተሽረዋል ወይም አሁን እነዚያን ማድረግ ግዴታ አይደለም የሚባሉቱ ነገሮች ምን ምን ናቸው?**

መልስ፦ በዋናነት ሥርዓተ መሥዋዕቱ ተሽሮ በክርስቶስ መሥዋዕትነት ተተክቷል። ግዝረት በጥምቀት ተተክቷል። አሁን ላይ ግዝረት ግዴታ አይደለም። "መገረዝ ቢሆን አለመገረዝም ቢሆን ከንቱ ነው። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ነው እንጂ" እንዲል (1ኛ ቆሮ.7፥19)። ሥርዓተ ክህነቱ ተሽሯል። የብሉይ ክህነት ከነገደ ሌዊ ለተወለደ ብቻ ይሰጥ ነበረ። አሁን ግን ለሥርዓተ ክህነቱ ብቁ የሆነ ሁሉ ይሾማል። ወዘተርፈ።

**፷፮. እግዚአብሔር የነጻነት አምላክ ነው እንላለን። ነጻነት ራሱ ምንድን ነው ከምርጫ በምን ይለያል? ፍጹም ነጻነትስ አለወይ? እና እንደዚህ ከሆነ ሰው በነጻነቱ ውጤት ለምን ይጠየቃል?**

መልስ፦ ነጻነት ማለት አንድን ነገር የማድረግና ያለማድረግ ሙሉ ሥልጣን መኖር ማለት ነው። ይህ ሲሆን ግን በማድረጉና ባለማድረጉ ምክንያት የሚገኘው ውጤት ኀላፊነትንም ያካተተ ነው። አንድ ሰው የመብላት ነጻነት አለኝ ብሎ አብዝቶ ቢበላና ቁንጣን ቢይዘው ተጠያቂው ራሱ ነው። "ጽጋብ ያመጽእ ግብረ ድንጻዌ፣ ወድንጻዌ ያፈደፍድ ደዌ" እንዳለ ባለቅኔ። የሰው የነጻነቱ ውጤት ባለቤቱ ራሱ ስለሆነ መጥጠየቁ አግባብ ነው። ሰው የፈለገውን የማድረግ ሙሉ ነጻነት አለው። ሁሉንም ለማድረግ የሚያስችል ባሕርይ ግን የለውም። በተፈጥሮው ወሰን ያለበት ነውና።

፳፱. ብሉይ ኪዳን ላይ ስናየው እግዚአብሔር ለሕዝበ እስራኤል ሕዝቤ እያለ ይጠራቸዋል ቢበድሉት እንኳን ነቢይ እያስነሣ ይገሥጻቸዋል ይቅር ይላቸዋል። በአንጻሩ ደግሞ ሌሎች አሕዛብን ስንመለከት ያለ ነቢይ ያለ አስተማሪ ሲቀጡ እናያለን ይሄ ነገር እንዴት ነው የሚታየው?

መልስ፦ እግዚአብሔር ባወቀ ይህንን አድርጓል። ይህንን ማድረጉ ለምን እንደሆነ ሙሉ ነገሩን የሚያውቀው ራሱ እግዚአብሔር ነው። እስራኤላውያን በአምልኮ ከሌሎች የተሻሉ ሆነው በመገኘታቸው ልዩ ሥጋዊ ረድኤትን ይሰጣቸው እንደነበረ ግን አልፎ አልፎ ተገልጿል።

፴. አምስት ዓለማተ ምድር እንዳሉ ሰምቻለሁ። መሬት፣ ገነት፣ ሲኦል፣ ብሔረ ሕያዋን እና ብሔረ ብፁዓን። በብሔረ ብፁዓን የሚኖሩት ሰወች ይዋለዳሉ ይባላል። እነዚህ ሰወች የተወሰዱት ከየትና በመቼ ጊዜ ነው?

መልስ፦ የተወሰዱት ከዚህች ዓለም ከእስራኤል ምድር እንደሆነና በነቢዩ ኤርምያስ ዘመን እንደሄዱ ገድለ ቅዱስ ዞሲማስ ይናገራል (ራእ.16፥12 ትርጓሜ)።

፴፩. ፈያታይ ዘጸጋም (በግራ የተሰቀለው ወንበዴ) ገነት ነው ያለው ወይስ ሲኦል? ነፍሳት ሲወጡ አብሮ ወጥቷል ይሆን?

መልስ፦ ገነት ያለውንና ሲኦል ያለውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው። ፈያታዊ ዘየማን ገነት እንደሚገባ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ነግሮታል (ሉቃ.23፥43)። ስለፈያታዊ ዘጸጋም ግን የተባለ ነገር እስካሁን አላገኘሁም።

፴፪. ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሳትን ሲያወጣ በሲኦል የቀሩ ነፍሳት አሉ ወይስ የሉም? እነ ፈርኦን እና እነ ሄሮድስ የት ናቸው? ገነት ወይስ ሲኦል?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ ሁለት እይታዎች ይነገራሉ። እነዚህ ሰዎች አልወጡም የሚሉ አሉ። መነሻቸው በመቅድመ ወንጌል ወኀደጎሙ ለእኩያን የሚለው ቃል ነው። በብዙዎች ዘንድ የሚታመነው ግን ማንም ሰው አልቀረም ሁሉም ሰው ከሲኦል ወደገነት ተመልሷል የሚለው ነው። ወኀደጎሙ ለእኩያን የሚለውንም በስመ ኀዳሪ ይጼዋዕ ማኅደር በሚለው አግባብ በነፈርያን አድረው ክፉ ያሠሯቸው አጋንንት አልወጡም ለማለት እንጂ ራሳቸው እነፈርያን አልወጡም ማለት አይደለም ብለዋል።

፴፫. ገሃነመ እሳት ያለው በየት ነው በሰማይ ወይስ ከመሬት በታች? በርባሮስ እና ገሃነም የተለያዩ ናቸው?

መልስ፦ በሥነ ፍጥረት ገሃነመ እሳት የሚባል እንዳለ እንጂ በየት በኩል እንዳለ የሚናገር መጽሐፍ አላገኘሁም። አንዳንዶች በሰማይ ውዱድና በመንበረ ስብሐት መካከል የተዘረጋው እሳት ነው የሚል አስተያየት ይሰጣሉ። ያ ገሃነም እንደሆነ የሚገልጽ ግን

ቃል በቃል አላገኘሁም። በርባሮስ ከመሬት በታች ያለ ፍጥረት ነው። ገሃነም የተባለ በርባሮስ ይሆን ወይም አይሆን ግን አላውቀውም።

**፸፬. ክርስትና ያልተነሣ ሕፃን ልጅ ክርስትና ሳይነሳ መስቀል መሳለም ይችላል ወይስ አይችልም? ቢሞትስ ቤተክርስቲያን መቀበር ይችላል?**

መልስ፦ በዚህ ዙሪያም የተሠራ ሥርዓት አላገኘሁም። ስለዚህ አላውቀውም። ርቱዐ ሃይማኖት ከተባለው በመካከለኛው ዘመን ከተጻፈ መጽሐፍ ላይ ከመጠመቁ በፊትም ቢሆን የክርስቲያን ልጅ የሌላ እምነት ካላቸው ልጆች ብልጫ እንዳለው ተጽፏል። ሲሞት ግን በቤተክርስቲያን ዙሪያ ይቀበር ወይም አይቀበር የማውቀው ነገር የለኝም። [ግላዊ አስተያየት፦ ዙሮ ዙሮ ለማስጠመቅ ዝግጅት ላይ እያለን ስለሞተብን ድኅነትን እንዲያገኝ ተስፋ በማድረግ ቤተክርስቲያን ብንቀብረው ችግር የሚያመጣ አይመስለኝም። የቤቴል ሐሰተኛ ነቢይ ከእውነተኛው ነቢይ ጋር በመቀበሩ ሌሎች ሲጠፉ ሳይጠፉ መቅረቱ የዚህን ምሳሌ ያሳየናል። "ዐፅመ ነቢየ ቤቴል ድኅነት ምስለ ዐፅመ ባዕድ፣ እንዘ ነፍሱ ትውዒ በነድ" እንዳለ ባለቅኔ (1ኛ ነገ.13፥1-31፤ 2ኛ ነገ.23፥15-17)]።

**፸፭. ዘመናችንን ዓመተ ምሕረት ብለን መቁጠር የጀመርን ታኅሣሥ 29 በክርስቶስ ልደት ምክንያት ሆኖ እያለ፣ 5500ውን ዘመን ገድፈን ዘመናችንን 1 ብለን የምሕረት ዘመናችንን እንድንቆጥር ያደረገን ልዩና ታላቁ የሆነው ክሥተት የክርስቶስ ልደት ሆኖ እያለ የዘመን መለወጫችን መስከረም 1 መሆኑ ማለትም ዘመናችን የተለወጠው ታኅሣሥ 29 በክርስቶስ ልደት ሆኖ እያለ መስከረም ላይ ያሉ የተፈጥሮ ክሥተቶችን ምክንያት በማድረግ ዘመን ተለወጠ ብሎ ማክበር አግባብ ነው ብለው ያምናሉን? ዘመናችንን በመቀየር መስከረም ላይ ካሉ ክሥተቶች ይልቅ ታኅሣሥ 29 ላይ የሆነው ክስተት አይልቅም?**

መልስ፦ በመሠረቱ የሰው ልጅ ድኅነት የሚጀምረው ከማሕፀን ነው። ይህም ማለት ጌታ ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ልደቱ መገለጫ ነው። ስለዚህ ዓመተ ምሕረት የጀመረው ከጌታ ፅንሰት ጀምሮ ነው። ጥያቄው ከመዳን ክሥተት ጋር ከተያያዘ መሆን የነበረበት ለምን መጋቢት 29 ቀን አልሆነም የሚል ነበር? ስለዘመን መለወጫ እግዚአብሔር የተናገረው የመጀመሪያው ወር ሚያዝያ መሆኑን ነው (ዘፀ.12፥2-3)። ሚያዝያ በእስራኤል ሀገር የክረምት መውጫ ነው። በሀገራችን ደግሞ የክረምት መውጫ መስከረም ነው። በባሕረ ሐሳብ ዕውቀት ደግሞ ሚያዝያ 1 ቀንና መስከረም 1 ቀን የሚውሉበት ቀን ተመሳሳይ ነው። ይህም ማለት ለምሳሌ መስከረም 1 ቅዳሜ ከዋለ ሚያዝያ 1 ቀንም ቅዳሜ ይውላል። በተጨማሪም የኦሪት መጨረሻ የወንጌል መጀመሪያ አካባቢ የነበረው ዮሐንስ ያረፈበት ቀን መስከረም 2 ነው። መስከረም 1 በሀገራችን ዝናሙ፣ ደመናው፣ ጎርፉ ወዘተ የሚቀንስበት፤ ብርሃን፣ ልምላሜ፣ ፍሬ የሚጀምርበት ዘመን ነው። ይህ ከነገረ ክርስቶስ ተመስሎ በምሥጢር አንድ ስለሆነ መስከረምን የዘመን መለወጫ አድርገነዋል። ልደቱን የዘመን መለወጫ ለማድረግ ግን ምንም ዓይነት መሠረት የለውም። ድኅነት የጀመረበት እንዳይሉ ድኅነት የተጀመረ ገና ከፅንስ ጀምሮ

ነው። ልደቱ የተከበረ ስለሆነ በዚያ እንጀምር እንዳይባል እንደልደት የከበሩ ዕርገት፣ ጰራቅሊጦስና የመሳሰሉ በዓላት ስላሉ በእነርሱም ለምን አልሆነም ቢባሉ መልስ አይገኝም።

፸፯. አንዳንድ ሰዎች ክህነት አይፈርስም። ሲጀመር ሥልጣነ ክህነት የሚፈርስ አይደለም ይላሉ። ይህ እንዴት ይታያል? እንዲያውም ብዙ መምህራን አንድ ካህን/ዲያቆን ድንገት ቢሳሳት ንስሓ ገብቶ ወደ ክብሩ ይመለሳል ይላል ፍትሐ ነገሥት ይላሉ። ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ክህነት የልዩ አገልግሎት ጸጋ ነው። ሰው ደግሞ ጸጋ የሰጠውን አካል ሕግና ሥርዓት ካላከበረ ጸጋው ሊወሰድበት ይችላል። ስለዚህ ክህነት የተቀበለ ሰው ክህነቱ የሚጠይቀውን ሥርዓት ካልፈጸመ ክህነቱ ይሻራል። ፈረሰ መባሉኮ ተሻረ ማለት ነው። እንደሚሻር ደግሞ ፍትሐ ነገሥት ከአንቀጽ 4 እስከ አንቀጽ 9 ከነሚሻርበት ምክንያት ተገልጿል። "አንድ ካህን/ዲያቆን ድንገት ቢሳሳት ንስሓ ገብቶ ወደ ክብሩ ይመለሳል ይላል ፍትሐ ነገሥት ይላሉ" ስለተባለው ጉዳይ በእርግጥ ፍትሐ ነገሥት ላይ ከፍትሕ ሥጋዊ ይህንን የመሰለ አነጋገር ይገኛል። ይህ የተደረገበት ዘመንም ሊኖር ይችላል። ከዚሁ ከፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ላይም ኤጲስ ቆጶስ ያገባ ይሁን ብሎ የሐዋርያትን ትምህርት መሠረት አድርጎ ገልጿል። አሁን ባለው ኦርቶዶክሳዊ ትውፊት ግን ጳጳስም ያላገባ ሆኖ፣ ዲያቆንም ቢሳሳት ዲቁናው እንደተሻረ ሆኖ እንዲኖር ሆኗል። እንዲህ ዓይነት ጉዳዮች እንደየዘመኑ ሁኔታ ሊቀነሱ የሚችሉ ስለሆኑ ወጥ በሆነ መልኩ እንዲህ ብቻ ነው ብሎ ለመናገር አያስደፍርም። የሆነ ሆኖ ከዘመናችን የደረሰውን በዘመናችን ያለውን ትውፊት ይዘን መቀጠል ይገባናል።

፸፰. ንስሐ ድንግል ያልሆነችውን ወደ ድንግልና ትመልሳለች ተብሎ ተጽፏል። ስለዚህ አንድ ካህን ቢሳሳት እንዴት በንስሓ ወደ ክብሩ አይመለስም?

መልስ፦ ንስሓ ድንግል ያልሆነውን ወደ ድንግልና ትመልሳለች የሚለው ስለነፍስ ድንግልና የተነገረ ነው እንጂ ስለሥጋ ድንግልና የተነገረ አይደለም። ነፍስ ኃጢአት ስትሠራ ድንግልናዋን አጣች ትባላለች። ንስሓ ስትገባ ደግሞ ድንግልናዋ ተመለሰ ይባላል። አንድ ካህን ከሌላ ሴት ቢደርስ ክህነቱ ይፈርሳል። ንስሓ ገብቶ ኃጢአቱ ይቅር ስለሚባል ነፍሳዊ ክብሩን መመለስ ይችላል። ክህነታዊ ክብሩ ግን በንስሓ አይመለስም።

፸፱. ጸሎተ ዘወትር፣ ውዳሴ ማርያም፣ መዝሙረ ዳዊትን እና ሌሎች ጸሎታትን እና መልክአ መልኮችን የሚደግም ሰው እነዚህን ጸሎቶች ለማድረስ ቅደም ተከተሉ እንዴት ነው? ሌሎች ከጸሎት ሥርዓት ጋር ተያያዥ የሆኑ ሥርዓቶችን በሚገባ ቢያብራሩልኝ እላለሁ።

መልስ፦ ዝርዝር ጉዳዩ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14 ላይ ስለተገለጸ ከዚህ ብዙ የምለው የለኝም። የጸሎት ቅደም ተከተል ሰው የፈለገውን አስቀድሞ የፈለገውን ማስከተል ይችላል። ፍሬ ነገሩ ጸሎት ማድረጉ ላይ እንጂ ቅደም ተከተሉ ላይ አይደለም። የጸሎት

መደምደሚያው ግን አቡነ ዘበሰማያት (አባታችን ሆይ) የሚለው ጸሎት ነው። በፍትሐ ነገሥት የተገለጹ በየቀኑ ልንጸልያቸው የሚገቡ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎችም አሉ። ከሰኞ እስከ እሑድ ባሉት ዕለታት ከጸሎተ ነቢያት ሊጸለዩ የሚገቡም ተገልጸዋል። በትውፊት ደግሞ ሰኞ ከመዝሙር 1 እስከ መዝሙር 30፤ ማክሰኞ ከመዝሙር 31 እስከ መዝሙር 60.... እየተደረገም ይጸለያል።

**፸፱. ቤተክርስቲያን በምጽአት ጊዜ ምድር እንደ ሰሌን ስትጠቀለል ቅድስት ቤተክርስቲያንም አብራ ትጠቀለላለች?**

መልስ፦ በሕንፃ ቤተክርስቲያን ዙሪያ ሁለት እይታዎች አሉ። አንደኛው እግዚአብሔር ባወቀ ይሠውራታል የሚል ሲሆን። ሁለተኛውና አብዛኛው ሰው የሚቀበለው ደግሞ ሕንፃ ቤተክርስቲያን እኛ እስካለን ድረስ ለእኛ መገልገያ ሆኖ ይኖራል። በምጽአት ሰማይና ምድር ሲያልፍ ሕንፃ ቤተክርስቲያንም ያልፋል የሚል ነው። ሁለቱም እይታዎች ስለሆኑ የሚያጣሉ አይደሉም። ያን ጊዜ ስንደርስ የምናውቀው ይሆናል።

**፹. ከቁርባን በኋላ የቆረቡት ከቤተ ክርስቲያን ግቢ ከመውጣታቸው በፊት የግድ ምግብ መቅመስ አለባቸው ወይ?**

መልስ፦ አስገዳጅ ነገር የለም። በትውፊት ከቆረቡ በኋላ እህል ሳይቀምሱ ከማንም ጋር አይነጋገሩ ይባላል። የሰንበት ቂጣ ካለ መቅመስ ነው። ከሌለ ደግሞ ከቤት ሄዶ የተገኘውን መቅመስ ነው። የግድ ቤተክርስቲያን ብቻ ምግብ መቅመስ አለባቸው የሚል አስገዳጅ ሕግ የለም።

**፹፩. የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከሌሎች ሀገራት ከግሪጎርያኑ ጋር የ7 ወይም የ8 ዓመት ልዩነት እንዴት ተፈጠረ?**

መልስ፦ ቀድሞ የነበረው የዘመን አቆጣጠር የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ነው። የግሪጎርያኑ አቆጣጠር በኋላ ዘመን (በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣ የካቶሊክ መነኩሴ የክርስቶስን ልደት በገመተበት ቀን መሠረትነት) የተሠራ ነው። 7 ወይም 8 ዓመት የጨመሩት ሊቃውንትም የቀድሞው አቆጣጠር ስሕተት አለበት በማለት ነው። ይህ ደግሞ በበቂ ጥናት ያልተደገፈ ስለሆነ አንቀበለውም። ይህንን እሳቤ መሠረት አድርጎ የካቶሊክ ጳጳስ የነበረ ጎርጎርዮስ የተባለ ሰው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግሪጎርያን ካላንደርን መሠረተ። ነገር ግን ከ0ሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት የነበረው ቅዱስ ድሜጥሮስ ትክክለኛውን የዘመን አቆጣጠር ቀድሞ ተገልጾለት እንደጻፈ ይታወቃል።

**፹፪. የጳውሎስ መልእክታት አንድምታ ትርጓሜ ላይ እንዲህ የሚል ቃል አለ «በክርስቶስ አሥምሮት እግዚአብሔርን ታሠምሩት ዘንድ ክርስቶስን ማላጅ አድርገን እንማልዳችኃለን»**

ይላል። ማላጅ ስለሚለው ቃል ያብራሩልኝ። ከዚህ አንጻር መጽሐፉ ማላጅ እንዳለው ኢየሱስን ማላጅ ብለን መጥራት ይቻላል?

መልስ፦ እውነት ነው ይህ ቃል 2ኛ ቆሮ.5፥20 ትርጓሜ ላይ ይገኛል። ክርስቶስን ማላጅ አድርገን ማለቱ የቅዱሳን ምልጃ ነፍሳዊ ጥቅምን የሚያሰጥ የሆነው ክርስቶስ በመስቀል ላይ ራሱ አስታራቂ (ማላጅ)፣ ራሱ ታራቂ፣ ራሱ መታረቂያ (መሥዋዕት) ሆኖ በሠራው ሥራ ምክንያት ነው። ይህንን ለመግለጽ ክርስቶስ አስታራቂ ሆኖ ከራሱ ጋር እንዳዳነን ሁሉ ሐዋርያትም በተሰጣቸው ጸጋ እየማለዱ ከእርሱ ጋር እንደሚያስታርቁን ለመግለጽ የተነገረ ነው። ክርስቶስን አስታራቂ (ማላጅ) እንለዋለን። ነገር ግን እንደ ፕሮቴስታንቶች ከስቅለት በኋላም እየማለደ ይኖራል አንልም። በመስቀል ማለደ መባሉም ለካሣነት ለቤዛነት ነው። ያስታረቀንም ከራሱ ጋር ነው።

፹፫. ድርሳነ ሰንበት 17፥1-2 ላይ ከዚህ በኋላ በገሃነም ውስጥ የነበሩ ክርስቲያን ነን እያሉ የክርስቲያን ሥራ የማይሠሩ ኃጥአንን ከመድኃኒታችን ሥልጣን ጸሎትን ይጸልይላቸው ዘንድ መላእክት ያቀርቧቸዋል አለ። መድኃኒታችን ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያስታርቃቸው ዘንድ ያቀርቧቸዋል። መድኃኒታችን ጸሎትን ከጸለየላቸው በኋላ መላእክት ወደ አማረች ወደ ተወደደች ምድር ወደ መንግሥተ ሰማያት ይወስዷቸዋል ይላል። ክርስቶስ አሁንም ይጸልያልን?

መልስ፦ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለቤዛነት፣ ለአርአያነት ከጸለየ በኋላ የቤዛነት ሥራውን ጨርሶ ተፈጸመ ካለ በኋላ መጸለይ፣ መማለድ የለበትም። ከዚህም ይጸልይላቸዋል እያለ መግለጹ የጸለየ ዋጋ እንደሚያሰጥ በዚህ ምድር አንድ ጊዜ በዕለተ ዓርብ በሠራው ቤዛነት ያድናቸዋል ማለት ነው። "ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። ቅዱስና ያለተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባልና። እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም። ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና" እንዲል (ዕብ.7፥25-27)። በገሃነም ከነበሩ ክርስቲያኖች ሰንበትን ያከብሩ የነበሩ ካሉ ይህ የራሱ ዋጋ ስላለው ከምጽአት በኋላ ገነት እንደሚገቡ በቅዳሴ ትርጓሜም ተገልጿል።

፹፬. በጎንደር ሐይከል የምትባል አካባቢ በኖኅ ሚስት እንደምትጠራ ኖኅ ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ ይሄን እንዴት ያዩታል?

መልስ፦ አሁን ላይ ሐይከል ተብላ የምትጠራ ሀገር አለች ተብሎ ቀድሞ የኖኅ ሀገር ጎንደር ነበር የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የሌለው፣ በአፈ ታሪክ ላይ የተመሠረተ አነጋገር ነው። በዚህ አካሄዳችን ጎጃም ሞጣ አካባቢ ቀራንዮ የሚባለው ቦታም ጌታ

የተሰቀለበት ነው፣ ደቡብ ጎንደር ታች ጋይንት ቤተልሔም ጌታ የተወለደበት ነው እያልን የራሳችንን ፍላጎትና መሰለኝ እውነት አስመስለን ማውራታችን አይቀርም። ስለዚህ የቀረበው ማስረጃ ኖኅ ጎንደር እንደኖረ ሊገልጽልን የማይችል፣ በጥንታዊ የቤተክርስቲያን መጻሕፍትም የሌለ የቅርብ ዘመን ልብወለዳዊ ድርሰት ስለሆነ ልክ አይደለም። ይህንን የመሰለ አዳም ጎጃሜ ነው የሚልም አለ። ሁሉም ልብ ወለዶች ናቸው።

፹፭. ሙሴ በግ ይጠብቅበት የነበረው የበግ ምድር በጌ ምድር እንደተባለ የሚነገሩትን እንዴት ያዩታል?

መልስ፦ ሙሴ በግ ይጠብቅበት የነበረው ቦታ ምድያም ነው እንጂ በጌምድር አይደለም። የስም ለውጥ ተደርጎ ነው ብለን እንዳናመልጥ ምድያም ወደ በጌምድር እንደተለወጠ የሚያሳይ ምንም ጥንታዊ ጽሑፍ ወይም ቅዱሳት መጻሕፍታዊ መነሻ የለውም። አንዳንዱ ኮሬብ ከዘመን ብዛት የተነሣ ኮረም ተብሎ ነው እያለ የራሱን ስሜት በውሸት ለማሳመን የማጠጋጋት ሥራ የሚሠራ ሁሉ አለ። ይህ የእኛ ጉዳይ አይደለም። ማስረጃ ሊያቀርቡበት ያልቻሉበትን ጉዳይ ታሪክ ብለን መቀበል የለብንም።

፹፮. ከበአታቸው ተለይተው የወጡ መነኮሳት በከተማ ውስጥ ያሉ የአጋንንት የግብር ልጆች ናቸው እላለሁ። ምክንያቱም በሕግ የሚኖረውን ካህን፣ ሊቃውንት፣ በዕውቀት የሚበልጧቸውን፣ በማሳደድ የተጠመዱ ግብረ እግዚአብሔርን የሚፈጽሙትን የማይወዱ፣ ከ20-40 ሴቶችን እንደ እንስሳ የሚጋልቡ በአፍቅሮ ንዋይ የታወሩ ቂመኛ እና ትዕቢተኛ ሃይማኖት የሌላቸው፣ እግዚአብሔርን የማይፈሩ፣ ሥጋዉን ደሙን የሚያቃልሉ ስለሆኑ ይሄን እላለሁ የግል ምልከታዬ ነው?

መልስ፦ ክቡር ጠያቂ አዎ ይህ የግል ምልከታዎት ነው። ምንም እንኳ ከላይ የጠቀሷቸውን ሁሉ ሊያደርጉ የሚችሉ ክፉ መነኰሳት ሊኖሩ ቢችሉም ከቀድሞ ጀምሮ እስከ አሁን ያሉ ወደፊትም የሚነሡ ደጋግ መነኰሳት አሉ። ስለዚህ ደጋጎቹንም በጅምላ ከምንጨፈጭፋቸው ከላይ የጠቀሷቸውን ክፉ ሥራዎች የሠራ መነኵሴ ካዩ ማስረጃዎትን አጠናክረው ለሚመለከተው አካል አመልክተው ከቤተክርስቲያን እንዲታገድ ማድረግ ቢቻል መልካም ነው። አሁን ላይ በጅምላ መናገር ደጋጎቹን የዘነጋ አካሄድ ስለሆነ ቢታረም መልካም ነው።

፹፯. የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ድጓ ብቻ ነው የሚሉ ሊቃውንት እየበዙ ነው። ሌሎች ድርሰቶች የአባ ጊዮርጊስ እና የሌሎች ሊቃውንት ናቸው የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ ምክንያታቸው እርሱ ጽፏቸዋል የተባሉ መጻሕፍት በዚያን ዘመን በዮዲት ጉዲት ስለጠፉ ወሎ እና ከዚያ ወደ ቤተልሔም በባሕታዊ አማካኝነት ድጓ ነው የተገኘው ይላሉ። እርስዎ ምን ይላሉ?

መልስ፦ እኔ የምለውና በትውፊት የተቀበልኩት የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ድጓ ብቻ ሳይሆን ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ እና መዋሥዕትም ጭምር ናቸው የሚል ነው:: ዮዲት ጉዲት አጥፍተዋለች የሚለው ማስረጃ የሌለው አንድን ታሪክ ለራስ በሚመች ሁኔታ ጠቅሶ ያልተረጋገጠ ድምዳሜ መስጠት ሆኖ አግኝቼዋለሁ:: እንዲህ ዓይነት ታሪካዊ ጉዳዮችን ይበልጥ የታሪክ ባለሙያዎች ቢጠየቁ የተሻለ ይሆናል:: የእኔ ሐሳብ ግን ይህ ነው:: ድጓ በተረፈት መንገድ ሌሎችም ድርሰቶች ተርፈው ለእኛ ደርሰዋል::

**፹፰. ግእዝ ግማሹ አግዓዝያን የሚባሉ ይዘውት እንደ ገቡ ሌሎች የአዳም ቋንቋ እንዳንዶች የመላእክት ቋንቋ ነው ይላሉ የጠራ ምላሽ እስካሁን የለም?**

መልስ፦ አዎ የለም:: ይህ ከሃይማኖት ጋር የማይያያዝ ታሪካዊ ጉዳይ ነው:: ታሪክ ደግሞ እንደሁኔታውና በየጊዜው በሚገኙ ማስረጃዎች ሊከለስ፣ ሊታደስ፣ ሊለወጥ ይችላል:: ስለዚህ ሁሉም የሚያቀርበው መረጃ በልበ ሙሉነት የሚያምኑት አይደለም:: ስለዚህ የሁሉንም አስተያየት አክብረን ማስረጃዎች ግን እኛን ለማሳመን በቂ ስላልሆኑ ለተጨማሪ ጥናት ጋብዘናል::

**፹፱. በእግዚአብሔር አቆጣጠር 1ቀን 1ሺ ዓመት ነው ስለዚህ ፍጥረታት የተፈጠሩት በ6ሺህ ዓመታት ሊሆን ይችል ይሆን?**

መልስ፦ በእግዚአብሔር አንድ የሚባለው ቀን በእኛ ብዙ መሆኑን ለመግለጽ እንደ አንድ ሺ ተብሏል:: አንድ ሺ የሚለው ቃል በቃል የተነገረ ሳይሆን ብዙ ለማለት ነው:: ንጉሥ ሆይ ሺ ዓመት ይንገሡ እንደሚለው አነጋገር ነው:: ፍጥረታት የተፈጠሩበት ቀን እንዳሁኑ ያለ በእኛ አቆጣጠር ነው:: የባሕረ ሐሳብ ትምህርታችን የሚገልጸው ይህንን ነው:: እንዲሁም ዘፀ.20 ላይ ሰንበትን አክብሩ ጌታ አርፎበታልና የሚለው አነጋገር አቆጣጠሩ እኛ በምንቆጥርበት መንገድ እንደተቆጠረ ያሳውቀናል:: 1000 ዓመት ነው ከተባለ ስድስት ሺ ዓመታት ሠርታችሁ በሰባተኛው ሺህ ዓመት እረፉ ያሰኛልና:: ይህ ደግሞ እንዳልሆነ በአከባበራችን ይታወቃል::

**፺. ጌታችን በወንጌል በተለያየ ጊዜ እያወቀ ጥያቄ ሲጠይቅ በተለይ ሐዋርያቱን እናስተውላለን (ለምሳሌ:- ኒቆዲሞስን ወዴት አኖራችሁት? እንዳለው):: በትርጓሜም በተደጋጋሚ አላዋቂ ሥጋን እንደ ተዋሐደ የሚል ትርጓሜ እናገኛለን:: የእኔ ጥያቄ ጌታችን ሁሉን አዋቂ ነውና በተዋሐደው ሥጋ ቢሆንም በመዋዕለ ስብከቱ በሥጋው እንደኛ የተከፈለ ዕውቀትን (አለማወቅን) ገንዘብ አድርጓል ማለት ነው?**

መልስ፦ ቃል ከሥጋ ጋር በመዋሐዱ ሥጋ ምን አገኘ ከተባለ ዕሩቅ ብእሲነት፣ አላዋቂነት፣ በግድ መራብ መጠማትና መከራ መቀበል ቀርቶለታል:: ከተዋሕዶ በኋላ በእውነት ተርቧል፣ በእውነት ተጠምቷል፣ በእውነት መከራን ተቀብሏል:: ይህ ግን የፈቃድ መራብ፣ የፈቃድ መጠማት፣ የፈቃድ መከራን መቀበል ነው እንጂ የግዴታ

አይደለም። አልዓዛርን የት ቀበራችሁት፤ በበለስ ፍሬ አላገኘባትም፤ ያችን ዕለት ከአብ በስተቀር የሚያውቃት የለም የሚሉት ቃላትና የመሳሰሉት በልብ ታስበው አለመነገራቸውን ለመግለጽ አለማወቅ ተብለዋል። ክርስቶስ የተከፈለ ዕውቀትን ገንዘብ አደረገ ተብሎ አይነገርለትም። እያወቀ አለመናገሩ አለማወቅ ተብሎ ቢገለጽም ነገር ግን አለመናገሩ ለሰዎች ጥቅም ስለነበረ እኛ ዕውቀት የምንለውን አያውቅም ለማለት አይደለም።

**፺፭. ራእ.12፥2 ላይ "እርሷም ፀንሳ ነበር ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጨንቃ ጮኸች" ሲል እናገኛለን። በትርጓሜው ይህች ሴት እመቤታችን ከሆነች እርሷ ደግሞ ምጥ እና ጭንቅ የለባትም ጌታን ስትወልድ እና ይህ እንዴት ነው የሚተረጎመው?**

መልስ፦ ይህ ራእይ ለድንግል ማርያም ሲነገር ምጥ=መከራ በሚለው ይተረጎማል። ለምሳሌ "ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና። በልዩ ልዩ ስፍራ የምድር መናወጥ ይሆናል፤ ራብ ይሆናል፤ እነዚህ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው" ሲል የምጥ ጣር ያለው የመከራ ለማለት ነው (ማር.13፥8)። እንጂ ጌታን ስትወልድ በሕመም፣ በምጥ እንደወለደችው አያመለክትም። ጌታን ከወለደች በኋላ ወደ ግብጽ በመሰደድ ልዩ ልዩ መከራዎችን ተቀብላለችና እነዚህን ለመግለጽ ምጥ ተብለዋል።

**፺፮. ቅዱስ ጳውሎስ ከ120ው ቤተሰብ ውስጥ ነው? አንዳንድ መጻሕፍት 120ውን ቤተሰብ ሲዘረዝሩ እርሱን ስለሚያካትቱ ነው።**

መልስ፦ ቅዱስ ጳውሎስ ጌታ ከመረጣቸው ከ120ው ቤተሰቦች ውስጥ አይደለም። ከሌላ መጻሕፍት ከ120ው ቤተሰብ አንዱ ጳውሎስ ነው የሚል ካለ ሌላ ጳውሎስ ነው ሊሆን የሚችለው እንጂ 14 መልእክታትን የጻፈው ጳውሎስ አይደለም። የስም መመሳሰል ግን ሊኖር ስለሚችል ጥናት የሚጠይቅ ነው።

**፺፯. ዕለቱኑ የቆረበ ሰው ካልቆረቡት ሰዎች ጋር ይበላል?**

መልስ፦ አዎ መቍረብ ከሌሎች ሰዎች ጋር አንድ ላይ መብላትን አይከለክልም።

**፺፰. ቋንቋውን ሳይረዱ በግእዝ ጸሎት ይደረጋል ወይ?**

መልስ፦ አይደረግም። ሰው የሚለውን ሳያውቅ ለምን ይናገራል። ስለዚህ የሚጸልይ ሰው ትርጉሙን በሚያውቀው ቋንቋ መጸለይ አለበት። በማያውቁት ቋንቋ መጸለይ የሚናገሩትን ሳያውቁ መነጋገር ስለሆነ መሆን የለበትም።

**፺፱. እግዚአብሔር አስቀድሞ ካወቀ፣ ለምን ክፉ ነገር እንዳይከሠት አያቆመውም (አያግደውም)?**

መልስ፦ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቃል አልን እንጂ የሰዎችን ነጻነት ይጋፋል አላልንም። ሰዎች ራሳቸው ወደው ክፋትም ከመረጡ የራሳቸው ምርጫ ስለሆነ አያስቆማቸውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር አዋቂ አምላክ ብቻ ሳይሆን የነጻነት አምላክም ነውና።

፺፮. የበዓላት አገባብና አወጣጥ ለምገባና ለባልና ሚስት ግንኙነት ልዩነትና አንድነት ቢያብራሩልኝ። ለምሳሌ ረቡዕ ሊገባ ማክሰኞ ማታ እስከ 4፡00 ሰዓት ጥሉላት እንበላለን። ግንኙነትስ ይፈቀዳል?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ በግልጽ የተጻፈ ነገር አላገኘሁም። በመምህራን ዘንድ ግን ሁለት እይታዎች ይነገራሉ። አንደኛው የጾሙ ቀኖና ከሌሊት ከ6፡00 ጀምሮ ወደ ቀጣዩ ቀን ይቆጠራል የሚል ነው። ይኸውም ለምሳሌ ቀዳም ሥዑር ጾም ሆኖ ሳለ ሌሊት ከ6፡00 ሰዓት ወደ እሑድ (ወደ ትንሣኤ ተቆጥሮ) የፍስክ ምግብ እንደሚበላ ሁሉ ቀጣዩ ቀን የጾም ከሆነ እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት የዋልንበት ቀን የፍስክ ይሆናል ቀጣዩ ቀን የፍስክ ከሆነ እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት የዋልንበት ቀን ጾም ይሆናል የሚል ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቀጣዩ ቀን ጾም ከሆነ እስከ ምሽቱ 3፡00 ሰዓት በልቶ ከዚያ በማግሥቱ እስከ ዘጠኝ ሰዓት መጾም ነው የሚል ነው። ወጥ የሆነ ሥርዓት ተጽፎ ስላላገኘሁ ለጊዜው የሁለቱንም መምህራን አስተያየት ተቀብለን በአንዱ መመራት ነው። በግንኙነት ዙሪያ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ላይ እንደተገለጸው ቀጣዩ ቀን ጾም ከሆነ እስከ ምሽት 3፡00 ብቻ እንደሚፈቀድ በሐተታ በትርጓሜ ተገልጿል።

፺፯. ዲያቆናት ሲያገቡ ዲያቆኑ የካህኑን፣ ሙሽሪት ደግሞ የዲያቆናትን ልብሰ ተክህኖ መልበሳቸው ተገቢ ነው ወይ?

መልስ፦ አይደለም። ሲጀምር የካህናትን ልብስ ክህነት የሌለው ሰው እንኳንስ መልበስ መንካት አይገባውም (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 8)። ስለዚህ ምንም እንኳ ወደ ገጠር አካባቢ የተክሊል ልብስ በማጣት (በመቸገር) የቄሱን ለዲያቆኑ፣ የዲያቆኑን ለሴቱ አልብሰው ሥርዓተ ተክሊል ቢፈጽሙም ነገር ግን ስሕተት መሆኑን ገልጸን የተክሊል ልብስ ገዝተን መስጠት ይገባናል።

፺፰. በውጭ ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ማረድ የሚታሰብ አይደለም። ሆኖም ማን እንዳረደው የማይታወቀውን እንጠቀማለን። እናም በአጋጣሚ የተገዛው ሥጋ እቤት ከመጣ በኋላ ሃላል የሚል ምልክት ተገኘበት። እናስ ሥጋው መጣል አለበት ወይስ የለበትም?

መልስ፦ ቀኖና ከከለከላቸው ምግቦች ውጭ ያለውን ምግብ ሳንጠራጠር ባርከን ብንበላው በእግዚአብሔር ስም ስለሚቀደስ ምንም የሚያመጣው ችግር የለም (1ኛ ጢሞ.4፥3-5)። ስለዚህ ይጎዳናል ብላችሁ የምትጠራጠሩ ከሆነ እየተጠራጠሩ መብላት ስለማይገባ መጣል ነው። በስመ እግዚአብሔር ይቀደሳል ብላችሁ አቡነ ዘበሰማያትን ጸልያችሁ

የምትበሉት ከሆነ ደግሞ አለመጣል ነው። "ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን አለ። ደካማው ግን አትክልት ይበላል። የሚበላ የማይበላውን አይናቀው የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ። እግዚአብሔር ተቀብሎታልና" እንዲል (ሮሜ 14፥2-3)።

**፺፱. አረጋዊ መንፈሳዊ ላይ "የወልድ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ በሰው ያደረ እንደ ሆነ እንደ ወልደ እግዚአብሔር ይሆናል። አንድም ከመን ትቶ ወልደ እግዚአብሔር ይሆናልና" ይላል። ከዚህ በፊት ሲያብራሩት እንደ እግዚአብሔር ይሆናል የሚለውን ብቻ ለይተው አብራርተውታል። ግን ከዚያ ከጥሎ እንደን ትቶ ወልደ እግዚአብሔር ይሆናል ይላል። ትርጉሙ ምንድን ነው? ይሄን ቃል ይዘው ሰው አምላክ ይሆናል የሚሉ አሉ እርስዎ የተረጎሙትን ስንናገር ትርጉሙ አንድ ቢሆን "ከመን ትቶ" ብሎ አይጽፍም ነበር ይሉናል። እውን ሰው አምላክ ይሆናል? ካልሆነ ለምን "ከመን ትቶ" ተብሎ ተጻፈ?**

መልስ፦ ሁለቱም ሐሳቡ ተመሳሳይ ነው። እንደ ወልደ እግዚአብሔር ይሆናል ማለት ወልደ እግዚአብሔር በባሕርዩ የአብ ልጅ እንደሆነ ሰው ደግሞ በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል ማለት ነው። "ከመ"ን ስንተወውና ወልደ እግዚአብሔር ይሆናል ማለትም ያው ነው። ወልደ እግዚአብሔር ማለት የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ነው። ምእመናን ደግሞ ተጠምቀን ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች እንባላለን። ሰውም የጸጋ አምላክ ይሆናል።

**፻. እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ሲል ተሰቅሏል። ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ አይሁዳውያን መስቀላቸው እንዴት እንደ ጥፋት ተቆጠረ?**

መልስ፦ እንደሚሰቅሉት የተነገረው ትንቢት ነጻ ፈቃዳቸውን ተጠቅመው እንደሚሰቅሉት ስለታወቀ እንጂ ትንቢቱ ስለተነገረ አይደለም የሰቀሉት። ትንቢት ውጤት እንጂ መንሥኤ አይደለም። የሰቀሉት የእግዚአብሔርን ሕግ ጥሰው ስለሆነ አጥፍተዋል። እርሱ ደግሞ ቸር ስለሆነ በመስቀሉ ለእኛ ሕይወትን ሰጠን። ነቢያት ሰዎች ነጻ ፈቃዳቸውን ተጠቅመው የሚያደርጉትን ድርጊት በመንፈስ ቅዱስ መነጽርነት አስቀድመው አወቁ እንጂ የነቢያት ዕውቀት ሰዎች ያንን ነገር እንዲያደርጉ አላስገደደም። ትንቢት የሰዎች ድርጊት ውጤት እንጂ ምክንያት አይደለም።

**፻፩. ቡዳ ዛር ስለሚባል ነገር የሆነ ነገር ቢሉን። ቡዳ የሚባል የሰው ዘርስ አለ ወይ?**

መልስ፦ እኩያን መናፍስት በየቋንቋው ልዩ ልዩ ስያሜዎች ይኖራቸዋል። ጥቅል ስማቸው ግን ያው ሰይጣናት ናቸው። ሰይጣናት ሌላ፣ የሰው ዘር ሌላ ነው። ስለሆነም ቡዳ የሚባል የሰው ዘር የለም። ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረ ክቡር ፍጥረት ነው (ዘፍ.1፥26-27)። ከተጠመቀ በኋላ ደግሞ ሁሉም ክርስቲያን የክርስቶስ ነው። "አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም

ሴትም የለም። ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" እንዲል (ገላ.3፥28)። ሰይጣናት ግን ሰዎችን መሣሪያ አድርገው ክፉ ሥራዎችን ሊያሠሯቸው ይችላሉ። በመጽሐፈ መነኰሳት በአረጋዊ መንፈሳዊ እንደተገለጸው ሰው መንፈስ ዝሙትን ተቀብሎ ዘማዊ፣ መንፈስ ጽርፈትን ተቀብሎ ተሳዳቢ፣ መንፈስ ቍጥዓን ተቀብሎ ቁጡ ተጠራጣሪ ሊሆን ይችላል። ይህንን በመሰለ መልኩ አጋንንት በሰዎች አድረው ያደሩበት ሰው ሌሎች ሰዎችን እንዲጎዳ ሊያደርጋቸው ይችላል። ለምሳሌ በላኤ ሰብእ አጋንንት አድሮበት 78 ነፍሳትን አጥፍቷል። ነገር ግን በግብር እስካልመሰለ ድረስ ከአባት ወይም ከእናት ወደ ልጅ በዘር የሚተላለፍ መንፈስ የለም። ይህ መንፈስ ያለባቸው ሰዎች እንኳ ቢኖሩ ንስሓ ገብተው ሥጋውን ደሙን በመቀበል ማራቅ ይችላሉ።

፲፪. አንድ ክህነቱን በጣም የሚያከብር እና በምንም መንገድ ቢሆን ክህነቱን ማጣት የማይፈልግ ወንድ ነበር። ከዕለታት በአንዱ ቀን በአገልግሎቱ እና በሥርዓቱ የተማረከች አንዲት ሴት አፍቅራው የፍቅር ጥያቄን አቀረበችለት። እርሱም ዲያቆን መሆኑን ነግሯት የሚያገባት ሴት ምን ዓይነት ሴት መሆን እንዳለባት (እምነታቸው አንድ የሆነ፣ ድንግል የሆነች፣ የምትቆርብ፣ መንፈሳዊ እውቀት ያላት ወዘተ) መሆን እንዳለባት አስረድቷት እርሷም አንተ የምትፈልገው ሁሉ አለኝ ብላው ግንኙነታቸውን ቀጠሉ (መጠናናት ጀመሩ)። ነገር ግን እርሷ በንግግራቸው ሁሉ እርሱን ላለማጣት ብላ አንድ ነገር ዋሽታው ነበር (ድንግል አልነበረችም)። እናም ፍቅራቸው አድጎ ሽማግሌ ተላከ። እርሷም ንስሓ እገባለሁ ብላ ዋሽታ ተክሊል አደረገች እና ተጋቡ። በቀጣይ ጊዜያት የጫጉላ ጊዜያቸውን እያሳለፉ ግንኙነት በሚፈጽሙበት ጊዜ ሴት ልጅ ድንግልናዋን ስታጣ የምታሳየውን ምልክት እርሷ ላይ አጣው (የደም፣ የህመም ምልክት አጣ)። እናም ሲጨንቀው ለመጠየቅ ወሰነ እና አወራት ከዚያም ይህች ሴት በጣም ስለወደደችው እርሱን ላለማጣት ብላ ዋሽታው ተክሊል እንዳደረገች ነገር ግን ድንግል እንዳልሆነች ነገረችው። ቀኖና ለዚህች ሴት ተሰጥቷት ሕይወታቸውን ይቀጥላሉ ወይስ ምንድን ነው ሥርዓቱ? የዚህስ ዲያቆን ቀጣይ ሕይወቱ እንዴት ነው የሚሆነው? ቤተክርስቲያን ፍትሐዊ ናትና እርሱስ ባላጠፋው ጥፋት ይቀጣል? ምክንያቱም ድንግልና ቀድሞ ታይቶ የሚገባበት ጉዳይ አይደለምና። እርሱ ክህነቱን አክብሮ እያገለገለ ነበርና የእርሱስ ቀጣይ ሁኔታ ምንድን ነው የሚሆነው?

መልስ፦ ዲያቆን ማግባት ያለበት ድንግል የሆነችን ሴት ነው (ዘሌ.21፥13)። ይህም በትውፊትና በአንዳንድ መጻሕፍት ተገልጿል። ለምሳሌ በመጽሐፈ ሐዊ "ይኩኑ እለይሠየሙ ዲያቆናት (ዲቁና) ደናግለ አው ዘአውሰቡ ብእሲተ አሐተ ድንግለ ወለተ ቤት እንተ ኢያእመረት ብእሴ፤ ዲቁናን የሚሾሙ ካህናት ድንግልና ያላቸው ይሁኑ። ወንድ ያላወቀች ድንግል የቤት ልጅም ያገቡ ይሁኑ" ይላል (ባህል 14)። ከዚህ ውጭ ከሆነ ግን ክህነታቸው ይሻራል። ከላይ የተጠቀሰው ልጅም በራሱ ያጠፋው ጥፋት የለም። ልጂቱ ባለማወቅ ይህንን ማድረግ አልነበረባትም። ቢሆንም ግን ድንግል እንዳልነበረች ካወቀበት ቅጽበት ጀምሮ ቢተዋትና ሌላ ሳያገባ እንዲሁ ከኖረ በክህነቱ ይቀጥላል። ካወቀ በኋላ ከእርሷ ጋር ቢቀጥል ግን ክህነቱ ይሻራል። ስለዚህ ክህነቱን በጣም ከፈለገም ከዚያ በኋላ ሳያገባ መኖር ነው። ሥጋዊ ፈቃድ ያሸንፈኛል አይሆንም

ካለ ደግሞ ክህነቱ ፈርሶ ከልጅቱ ጋር አንድ ላይ መቀጠል ይችላል። ማናቸውም ፈተና ሲደርስ ፈተናውን በሕጉ መሠረት ከተወጡት ሰማያዊ ዋጋን ያገኙበታል። ስለዚህ ይህ የቤተክርስቲያንን ፍትሓዊነት ጥያቄ ውስጥ አይከተውም።

## ፻፫. ባልና ሚስት ግንኙነት ከፈጸሙ በኋላ ቤተክርስቲያን መግባት ይቻላል?

መልስ፦ በሐዲስ ኪዳን ባልና ሚስት በመኝታ የሚያደርጉት ግንኙነት ርኵሰት አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው መኝታው ቅዱስ ነው። "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን። ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል" እንዲል (ዕብ.13፥4)። አሁን በወር አበባ ያለች ሴት ወደ ቤተክርስቲያን አትገባም። ይኸውም ርኵሰት ሆኖ ሳይሆን ስለክብረ ቤተክርስቲያን ነው። እንኳንስ በእግዚአብሔር ፊት በምድራዊ ንጉሥ ፊት ስንቀርብ ልብሳችንን አንጽተን፣ ሰውነታችንን ታጥበን ነው። ወደ እግዚአብሔር ቤት ስንመጣም ሰውነታችንን ታጥበን ልብሳችንን አንጽተን መሆን ይገባናል። ባልና ሚስት ግንኙነት ካደረጉ በኋላ ሰውነታቸውን ታጥበው ወደ ቤተክርስቲያን መቅረብ እንደሚችሉ ሳዊሮስ ዘእስሙናይን ጽፏል። በብሉይ ወደ ቤተ መቅደስ የሚገባ ሰው ግንኙነት ካደረገ ከሦስት ቀን በኋላ ይገባ ነበር (1ኛ ሳሙ.21፥5)። በሐዲስ ግን እንዳልተከለከለ ሳዊሮስ "ወኢረሰየነ እንከ ርኩሳነ በእንተ ምስካብነ ምስለ ብእሲትነ ወኢከልአነ እምጸሎት ወእምበዊአ ቤተክርስቲያን፤ ከሚስታችን ጋር በመተኛታችን ርኩሳን አላደረገንም ከጸሎትና ቤተክርስቲያን ከመግባትም አልከለከለንም" ብሏል (ድርሳን 8)። በሀገራችን አንዳንድ መምህራን እስከ ሦስት ቀን ይከልከል ሲሉ አንዳንዶች ደግሞ አንድ ቀን ይከልከል ይላሉ። ለሁለቱም ሐሳቦች ማስረጃ ግን አላገኘሁም። ነገር ግን ለጸሎት ስንቆምና ቤተክርስቲያን ስንገባ ታጥበን መግባት ይገባናል። የነግሁንና የመንፈቀ ሌሊቱን እጃቸውን ከታጠቡ በኋላ ይጸልዩ ሰው ከተኛ ዘንድ ዝንየት አይጠፋምና ተብሏል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14)። ቁርባን ለመቁረብ ግን በፊት ሦስት ቀን በኋላ ሁለት ቀን ከግንኙነት መከልከል ይገባል።

## ፻፬. ወልድ በባሕርይ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው እንላለን። ወልድ ከድንግል ማርያም ሥጋን ነስቶ ሲወለድ የሰውን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጓል ይባላል። ስለዚህ ኢየሱስ ሰውም አምላክም ነው። ታዲያ አሁን ክርስቶስን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንዴት አንድ ባሕርይ ነው እንላለን? ምክንያቱም እርሱ የሰውም የአምላክም ባሕርይ ነው ያለው አብና መንፈስ ቅዱስ ግን የአምላክነት ባሕርይ ብቻ ነው ያላቸውና።

መልስ፦ ክርስቶስን በባሕርይ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ ነው ስንለው በአምላክነቱ ነው። ከእኛ ጋር በባሕርይ አንድ ነው ስንለው ደግሞ በሰውነቱ ነው። ኤራቅሊስ የተባለ ሊቅ "አንተ ዘኢትመውት ዘከመ ዕሪናከ ምስለ አብ ወአንተ መዋቲ ዘከመ ዕሪናከ ምስሌነ፤ ከአብ ጋር አንድ እንደመሆንህ ሞት የሌለብህ ከእኛ ጋር አንድ እንደመሆንህ [በመስቀል ላይ] የሞትክ አንተ ነህ" ብሏል (ሃይ.አበ.48፥12)።

ከአስታራቂነቱ በተጨማሪ ክርስቶስን መካከለኛ ከምንልበት ምክንያት አንዱ አምላክ ወሰብእ በመሆኑ ነው:: ይህንን ስንል ሁለትነት ያለ አያስመስልም ወይ ከተባለ አያስመስልም:: ተዓቅቦው በተዋሕዶ ነውና:: ተጠፋፋስ አያሰኝም ወይ ከተባለ አያሰኝም ተዋሕዶው በተዓቅቦ ነውና:: የእኛ የሰዎች ነፍስና ሥጋችን በተዋሕዶ አንድ ሆነው ሰው እንባላለን:: በርቀታችን መላእክትን በግዘፋችን እንስሳትን ብንመስልም አንድ እንባላለን አንድ ባሕርይ አለን እንባላለን እንጂ ሁለት አንባልም:: ክርስቶስንም በመለኮቱ አብን ይመስላል በሰውነቱ እኛን ይመስላል ስንል ዋሕደ ባሕርይነቱን በመመስከር ነው::

፻፳. በአብዛኛው የቅዱሳን ገድላት ቤተክርስቲያንህን የተሳለመ፣ በቤተክርስቲያንህ የተቀበረ፣ ቤተክርስቲያንህን ያሠራ ወዘተ ይህን ያክል ትውልድ እምርልሃለሁ የሚል ቃል ኪዳን አላቸው:: ሰው የፈለገ ኃጢአት ሠርቶ በቃል ኪዳን ብቻ መዳን ይቻላል?

መልስ፦ በቃል ኪዳን ብቻ ሰው አይድንም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ተብሎ ተጽፏል (ማር.16፥16):: ይህ ማለት ግን ያመነ የተጠመቀ ብቻ ይድናል ማለት አይደለም:: ከማመን በተጨማሪ መልካም ሥራን መሥራት፣ ሥጋውን ደሙን መቀበልም እንደሚያስፈልግ በሌላ ክፍል ተገልጿልና (ያዕ.2፥17፤ ዮሐ.6፥54):: ቃልኪዳንም የራሱ የሆነ ጥቅም ቢኖረውም ያለእምነት፣ ያለመልካም ሥራ ብቻውን ግን ያድናል ብለን አናስተምርም::

፻፳፩. እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው ሁሉን ቻይ ነው ስለዚህ ሲኦል ቀድሞ መፈጠሩን ያውቃል:: ከምድርም ከመላእክትም ዘንድ ኃጢአትን ወይም ክፍትን እናዳናስብ አድርጎ ዓለምን ለምን አልፈጠረም? ይህ ሁሉ ከሚሆን ለምን መንግሥተ ሰማያትን ብቻ አያዘጋጅልንም ነበር?

መልስ፦ በነገራችን ላይ ሰውና መላእክት ከሁሉ በላይ የከበሩ ተደርገው ተፈጥረዋል:: ከክብራቸው መገለጫዎች አንዱ ነጻ ፈቃድ ያላቸው መሆናቸው ነው:: እግዚአብሔር ደግሞ ቸር ስለሆነ ከማስገደድ ይልቅ ምርጫቸውን ራሳቸው እንዲወስኑ አድርጓቸዋል:: ሲኦል በራሷ መልካም ፍጥረት ናት:: ነገር ግን የሚበድሉትን የምታቃጥል ናት:: ሰው ገነትና ሲኦል ቀርበውለት በራሱ ምርጫ ሲኦልን ከመረጠ የሰዎችን ምርጫ ማክበር የተገባ ነው:: መንግሥተ ሰማያትን አልፈልግም ያሉ ሰዎች በምርጫቸው ይሻለናል ያሉትን ሲኦል መርጠዋል:: ስለዚህ የሲኦልም የመንግሥተ ሰማያትም መፈጠር ሰው የራሱን ምርጫ ራሱ እንዲመርጥ ነው:: በግድ ማዳን የእግዚአብሔር ሥራ አይደለም:: እግዚአብሔር የእኛን በጎ ነጻ ፈቃድ አይቶ ያድነናል:: ክፋት ራሱን የቻለ ህልውና ያለው ነገር አይደለም:: ክፋት ሰው በራሱ ፈቃድ የፈጠረው የሰውና የሰይጣናት ፍጥረት ነው:: እግዚአብሔር በጎውን አድርጎልን በጎ አንፈልግም ሲኦል ይሻለናል ለምንል ሰዎችም ምርጫችንን ለማክበር ብሎ ሲኦልን ፈጥሯታል::

፻፳፪. ቀሌምንጦስ 8፥6 ከገለጽኩላችሁ ሁሉ የሚዘነጋችሁ ካለ፣ ካያችሁት ተአምራት መንክራት ከሰማችሁት የሚዘነጋችሁ ካለ፣ ካረግሁ በኋላ አባቴ የሚልከው መንፈስ ቅዱስ የተረሳውን

ሁሉ ያስታውሳችኋል ይላል። ራሱ ክርስቶስ እንዳይረሳቸው ማድረግ እየቻለ ለምን ቀጠራቸው? የተላከው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው?

መልስ፦ እግዚአብሔር ሥራውን የሚሠራበት የራሱ ጊዜ አለው። "ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር" እንዲል (መዝ.118፥126)። በመሠረቱ ክርስቶስ ከሐዋርያት ጋር በሥጋ በመካከላቸው ሳለ የገለጠላቸው ዕውቀት ሁሉ የአንድነት ሥራ ስለሆነ ገላጩ እርሱ ብቻ አይደለም። አብም፣ መንፈስ ቅዱስም ናቸው እንጂ። በኋላም መንፈስ ቅዱስ የተረሳውን ይገልጥላችኋል ሲል በመንፈስ ቅዱስ እርሱንም አብንም መናገሩ እንጂ በኋላ መግለጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ብቻ ሆኖ አይደለም። ክርስቶስ ስለእርሱና ስለአባቱ ደጋግሞ ነግሯቸዋል አስተምሯቸዋል። ይህ ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ምንም ያላደረገላቸው እንዳይመስላቸውና ይህ ሥራም የሦስቱም መሆኑን እንዲረዱ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ገላጭ አድርጎ ነግሯቸዋል።

፻፰. ፈያታዊ ዘየማን ያለምስጢራት ገነት ገብቷልና ምስጢራት አያስፈልጉም የሚሉ አሉ። ይህን እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ምሥጢራትን እንድንፈጽም ያዘዘ ራሱ ክርስቶስ ነው። ምሥጢረ ጥምቀትን መፈጸም እንደሚገባ "ኢየሱስም መልሶ እውነት እውነት እልሃለሁ። ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም" ብሎ ተናግሯል (ዮሐ.3፥3)። ምሥጢረ ቁርባንን መፈጸም እንደሚገባ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ" ብሏል (ዮሐ.6፥56)። ሌሎችንም ምሥጢራት መፈጸም እንደሚገባ ያስተማረን ራሱ ክርስቶስ ሆኖ ሳለ የክርስቶስ ተቃራኒ ሆኖ ምሥጢራት አያስፈልጉም ማለት ታላቅ ክሕደት ነው። ፈያታዊ ዘየማን ምሥጢራትን አለመፈጸሙ ቶሎ በመሞቱ ምክንያት እንጂ ምሥጢራት አያስፈልጉም ብሎ አይደለም። በክርስቶስ አምነው ምሥጢራትን ለመፈጸም በዝግጅት እያሉ የሞቱ ሰዎች የሞቱት ደማቸው ጥምቀት ሆኗቸው በዚያ ክብር እንዲያገኙ አድርጓቸዋል። በልቅሶ የነበሩትን ዕንባቸውን ጥምቀት አድርጎ አድኗቸዋል።

፻፱. አንድ ወንድ አግብቶ ልጆችን ከወለደ በኋላ ተምሮ ዲያቆን መሆን ይችላል ወይ? ይህ በውጭ ዓለም ላይ በተለይ እየተለመደ ስለመጣ ቤተክርስቲያን ትፈቅዳለች ወይ? በምን ማስረጃ?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት ላይ "ዲያቆን በአንዲት ሴት የተወሰነ፣ ቤተሰቦቹንም ልጆቹንም ሠርቶ ቀጥቶ ያሳደገ ሰው ዲቁና ይሾም" ይላል (አንቀጽ 7)። በዚህ መሠረት እርሱም ድንግል ሆኖ ኖሮ ድንግል ሴትን በሥርዓተ ቤተክርስቲያን አግብቶ የኖረ ሰው ተምሮ ዲቁናን ሊሾም ይችላል። ይሁንና በሀገራችን ገና በድንግልና ሳሉ ዲቁናን መቀበል የተለመደ ነው። ከመቼ እንደጀመረ ግን መረጃው የለኝም። ከላይ ያለው የተለመደ ባይሆንም ነገር ግን መደረግ የሚችል ነው።

**፻፲. አንድ ዲያቆን ሥጋው አሸንፎት ሴት እያሰበ ወይም በቪዲዮ እያየ መራቢያ አካሉን እየነካ ዘሩን ቢያፈስስ ክህነቱ ይቀጥላል ወይስ ይፈርሳል?**

መልስ፦ ይህንን ጥያቄ እጅግ በጣም ብዙ ጊዜ ተጠይቄያለሁ:: ዘመኑ ያመጣው ክፉ ፈተና መሆኑንም በዚህ መረዳት ይቻላል:: ሰውን መንፈሰ ዝሙት የተባለ ሰይጣን ሲቀርበው ሴቷን የወንዱን አካል ማየትን ያስመኛታል፣ ወንዱን ደግሞ የሴትን አካል ማየትን ያስመኘዋል:: ሕዋሳቱን እንዲዳብስ ያደርገዋል (ወቦ አመ እንዘ ትቀውም ታረመስስ ዲበ አባላቲከ) እንዲል:: ወዓዲ ይወርድ ዲበ እስኪት (ዳግመኛ ወደአባለ ዘር ይወርዳል) ተብሏል (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን 7):: ስለዚህ ሰው ግንኙነት ሳያደርግ በሐሳቡ ግን ግንኙነትን እያሰበ ዘሩን ቢያፈስስ በዚህም ሥጋዊ ደስታን ቢያገኝ ይህ ትልቅ በደል ትልቅ ኀጢአት ነው:: ኃጢአትነቱ ይገለጽ እንጂ ክህነት ያስፈርሳል ወይስ አያስፈርስም በሚለው ዙሪያ ግን መጻሕፍት ላይ የተጻፈ ነገር አላገኘሁም:: እንዲህ ዓይነት ነገሮች ከዘመኑ ጋር የመጡ ፈተናዎች በመሆናቸው አዲስ ቀኖና ሊሠራባቸው ይገባል:: ቀኖና ባልተሠራበት ጉዳይ ላይ ግን ያስፈርሳልም አያስፈርስምም ለማለት ይከብዳል:: ሰው ግን በፍትወት ራሱን ከሚያጎሳቁል ይልቅ ጋብቻ ስለተሠራለት ቢያገባ ይሻለዋል::

**፻፲፩. ዮሐ.1፥14 ላይ ቃል ሥጋ ሆነ ይላል:: ሥጋ ቃልን ሆነ ማለትስ እንችላለን? ወልድ ሥጋ ሆነ ማለትስ እንችላለን?**

መልስ፦ አዎ እንችላለን:: ቃል ሥጋ ሆነ ማለት አምላክ ሰው ሆነ ማለት ነው:: ሥጋ ቃልን ሆነ ካልን ደግሞ ሰው አምላክ ሆነ ማለት ነው:: ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ "ወኮነ ሰማይ ዓለመ ወዓለም ሰማየ" ያለውን መተርጉማን አምላክ ሰው ሰው አምላክ ሆነ ብለውታል (ሃይ.አበ.85፥37):: ቃል በቃልም በተጨማሪ "ውእቱ እግዚአብሔር ዘኮነ ሰብአ ወውእቱ ሰብእ ዘኮነ አምላከ፤ አምላክ ሰው የሆነ ነው:: ሰውም አምላክ የሆነ ነው" ሲል ይገኛል (ሃይ.አበ.61፥23):: ወልድ ሥጋ ኮነ ቢልም ምንም ችግር አያመጣም:: በተለየ አካሉ ሰው የሆነ እርሱ ነውና:: "እስመ ቃል ውእቱ ወልድ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ፤ ሁሉ የተፈጠረበት ወልድ ሥጋ እንደሆነ እንናገራለን" እንዲል (ሃይ.አበ.31፥41)::

**፻፲፪. በማሽን የታረደ ሥጋ መብላት ይቻላል? ማለት የማንኛውም ስም ያልተጠራበት በማሽን ታርዶ ታሽጎ ያለ ሥጋን ባርከን መመገብ እንችላለን?**

መልስ፦ በካራም ይታረድ፣ በማሽንም ይታረድ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብለን ባርከን ብንበላው ምንም በደል የለውም:: "እስመ ይትቄደስ በቃለ እግዚአብሔር ወበጸሎት፤ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና" እንዲል (1ኛ ጢሞ.4፥5)::

**፻፲፫. እመቤታችን ድንግል ማርያም ጥንተ አብሶ (original sin) ነበረባት ወይስ አልነበረባትም?**

መልስ፦ በመሠረቱ ጥንተ አብሶ የሚለው ቃል ሲተረጎም የበደል መጀመሪያ ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለአዳምና ለሔዋን ብቻ ይነገራል እንጂ ለሁሉም ሰው አይነገርም፡፡ ነገር ግን መርገም በጥንተ አብሶ ምክንያት ስለመጣ መርገምን ለመግለጽ ጥንተ አብሶ የሚሉ ሰዎች አሉ፡፡ በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን ግን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ናት፡፡ ስለዚህ ከፅንስ ጀምሮ አልነበረባትም፡፡ እንዳይኖርባትም ራሱ እግዚአብሔር ጠብቋታል፡፡

፻፲፬. በሳይንሱ ዓለም እንደሚወራው የቅሬታ አካል ዕድሜያቸውና (fossil ages) የቤተክርስቲያን ዘመን አቆጣጠርን እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

መልስ፦ ሳይንስ ተለዋዋጭ ነው፡፡ ቋሚ ዕውነት የለውም፡፡ ከዘመናት በፊት እውነት ብሎ የያዘውን ነገር ከዘመን በኋላ በመጡ ምርምሮች መሠረት ሲንደው እናስተውላለን፡፡ ስለዚህ የቅሬት አካላት ዕድሜያቸው ነው እየተባለ የሚነገረው የራሱን የሳይንስን መሠረት የሚጥስ ነገር ነው፡፡ ሳይንስ በማስረጃ የተመሠረተ እውነታ ነው፡፡ ይህ ግን ከማስረጃ ይልቅ ግምት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ የዓለም ዕድሜ የቤተክርስቲያን ዘመን አቆጣጠር እንደሚገልጸው ነው፡፡ ይህንን ደግሞ በእምነት እናውቃለን፡፡

፻፲፭. አንድ ሰዉ በክርስቶስ አምኖ ተጠምቆ፣ ቆርቦ የሚድን ከሆነ በቅዱሳን ባያምንና ባያከብር ምን ችግር ይኖረዋል? በቂ ነውስ አያሰኝም ወይ?

መልስ፦ አያሰኝም፡፡ በቅዱሳን ማመን ማለት እግዚአብሔር ለቅዱሳን ክብርን እንደሚሰጣቸውና በእርሱ ዘንድ የከበሩ መሆናቸውን ማወቅ ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው ቅዱሳንን አልቀበልም ካለ እግዚአብሔር ለቅዱሳን የሰጣቸውን ስጦታ የሚክድ በመሆኑ በተዘዋዋሪ እግዚአብሔርንም አላምንም ማለት ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡ "እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፡፡ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል" እንዲል ቅዱሳንን መቀበል እግዚአብሔርን መቀበል ነውና (ማቴ.10፥40)፡፡ ቅዱሳንን ሳይቀበሉ እግዚአብሔርን አምናለሁ ማለት ማጭበርበር ነው፡፡ ራሱ ክርስቶስ ቅዱሳን ሐዋርያትን "የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፡፡ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፡፡ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል" ብሎ ተናግሯልና (ሉቃ.10፥16)፡፡

፻፲፮. አንዲት ልጅ ከግንኙነት ነጻ (ድንግል ሁና) ግን ከሌላ ወንድ ጋር የፍቅር ግንኙነት ቢኖራት እና ተሳስመው ከዚያ በኋላ ግንኙነት እናድርግ ሲላት አላደርግም ብላ ትታው ብትኖር (ቢለያዩ) ይህች ልጅ ዲያቆን ማግባት ትችላለች?

መልስ፦ ካላገቧት ሚስት ጋር ፍትወታዊ መሳሳም ኃጢአት ነው፡፡ በኃጢአትነቱ ንስሓ መግባት ይገባል፡፡ ሳይጋቡ መሳሳም ትልቅ በደል ነው፡፡ ንጽሕናችንን እንጠብቅ፡፡

ፍትወት አያሸንፈን። ይሁን እንጂ ድንግልና የሚተረጎም ከግንኙነት ጋር ተያይዞ ስለሆነ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ድንግልና አይፈርስም። ስለዚህ አዎ ማግባት ትችላለች።

፶፲፮. ከሲኖዶስ መመሥረት በፊት የነበረችው ቤተክርስቲያን ራሷን ማን ብላ ነበር የምትጠራው? ቅዱስ ሲኖዶስ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ስንት ስብሰባ አደረገ? የወሰናቸው ሃይማኖታዊ (ዶግማዊ)፣ ቀኖናዊ፣ ትውፊታዊ ውሳኔዎች አሉ? ካሉ ቢገለጽ ወይስ አስተዳደራዊ ብቻ ነው? ቅዱስ ሲኖዶስ እስከ ዛሬ ያጸደቃቸው የቤተክርስቲያን የጸሎት እና የአገልግሎት መጻሕፍት አሉ?

መልስ፦ ጥያቄው ሰፊ ነው። ሁሉንም በአጭር ጊዜ መመለስ አልችልም። ቤተክርስቲያን የሚለውን ስም ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገረው ራሱ ክርስቶስ ነው (ማቴ.18፥17)። የሲኖዶስ ጀማሪም እርሱ ራሱ ክርስቶስ ነው። ቀጥለው ሐዋርያት ናቸው። ሐዋርያት በ50 ዓ.ም ሲኖዶስ አድርገዋል። ከዚያም በኋላ ዓለማቀፋዊ ሲኖዶስ፣ አካባቢያዊ ሲኖዶስ ወዘተ ስለነበረ በርካታ ጉባኤያት ተደርገዋል። በየጉባኤው ምን ተወስኖ እንደነበር ፍትሐ ነገሥት ላይ ጥቂቱ ተገልጿል። የአንጾኪያ ሲኖዶስ፣ የሎዶቅያ ሲኖዶስ፣ የዕንቄራ ሲኖዶስ...ወዘተ ይጠቀሳሉ። ኢትዮጵያም በሀገረ ስብከት ደረጃ ሆና በግብጽ የነበሩ የሲኖዶስ ጉባኤዎችን ተሳትፋለች። የራሷን ሲኖዶስ ከአቋቋመች በኋላም መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ በርካታ ጉባኤዎችን አድርጋለች። በእየአንዳንዱ ጉባኤ ምን ተወስኖ እንደነበር በመጽሐፍ መልኩ ወጥቶ ብናየው መልካም ነው። ውሳኔዎቹ ቀኖናዊም፣ አስተዳደራዊም ናቸው። ዶግማ ግን በሲኖዶስ የሚወሰን ሳይሆን እግዚአብሔር አንድ ጊዜ የገለጠው እውነት ስለሆነ ሲኖዶስ የማሻሻልም የመለወጥም መብት የለውም። በዶግማ ላይ የተነሡ ከሓድያን ካሉ እነርሱን እየለየ ይኖራል እንጂ። በሀገራችን በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት የሚወጡት መጻሕፍት ብዙ የሲኖዶስ ይሁንታ ያላቸው መጻሕፍት ናቸው።

፶፲፯. በቤተክርስቲያን ትክክለኛና የተሰጠ ጥበብ አለ ወይ? ቢኖርስ እንዴት አድርገን ነዉ ከጥንቆላ የምንለየው? በዚያው ላይ ፈውስ ሥጋዊና ፈውስ መንፈሳዊ ቢኖራት እንዴት እንጠቀማለን በቤተክርስቲያን መለያዉስ ምን ሊሆን ይችላል?

መልስ፦ የቤተክርስቲያን ዋና ጥበብ ራሱ ክርስቶስ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሰዎች ይጠቀሙበት ዘንድ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጣቸው ጥበቦች አሉ ይኖራሉ። ጥበብን በሦስት ልንከፍለው እንችላለን። መንፈሳዊ ጥበብ፣ ሰይጣናዊ ጥበብና ሥጋዊ ጥበብ ብለን። ሥጋዊ ጥበብ ማረስ፣ መቆፈር፣ መጻፍና የመሳሰለው ነው። መንፈሳዊ ጥበብ መጸለይ፣ መጾም፣ መስገድና የመሳሰለው ነው። ሰይጣናዊ ጥበብ የሰይጣንን ስም በመጥራት የሚደረጉ ክፉ ሥራዎች ሁሉ ናቸው። አሁን አሁን ግን ጥበብ አለን እያሉ ሰውን የሚያታልሉ ብዙ አጭበርባሪዎች ተነሥተዋል። ስለዚህ ሰው በአጭበርባሪዎች እንዳይበላ መፈወስ ከፈለገ ሐኪም ቤት ሄዶ ወይም ጠበል ሄዶ መታከም መጠበል ነው። ጥንቆላ ሰይጣናዊ ጥበብ ነው። ጥበብ መንፈሳዊ ለሁሉ የተሰጠ ነው። የጥበብ

መጀመሪያም እግዚአብሔርን መፍራት ነው፡፡ ከዚያ ውጭ መርጌታ ነን እያሉ ቃለ እግዚአብሔርን ከሰይጣናዊ ድግምት ጋር እያቀላቀሉ የሚያጭበረብሩ ብዙ ናቸው፡፡ ጥበብ የፈለገ ወደ ቤተክርስቲያን ይምጣ፡፡ ንስሓ ገብቶ ሥጋዉን ደሙን ይቀበል፡፡ ከዚህ የበለጠ ጥበብ የለም፡፡

፪፲፱. በተክሊል የተጋቡ ሰዎች ቢፋቱ እና ሌላ ማግባት ቢፈልጉ በምንድን ነው ማግባት የሚችሉት?

መልስ፦ ከተጋቡ በኋላ የጋብቻ ሕይወት የሰማዕትነት ሕይወት ስለሆነ ተቻችሎ፣ ተከባብሮ፣ በመነጋገር መኖር ይገባል፡፡ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት የተፋቱ ሰዎች ካሉና መታረቅ የማይችሉበት ደረጃ ከደረሱ ግን ጋብቻ የሚፈጸመው ሁልጊዜም ቢሆን በቊርባን ነው፡፡ ይህም ከንስሓ አባት ጋር በመመካከር ይፈጸማል፡፡ ያለቊርባን ጋብቻ አይደረግም፡፡

፪፳. ዲያቆን ከጋብቻ በፊት ከሚያገባት ጋርና በኋላ ከሚስቱ ጋር መሳሳም ይችላል? በፊት ተሳስሞስ ቢሆን ምን ማድረግ አለበት?

መልስ፦ ከጋብቻ በፊት እጮኛው ብትሆንም ፍትወታዊ መሳሳም አይፈቀድም፡፡ ይህ ቁጥሩ ከምርዐት (ከመዳራት) ነውና፡፡ ተሳስሞ ከነበረ ንስሓ ይግባ፡፡ ካገባት በኋላ ግን ለሌላው ሰው ፈተና እንዳይሆን በአደባባይ አይሳማት እንጂ በቤታቸው መሳሳምም ሌላም ይቻላል፡፡

፪፳፩. የወለደች ሴት/አራስ የወለደችው ወንድ ከሆነ በ10 ቀን የወለደቻት ሴት ከሆነች በ20 ቀን ካህናት ወደ ቤት በመሄድ ወላዲን ያጠምቋታል፡፡ ከሕፃናቱ በ40/80 ቀን ጥምቀት ጋር የሚያገናኘው ነገር አለ? ካህን ሚስቱ ብትወልድ ከአገልግሎት (ቅዳሴ) ይከለከላልን?

መልስ፦ አንዲት ሴት ከወለደች በኋላ በአንዳንድ ቦታዎች በዐሥረኛ ቀኗ ካህናት ሲያጠምቋት ይስተዋላል፡፡ በእርግጥ የተጸለየበትን ውሃ መረጨት ለማንኛውም ሰው መልካም ነው፡፡ ከዚህ በዘለለ ስለምትረክስ ነው የሚያጠምቃት የሚሉ ሰዎች ግን ፍጹም ተሳስተዋል፡፡ በሐዲስ ኪዳን ልጅን መውለድ በረከት እንጂ ርኵሰት አይደለም፡፡ አንዳንዶች አራስ ጠይቀናል ረክሰናል ብለው ከቤተክርስቲያን ሁሉ የሚቀሩ አሉ፡፡ ነገር ግን ይህ ስሕተት ነው፡፡ እንኳን አራስ የጠየቀ ሰው ሚስቱ ብትወልድለት ካህን ከአገልግሎት መከልከል የለበትም ተብሏል፡፡ መጽሐፋዊ መሠረት የሌለው ክፉ ልማድ መቅረት አለበት፡፡ የወለደችን አራስ ማሳለምም አልተከለከለም፡፡ ከቤተክርስቲያን የምትገባው ግን ወንድ ከወለደች ከ40 ቀን በኋላ ሴት ከወለደች ከ80 ቀን በኋላ ነው፡፡ ካህን ሚስቱ ብትወልድ ከአገልግሎት መከልከል እንደሌለበት ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6 ላይ ቅዱስ አቡሊዲስን ጠቅሶ ገልጾታል፡፡

፻፳፪. የሲኖዶስ ጉባኤ የሚመራው በመንፈስ ቅዱስ ነው ብለን እናምናለን፡፡ ውጤቱ (ውሳኔው) ግን ሥጋዊ (ፖለቲካዊ) ለምን መሰለ?

መልስ፦ የሲኖዶስ ጉባኤ የሚመራው በመንፈስ ቅዱስ ነው ማለት ነገረ መንፈስ ቅዱስን ይነጋገራል፣ በመንፈስ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ይነጋገራል ማለት ነው፡፡ እንጂ የሰዎች ስብስብ የወሰነው ውሳኔ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ነው ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ ሲኖዶስ እግዚአብሔር ባዘዘው ሕግና ሥርዓት ተመርቶ ከወሰነ ውሳኔው መንፈስ ቅዱሳዊ ነው ይባላል፡፡ እግዚአብሔርን ትቶ በፖለቲካዊ ጫናና በመሳሰሉት ያለ እግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት ከወሰነ መለካዊ ወይም ሰይጣናዊ ይባላል፡፡

፻፳፫. ሥዕለ አድኅኖ ቤት ላይ ማስቀመጥ ይቻላል አይቻልም?

መልስ፦ ሥዕለ አድኅኖ ከቤትም ከቤተክርስቲያንም ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑን ትውፊታዊና ታሪካዊ ነገሮች ናቸው፡፡ ሥዕለ አድኅኖ በቤተክርስቲያን እንደሚኖር በትርጓሜ ቢያንስ ቢያንስ በታቦቱ ሥዕለ ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ እንዲኖር በትርጓሜ መነገሩ ነው (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 1 ትርጓሜ)፡፡ በታሪክ መገለጹ አፎሚያ ሥዕለ ሚካኤልን ከቤቷ አውጥታ ሰይጣንን ማሸነፏ በድርሳነ ሚካኤል መገለጹ ነው፡፡

፻፳፬. አብ መለኮት ወልድ መለኮት መንፈስ ቅዱስ መለኮት ይባላል ወይ?

መልስ፦ መለኮት የሚለው ባለብዙ ትርጉም ነው፡፡ መለኮት ከዊንን የሚያመለክትበት ጊዜ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ አብ መለኮት፣ ወልድ መለኮት፣ መንፈስ ቅዱስ መለኮት ልንል እንችላለን፡፡ ትርጉሙ አብ ልብ፣ ወልድ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ማለት ነው፡፡ በዚህ አግባብ ከሆነ ይባላል፡፡

፻፳፭. የክህነት ሥርዓት እና ጾም ከዶግማ ነው ከቀኖና የሚያያዙት?

መልስ፦ ዶግማ የሚባለው በዘመን ብዛት የማይለዋወጥ የቤተክርስቲያን ዕውነት ነው፡፡ ቀኖና ደግሞ ያንን ዕውነት ለማስፈጸም በተለያዩ ዘመናት፣ በተለያዩ ቦታዎች የሚተገበር በአተገባበሩ በየዘመናቱ ሊለዋወጥ የሚችል ነገር ነው፡፡ የክህነትን አስፈላጊነት መግለጽ ወይም ክህነት አስፈላጊ እንደሆነ መናገር እውነት ስለሆነ ዶግማ ነው፡፡ ክህነት ማን ይሾም? በምን መሥፈርት ይሾም? ወዘተ የሚሉት ደግሞ አተገባበሮች ስለሆኑ ቀኖና ይሆናል፡፡ ጾም አስፈላጊ መሆኑን መናገር ዶግማ ነው፡፡ እስከ ስንት ሰዓት ይጾም? ማን ይጹም? እንዴት ይጾም የሚሉትና የመሳሰሉት ግን አፈጻጸሞች ስለሆኑ በጊዜ፣ በቦታ፣ በዕድሜ፣ በጤናና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ስለሚወሰኑ ቀኖና ይሆናሉ፡፡

፻፳፮. መቅድመ ተአምረ ማርያም ቁጥር 35 ላይ በሥዕሏም ፊት ስገዱ፡፡ ለሥዕሏ ያልሰገደ ግን ከቀመበት ቦታ ይጥፋ፡፡ ስም አጠራሩም አይታወቅ ሲል ምን ማለት ነው?

መልስ፦ በሥዕሏ ፊት መስገድ የጸጋ አክብሮት ምልክት ነው። ቅዱሳንን በጸጋ ማክበር ደግሞ ተገቢ ነው። ለቅዱሳን የጸጋ ክብር አያስፈልግም ብሎ ለሥዕሏ ያልሰገደ ሰው ግን ይጥፋ ማለቱ ይጠፋል ማለት ነው። ስም አጠራሩም አይታወቅ ማለት አይታወቅም ማለት ነው። የሚገባ ርግማን አለና። ይህም ቅዱስ ጴጥሮስ ረግሞ እንዳጠፋው ያለ ነው። "ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ" እንዲል (የሐዋ. ሥራ 8፥20)።

፻፳፬. ለ5500 ዘመን ያህል ዲያብሎስ ከፅንስ ጀምሮ ሰወችን ሲቆራኝ ነበር። ከነጻ ፈቃዳቸው ላይ ሥልጣን ነበረው? ከነበረው ለምን ሰወች በንፍር ውሃና በእሳት ጠፉ?

መልስ፦ የሰው ልጅ ነጻ ፈቃዱን ተጠቅሞ ዕፀ በለስን ከበላ በኋላ በራሱ ላይ ባለሙሉ ሥልጣን መሆኑን አጥቶት ነበር። በመሆኑም እኩያት ፍትወታት፣ አጋንንት ሠልጥነውበት የሚኖሩ ሆነዋል። እግዚአብሔር ግን ቸር ስለሆነ ነጻነታቸውን ጨርሶ አላጠፋባቸውም። ስለሆነም የሐዲስ ሕግ እስክትሠራ መቆያ ትሆናቸው ዘንድ የኦሪትን ሕግ ሰጣቸው። ከኦሪትም በፊት ክፉና ደጉን የሚለዩበትን ሕገ ልቡና ከልባቸው አኑሮላቸው ነበር። ከዚህም በኋላ በተቀመጠላቸው ሕግ ባለመኖራቸው በንፍር ውሃ፣ በእሳት እንዲጠፉ አድርጓቸዋል።

፻፳፭. አንድ ሰው ንስሓ ገብቶ ሳያስፈታ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን መቀበል ይችላል? አገልጋዮችስ ንስሓ ገብተው ሳያስፈቱ ቅዳሴ መግባት ይችላሉ? ለነፍስ አባታችን ንስሓችን ተናዝዘን ሱባዔ ስንጨርስ ወዲያው ብንቆርብ እንደገና ከአንድ ወር በኋላ መቁረብ ብንፈልግ ሌላ ንስሓ ገብተን ነው ወይስ ጌታ ሆይ ማረን ብለን መቁረብ እንችላለን? አንድ ክርስቲያን በዓመት ቢያንስ ስንት ጊዜ መቁረብ ዓለበት?

መልስ፦ አይችልም። ሰው ንስሓ ከገባ በኋላ ቀኖናውን ጨርሶ ፍትሐት ዘወልድ ተደግሞለት ከተፈታ በኋላ መቀበል ይገባዋል። ንስሓ ገብተን፣ ቀኖናችንን ጨርሰን፣ ፍትሐት ዘወልድ ተደግሞልን ከቆረብን በኋላ ከዚያ በኋላ ኃጢአትን ካልሠራን ደጋግመን ለብዙ ጊዜ መቍረብ እንችላለን። መካከል ላይ ኃጢአትን ከሠራን ግን ንስሓ እየገባን ከላይ ያሉትን ቅደም ተከተሎች ፈጽመን መቍረብ ነው። አንድ ክርስቲያን ንስሓ እየገባ በየጊዜው መቍረብ አለበት። ቢያንስ፣ ቢበዛ የሚባል ነገር የለም።

፻፳፮. ቀዳም ሥዑር ወይም የተሻረች ቅዳሜ የተባለበት ዋናው ምክንያት ምንድን ነው? ቀዳም ሥዑር የማይቀደስበት ምክንያት ምንድን ነው?

መልስ፦ ቅዳሜ ሥዑር የማይቀደስበት ምክንያት ቀኑን ሙሉ የምትጾም ጾም ስለሆነች ነው። ቀዳም ሥዑር የተባለችበት ምክንያት ዓመቱን ሙሉ የማይጾምባት በዓል ሆና ሳለ በዚህ ቀን ግን በጾም በመሻሯ ምክንያት ነው። ሁለተኛ ክርስቶስ በመቃብር ሆኖ ሙስና መቃብርን ያጠፋባት፣ የመቃብርን ሥልጣን የሻረባት በመሆኗ ቀዳም ሥዑር ተብላለች።

፶፴. ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን በጸሎተ ኀሙስ ከበሉ በኋላ አቆረባቸው፡፡ ዛሬ በቤተ ክርስቲያናችን 18 ሰዓት ተጹሞ ነው የሚቆረበው ምክንያቱ ምንድን ነው?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13 ላይ ወኢይንሣእ መኑሂ ቊርባነ ዘእንበለ ይጹም በንጹሕ ተብሏል፡፡ ይህም ከቊርባን በፊት መጾም እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ የጾም ጊዜ ደግሞ ቢያንስ እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ነው፡፡ ይህም ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡ ይህንን ስንደምረው 18 ሰዓት ይሆናል፡፡ ይህንን መሠረት አድርጎ ከቊርባን በፊት 18 ሰዓት እንዲጾም በትውፊት ይነገራል፡፡ ቃል በቃል 18 ሰዓት ይጾም የሚል ግን እስካሁን አላገኘሁም፡፡ እንደ ምክንያት ጌታ ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ 9፡00 መከራ መቀበሉን ለማሰብ እንደሆነ ሲነገር ሰምቻለሁ፡፡ ሐዋርያት ወዲያው ቢበሉም በተአምራት አጥፍቶላቸው፣ በሕፃናት አምሳል እንደቆረቡ ይነገራል፡፡

፶፴፩. የሥጋዌ ስሞች ለምሳሌ ክርስቶስ ኢየሱስ ሁላቸውም የባሕርይ ስም ይባላሉ?

መልስ፦ እንኳንስ የእግዚአብሔር የፍጡራን የባሕርይ ስም እንደማይታወቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ገልጾልናል፡፡ "እስመ ሶበ ኢረከበ ስመ ዘይኤምር ኀበ ባሕርይሁ፤ የባሕርይ ስሙን የሚያስረዳ ስም ባይገኝ ዕበይ አለው" ብሏል፡፡ ቀጥሎም "ዝ ስም ዘውእቱ ብሂለ እግዚአብሔር ኢይኤምር እንከ ኀበ ውእቱ ባሕርይ፤ ይኸውም እግዚአብሔር ማለት የባሕርይ ስሙን አያስረዳም፡፡ ኅድግሰ ባሕርየ እግዚአብሔር ልዑል ለመልአክኒ ጥቀ ኢይትረከብ ስመ ባሕርይሁ፤ ባሕርየ እግዚአብሔርንስ ተወውና የመልአክስ እንኳ የባሕርይ ስሙ አይታወቅም" ብሏል (ድርሳን 2)፡፡ ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ አማኑኤል ወዘተ የሚሉት የሥጋዌ ስሞች ግብረ ባሕርይን የሚያመለክቱ ናቸው እንጂ የባሕርይ ስሞች አይደሉም፡፡ ኢየሱስ የሚለው አዳኝነቱን፣ አማኑኤል የሚለው እንደእኛ ሰው ሆኖ ከእኛ ጋር መሆኑን ያመለክታል፣ ክርስቶስ የሚለው ሥጋ በተዋሕዶ መክበሩን ያመለክታል፡፡

፶፴፪. አብዛኛውን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ሰንበቴ እና ነዳያን እንዲመገቡ ይደረጋል፡፡ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 1 በቤተክርስቲያን ለማብላት ሰውን መጥራት አይገባም፡፡ በዙሪያውም ለማብላት መጥራት አይገባም ይላል፡፡ አይቃረንም?

መልስ፦ ይቃረናል፡፡ እንደ ፍትሐ ነገሥቱ በቤተክርስቲያን ውስጥና በቤተክርስቲያን ዙሪያ ድግስ ተደግሦ ሥጋዊ ምግብ አይበላም ነበር፡፡ በእርግጥ ይህንን ተግባራዊ የሚያደርጉ አድባራት ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ በተቻለ መጠን ከቅጽረ ቤተክርስቲያን ውጭ ሰንበቴ ማድረግ፣ ነዳያንን መመገብ ይገባል፡፡

፶፴፫. አንድ ምእመን ወይም ዲያቆን ዝንየት ቢያገኘው ቅዱስ ቁርባን የሚቀበለው ከአንድ ቀን በኋላ ነው ወይስ ከሦስት ቀን በኋላ ነው?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተጻፈ አላገኘሁም። እንዲሁ ግን አንዳንድ መምህራን ታጥቦ አንድ ቀን ቆይቶ ይቍረብ ሲሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ በጋብቻ በግንኙነት እንደሚያጋጥም ያለ ነገር ስለገጠመው ሦስት ቀን ይላሉ። በዚህ ዙሪያ የተሠራ ሥርዓት ካለ አላውቅም። እኔ ካነበብኳቸው መጻሕፍት ግን በዚህ ዙሪያ የተጻፈ አላገኘሁም።

፻፴፬. አውሮፓ የሄድኩት በቅርቡ ነው። እዚህ ሀገር ለመጾም በጣም ይከብዳል። ቢሆንም ግን እስካሁን ሁሉንም አጽዋማት ለመጾም ሞክሬያለሁ። ወደ ጥያቄዬ ስመጣ ልጄ 10 ዓመት አልፏት ወደ 11 እየሄደች ነው። እዚህ ስንመጣ በተለይ አሁን ያሳለፍነውን የዐቢይ ጾም አልጾመችም። ጨለማና በረዶ ስለነበር የግድ ፀሐዩን እና ብርዱን የሚቋቋሙ ምግቦችን መመገብ ነበረባት። እና አሁን መጾም የለብሽም ብዬ እንድትበላ አደረኳት። በዚያ ላይ ያለንበት ቦታ ቤተክርስቲያን የለም። የኤርትራውያን የአምልኮ ቦታ አለ ከዚያ አንዳንዴ እንሄዳለን። በሦስት ወርም በሁለት ወርም ዐበይት በዓላትን እየጠበቁ ታቦት ከሌላ ቦታ በማምጣት ቅዳሴ ይቀድሳሉ። እናም የፊታችን ቅዳሜ ቅዳሴ አለ። ልጄ ሳትጾም ብትቀርብ ችግር አለው? ዝም እንዳልላት አሁን ጀምራ ሥጋውን ደሙን ማቋረጧ ውስጤን ረበሸው። ትቁረብ ብዬ እንዳላቆርባት እያወኩ ማቁረቡ እግዚአብሔርን መዳፈር ሆነብኝ ምን ላድርግ?

መልስ፦ ጾም ለሁሉም አስፈላጊ መሆኑ በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15 በስፋት ተገልጿል። ነገር ግን ከንስሓ አባት ጋር በመነጋገር የታመሙ ሰዎችና ልዩ ምክንያት ያላቸው ሰዎች መጾም የማይችሉበት ምክንያት ካለ በመነጋገር ሊፈጸም ይችላል። አኃት አብያተ ክርስቲያን አንድ ስለሆንን መቍረብ እንችላለን። ልጅቱ ትቍረብ ወይስ አትቍረብ የሚለውን ግን የንስሓ አባታችሁን አማክራችሁ በእርሳቸው ውሳኔ መሠረት ቢደረግ መልካም ነው።

፻፴፭. ሰው ከምንኩስናና ከጋብቻ ውጭ መኖር ይችላልን?

መልስ፦ ሳያገቡም፣ ሳይመነኩሱም የእግዚአብሔርን ሕግ እየፈጸሙ የሚኖሩ ሰዎች ይኖራሉ። ለዚህ ብዙ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻል ይሆናል። ለምሳሌ ሥርዓተ ምንኵስና የተጀመረው በእንጦንስ ነው። ከእንጦንስ በፊት የነበሩት አባቶችን ብናይ ሳያገቡ ሳይመነኩሱ ኖረዋል (ነቢዩ ኤልያስ፣ ዮሐንስ መጥምቅ)። ወይ ማግባት አለበት ወይ መመንኰስ አለበት የሚል አስገዳጅ ሕግ ያለበት ጽሑፍ እስካሁን አላገኘሁም።

፻፴፮. ለቤተክርስቲያን ወሳኙ አገልግሎት የቱ ነው ቅዳሴ ነው? ሰዓታት ነው? ማሕሌት ነው ወይስ ስብከት ነው? ሦስቱም ወሳኝ ነው ካሉ ሦስቱም ተሟልቶ የማይገኝበት አለ የእነርሱ መፍትሔ ምንድን ነው?

መልስ፦ ብዙው ሰው የተማራትን ትምህርት ከፍ ከፍ እያደረገ፣ ያልተማራትን ትምህርት ደግሞ እየናቀ ማየት የተለመደ ነው። የቤተክርስቲያን ትምህርት ግን ሁሉም ዓላማው ወደ ድኅነት ማድረስ ነው። ስለዚህ ልናበላልጠው አንችልም። ሁሉም አስፈላጊ

ትምህርት ነው። ባወቅነው ዕውቀት እግዚአብሔርን በፍቅር ማገልገሉ ላይ ትኩረት ብናደርግ የተሻለ ነው። ሁሉም የቤተክርስቲያን ትምህርቶች ተሟልተው የማይሰጡበት ቦታ እንኳ ቢኖር ባለው ትምህርት ማስኬድ ነው። ሰው እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ስብከት ያስፈልጋል። እግዚአብሔርን ያወቀ ሰው ምሥጢራትን መፈጸም ስላለበት ምሥጢራት የሚፈጸሙበት ቅዳሴ ያስፈልጋል። ምሥጢራትን የፈጸመ ሰው እግዚአብሔርን ለማመስገን ሰዓታት፣ ማኅሌት አሉለት።

**፻፴፯. አንድ መምህር መድረክ ላይ ንስሐ መግባት ያለማሰሪያው ሥጋውና ደሙ ዋጋ የለውም አሉን። እውን ንስሐ ገብተን ባንቆርብ የኃጢአት ሥርየት አይደረግልንምን?**

መልስ፦ ንስሓ መግባት መልካም ነገር ነው። የራሱ የሆነ ጥቅምም አለው። ንስሓ የገባ ሰው ካልቆረበ ግን ኃጢአቱ አይሠረይለትም። ከጥምቀት በኋላ የተሠራ ኃጢአት በቁርባን ይሠረያልና። በመጽሐፈ መነኮሳት "ወኀጣውእሰ እንተ እምድኅረ ጥምቀት ትሠረይ በምሥጥራተ ቅድሳት፤ ከጥምቀት በኋላ የሚሠሩ ኃጣውእ ግን በሥጋው በደሙ ይሠረያሉ" እንዲል (ፊልክስዩስ ተስእሎ 142)።

**፻፴፰. አንድ የክርስትና እናት ወይም አባት ለመሆን የሥጋ ዘመድ ይቻላል?**

መልስ፦ የሚከለክልም፣ የሚፈቅድም መጽሐፍ አልገጠመኝም። አላውቀውም። ከዓላማ አንጻር ካየነው የክርስትና እናት አባት ዓላማ ክርስትናን ማስተማር ስለሆነ ለማስተማር ዘመድም ይችላል። ከትውፊት አንጻር ከታየ ደግሞ ብዙ ጊዜ ከዘመድ ውጭ የሆነ ሰው ነው ክርስትና የሚያነሣ።

**፻፴፱. ክህነት ያለው ሰው ዶሮ፤ በግ ማረድ ይችላል?**

መልስ፦ ስለ ካህናት ከክርስቶስ ሥጋና ደም ውጭ የሌላ ፍጥረት ደም ማፍሰስ አይገባቸውም እየተባለ ይነገራል። ለዚህ አነጋገር መነሻ የሆነ መጽሓፋዊ ቃል ግን አላገኘሁም። ስለዚህ ይችላልም አይችልምም ማለት አልችልም። አላውቀውም።

**፻፵. ሰኔ ጎልጎታና ራእየ ማርያም የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ናቸው?**

መልስ፦ ሰኔ ጎልጎታና ራእየ ማርያም የሚባሉ መጻሕፍት እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ መጻሕፍት በቀኖና ደረጃ ከአዋልድነት ይመደቡ ወይም አይመደቡ ግን መረጃው የለኝም።

**፻፵፩. እኔ በሙያየ አዋላጅ ነርስ ነኝና ሁሌ ኪዳን ማስደረስ እፈልጋለሁ። መቼ ነው ቤተክርስቲያን የምገባው? ከዚህ ሥራ ስወጣ ስሞት?**

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አዋላጆች ወንድ ካዋለዱ 20 ቀን ሴት ካዋለዱ 40 ቀን ከቍርባንና ቤተክርስቲያን ከመግባት እንዲከለከሉ ይናገራል። ይህ በቀድሞው ዘመን

የተሠራ ነው (አንቀጽ 24)፡፡ (እስከዚህ ቀናት እንዲቆዩ የታዘዘበት መነሻ ምክንያት ምን እንደሆነ አላውቀውም)፡፡ ነገር ግን አዋላጅ ነርስ ሥራው ይህ ስለሆነ በዚህ አካሔድ ከሄድን ለዘለዓለም ቤተክርስቲያን አይግባ እንደማለት ይቆጠራል፡፡ ይህ ደግሞ ከቤተክርስቲያን ሰውን የማዳን ተልእኮ ጋር ይቃረናል፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ቀኖናውን ከዘመኑ ጋር አስታርቆ የምትገቡበትን መንገድ ወይም ሥርዓት መሥራት ይገባዋል፡፡ [ምናልባት የሲኖዶስ ውሳኔዎች በመጽሐፍ ስላልወጡ አላውቀው ብለን እንጂ ወስኖም ሊሆን ይችል ይሆናል]፡፡ ይህንንና ዘመንን መሠረት አድርገው የመጡ ጉዳዮችን ተወያይቶ አፋጣኝ መልስ መስጠት ግዴታው ነው፡፡

፻፴፪. አንዳንድ አካባቢዎች አባቶች በሠርክ ሰዓት ዝክር ሲዘክሩ ጸሎት ዘዘወትር አሥርቀት ኪዳንና መስተበቊዕ ደግመው ባርከው ጠበሉን ለሰው ሁሉ ይረጩታል፡፡ ካህናቱም ምእመናኑም ተመግበዋልና ተገቢ ነውን?

መልስ፦ ማናቸውንም ጸሎት መጸለይ ከእግዚአብሔር በረከትን ለማግኘት ነው፡፡ ለምሥጢራት መፈጸሚያ የሆኑት ጸሎቶች ቤተክርስቲያን ብቻ ይጸለያሉ፡፡ ከዚያ ውጭ ያሉት ጸሎታት ግን እንደ ጊዜ ግብሩ ሊጸለዩ ይችላሉ፡፡ ከበላን በኋላም ቢሆን ውሃውን አቅርበን ጸልየን ብንጠጣው ወይም ብንረጨው ምንም የሚያመጣው ክፋት የለውም፡፡ ቁርስም፣ ምሳም ስንበላ ጸልየን እንበላለን፡፡ ጸልየን እንጠጣለን፡፡ ይህ በረከትን ያስገኛልና፡፡ በራእየ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ትርጓሜ ላይ እንደተገለጸው ዐቃቤ ሰዓት አበሞ የተባሉት ሊቅ አንድን ውሃ ሰባ አንድ ጊዜ ጸሎት አድርጌበት ብጠጣው ምሥጢር ገለጠልኝ ብለዋል፡፡ የታመመ ሰው ከሕመሙ ይፈወስበት ዘንድ በማናቸውም ሰዓት የተጸለየበትን ውሃ ቢጠጣው ቢረጨው ፈውስን ያገኝበታል፡፡ ስለዚህ በልተው ቢሆንም ምንም ችግር የለውም፡፡

፻፴፫. አንዳንድ የጠበል ቦታዎች ሰዓት ሳይደርስ ጠበል መጠመቅን ይከለክላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ጾም ሆኖ ሳለ በጠዋት መጠመቅ ችግር የለም ይላሉ፡፡ ይህ ከሥርዓት አንጻር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ለመጠመቅ ብቻ ከሆነ በጾም ወቅት ጠዋትም መጠመቅ ይቻላል፡፡ ጠበል መጠጣት የሚቻለው ግን የጾሙ ሰዓት ከደረሰ በኋላ ነው፡፡ በጠዋት ጸሎት ፊትን እጅን መታጠብ እንደሚገባ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14 ተገልጿል፡፡ መጠመቅም ምንም እንኳ በተቀደሰ ውሃ (በጠበል) ቢፈጸምም አፈጻጸሙ ተመሳሳይ ስለሆነ ጾም አያስገድፍም፡፡

፻፴፬. በክብረ በዓል/ንግሥ ጊዜ አንዳንድ አካባቢዎች ግማሾቹ ካህናት ወደ ቅዳሴ ሲገቡ ግማሾቹ ደግሞ ወደ መስክ ታቦቱን ይዘው ይሄዳሉ ታቦቱ ሲመለስ ቅዳሴው ይፈጸማል፡፡ ታቦት በሌለበት ደግሞ አይቀደስም፡፡ እንዲህ የሚያደርጉት ከምን አንጻር ነው? አንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ታቦቱ እዚያው ዞሮ ይገባና ቅዳሴው ይጀመራል ሁሉም ያስቀድሳል ትክክለኛው ሥርዓታችንስ የትኛው ነው?

መልስ፦ ታቦት በሌለበት ቤተክርስቲያን ሊቀድሱ አይገባም። ታቦት በሐዲስ ኪዳን የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚፈተትበት ነውና። ምናልባት በአንዲት ቤተክርስቲያን ከሁለት በላይ ታቦታት ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ ይዘው የወጡት በዔዱበት ሌሎች ደግሞ ባልወጣው ታቦት ምክንያት ቅዳሴ ሊጀምሩ ይችላሉ። ታቦቱ አንድ ብቻ ከሆነ ግን ታቦቱ ዑደቱን ጨርሶ ከገባ በኋላ ቅዳሴ መጀመር የተገባ ነው።

፻፴፫. የሞትን ወይም የልደትን መታሰቢያ ቀናት ለመቁጠር እንደመክፈያ የምንጠቀመው ስንት ሰዓት ነው? አንድ ቀን (ዕለት) መነሻው ስንት ሰዓት ነው? መድረሻው/መጨረሻውስ? መዓልትና ሌሊቱን ለመክፈልስ (ዕለቱ መዓልት እና ሌሊት ተብሎ የሚከፈለው እንዴት ነው ሰዓቱ)? ከሌሊትና መዓልት የሚቀድመው የቱ ነው?

መልስ፦ የሥነ ፍጥረት የጊዜ አቆጣጠር የሚጀምረው ከሠርክ ነው። ይህም ማለት ከምሽቱ 12:00 ሰዓት በኋላ ቀጣዩ ቀን ይጀምራል። የአንድ ቀን ምሽቱ ቀድሞ ቀኑ ይከተላል ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ይህን ቅደም ተከተል በሚያሳውቅ መንገድ "ማታም ሆነ ጠዋትም ሆነ አንድ ቀን" ብሏል (ዘፍ.1፥5)።

፻፴፬. ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንድ ዓመት ገደማ አእምሮየ ላይ የሚመላለስ ጥያቄ ነበር። ካፌ ላይ እየተዝናናን ከጓደኞቼ ጋር ኮከብህ ምንድን ነው። የእናትህ ስም የአንተ ስም ከዚያ በኋላ ስለ ባሕሪ ስለወደፊት ሕይወት ስለ የምትሞትበት ቀን እንዲሁም ብዙ አሉኝ። ከዚህ በኋላ በጭንቀት እና በድብርት ነው ያለሁት። ይህ ነገር ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ አንጻር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ የሰው ልጅ የሚሞትበትን ቀን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህ ኮከብ እንቆጥራለን፣ የምትምትበት ቀን በዚህ ቀን ነው እያሉ በውሸት አስጨንቀውሃል። ሲጀምር ኮከብ ቆጣሪነት በቤተክርስቲያን የሚከለከል ክፉ ሥራ ነው። "ኮከብ ቆጣሪ አትሁን" እንዲል (ሃይ.አበ.125፥4)።

፻፴፭. በዕለተ ሰንበት ተአምሯን የሚያነበው ካህን ልብሰ ተክህኖ እንደለበሰ አይደለም ወይ? በብዙ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ልብሰ ተክህኖ ሳይለብሱ ያነባሉና።

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተጻፈ ሥርዓት አላውቅም። ስለዚህ የዚህን ጥያቄ መልስ አላውቀውም።

፻፴፮. ሰው በተለያየ ነገር ይሞታልና እግዚአብሔር ከቆረጠለት ቀን ማምለጥ ይቻለዋል ወይ? ቀኔ ካልሆነ አልሞትም ብሎ አለመጠንቀቅስ ተገቢ ነው ወይ? በጥንቃቄ መዳንስ አለ ወይ?

መልስ፦ የሰው ልጅ ንስሓ ሳይገባ እንዳይሞት መጠንቀቅ ይገባዋል። የሚሞትበት ቀን መቼ እንደሆነና በምን ምክንያት እንደሚሞትም ስለማያውቅ ሁልጊዜም ተዘጋጅቶ መኖር ይገባዋል። የሰው ልጅ ተጠንቅቆ በመኖር ሳይሞት መቅረት አይችልም። እንደገና

ደግሞ ቀኔ ካልሆነ አልሞትም ብሎ ያለጥንቃቄ መኖርም አይገባውም፡፡ አንዳንዱ ገደል ወድቆ፣ መብራት ይዞ ወይም በመሳሰለ መንገድ ቢሞት ራሱን ገድሏልና ሁለተኛ ሞት ይጠብቀዋል፡፡ የሞት ቀን (የሥጋ ከነፍስ መለየት) በምንም ምክንያት ይሁን በእግዚአብሔር የተወሰነ ነው፡፡ በምንም ምክንያት ልንሞት ስለምንችል ሁልጊዜም ንስሓ ገብተን፣ ምግባር ትሩፋት ሠርተን፣ ሥጋውን ደሙን እየተቀበልን መኖር አለብን፡፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ለእግዚአብሔር እንተውለት፡፡ ከእኛ የሚጠበቀው ሥራ ላይ እናተኩር፡፡

፫፻፱. ከሥነ-ፍጥረት ጋር የሚገናኝ የሆነ ጽሑፍ እያነበብኩ በተደጋጋሚ 42 ቁጥርን ይጠቅሳል፡፡ 42 ቁጥር (መስፈሪያ) በሥነ-ፍጥረትና በጸሎት ውስጥ የተለየ ምስጢር ይኖረው ይሆን? ምንአልባትም ሳይንሱ Resonance (ንዝረት) ከሚለው ጋር የሚገናኝ፡፡ የማውቀው ስለሌለ ያየሁት ሁሉ ምስጢር እየሆነብኝ ተቸግሬ ነው፡፡ ያገኘሁትን ጽሑፍ እውነታውን እረዳ ዘንድ የእርስዎ መልስ በእጅጉ ያስፈልገኛል፡፡

መልስ፦ የቁጥር አምልኮ ቢቀር መልካም ነው፡፡ ቁጥሮች ነገሮችን ለመቁጠር ያገለግላሉ፡፡ ከዚያ የዘለለ ትርጉም እየሰጠን ራሳችንን ባናስጨንቅ መልካም ነው፡፡ 42 ቁጥር የተለየ ምሥጢር የለውም፡፡ በ43 እና በ44 መካከል በእኩል ርቀት የሚገኝ ቁጥር ነው፡፡ ሌላ ማወሳሰብ አይገባም፡፡ ልዩ ልዩ ክሥተቶችን ለመግለጽ ልዩ ልዩ ቁጥሮችን ልንጠቀም እንችል ይሆናል፡፡ ቁጥሩ ክሥተቱን ለማብራሪያነት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል እንጂ፡፡ ቁጥሩ ክሥተቱን አይፈጥረውም፡፡ ስለዚህ ራሳችንን ምሥጢር ባልሆነ ምሥጢር ባናስጨንቅ ባይ ነኝ፡፡ አንዳንዱኮ የ1000 ሰዎች ዝርዝር ላይ 666ኛ ሆኖ ሲያገኘው የሚፈራ አለ፡፡ የእርሱን ጉዳይ ከሐሳዊ መሢሕ አገናኝቶ ይጨነቃል፡፡ ከእንዲህ ዓይነት ተራ ነገር ብንወጣ መልካም ነው፡፡

፫፲. በተአምረ ማርያም ሰው ሁሉ እመቤታችን ለማመስገን ተፈጠረ የሚለው ቃል ሰው የእግዚአብሔር ስሙን ለመቀድስ ክብሩን ለመውረስ ተፈጠረ ከሚለው ጋር አይጋጭም ወይ? የእግዚአብሔር ክብሩን መውረስ ሲባል ክብሩን ሰው መውሰድ ይችላል ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ አገላለጽ በወንጌል "ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይለኛል" ከሚለው ጋር ይመሳሰላል (ሉቃ.1፥48)፡፡ ፍጥረታት ሁሉ ጌታቸውን እግዚአብሔርን በሥጋ ወልዳላቸዋለችና ድንግል ማርያምን ያመሰግኗታል፡፡ ይህም ብዙውን ሁሉ ማለት መጽሐፋዊ ልማድ ስለሆነ የተነገረ ነው እንጂ እንኳን እርሷን እግዚአብሔርንም የማያመሰግኑ ፍጥረታት አሉ፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ሰዎችና ሰይጣናት እግዚአብሔርን አያመሰግኑም፡፡ ብዙዎች ግን እግዚአብሔርን በባሕርዩ እንደሚያመሰግኑ ሁሉ ድንግል ማርያምን በጸጋ ያመሰግኗታልና ሰው ሁሉ እመቤታችንን ለማመስገን ተፈጠረ አለ፡፡

**፻፶፮. ይዌድስዋ መላእክት ከሚለው ጸሎት መጨረሻው ላይ ለፍርድ በሚመጣ ጊዜ ከመጥምቁ ዮሐንስ እና ከሰማዕቱ እስጢፋኖስ ጋር ያቆመን ዘንድ ይላል። ከብዙ ቅዱሳን መካከል እነዚህ ሁለቱ ቅዱሳን የተጠሩበት ምክንያት ልዩ ምስጢር ይኖራቸው ይሆን?**

መልስ፦ ለጊዜው ይህንን ጸሎት ያዘጋጀው ሰው ሁለቱን ቅዱሳን ጠቅሷል። እንዲህ ዓይነት አጠቃቀስ በትርጓሜ ነሣሣለትና ዘምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን ብሏል ይባላል። ሁሉንም ቅዱሳን መጥቀስ ባይችል ሁለቱን ጠቅሶ ከሁሉም ቅዱሳን ጋር ብሎ ሁሉንም ጠቀሰ።

**፻፶፯. መልክአ ኢየሱስ ለኵርናዕከ ላይ ድኅረ ተፈጸመ ሱባኤ ሰንበታት ስሳ ይላል። ሰንበታት ስሳ ምንድን ናቸው?**

መልስ፦ ይህ ትንቢተ ዳንኤል ላይ ከተገለጸው ታሪክ የተወሰደ ድርሰት ነው (ዳን.9፥25)። ሰንበት የሚባለው በዳንኤል አቆጣጠር ሰባቱ ዓመት ነው። ስልሳ በሰባት ሲባዛ= 420 ይሆናል። ትንቢት 62 ሁለት ይላል። ደራሲው የተረፈ ትቶ ስልሳ ብሏል። ስለዚህ 434 ይሆናል ማለት ነው። ይህም ለዳንኤል ይህን ትንቢት ከተናገረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ስቅለት ያለውን ዘመን የሚያመለክት ነው። ድኅረ ተፈጸመ ሱባኤ ሰንበታት ስሳ በምጽአትከ ተንትመ አበሳ ማለት ሰው ሆኖ መስቀል ላይ ተሰቅሎ መርገምን ማጥፋቱን ያመለክታል። ምጽአትከ ያለው ሰው መሆኑን ነው።

**፻፶፰. አንድ ካህን ሚስት ካገባ በኋላ ሚስቱ ለሥራ ብላ ዓረብ ሀገራት ደርሳ ብትመጣ ካህኑ በክህነቱ መቀጠል ይችላል?**

መልስ፦ አረብ ሀገር መሄድኮ ምንም በደል የለውም። ስለዚህ አረብ ሀገር መሄድ ከክህነት መፍረስ ጋር አይገናኝም። እዚያ መሄድ ክህነትን የሚያስፈርስ ቢሆን ኖሮኮ የዚያና የአካባቢው ሊቀ ጳጳስ ክህነታቸው ይፈርስ ነበር።

**፻፶፱. የአሳማ ሥጋ ይበላል ወይስ አይበላም?**

መልስ፦ መጽሐፈ ዲድስቅልያ ላይ "የእሪያዎች ሥጋ ንጹሕ ነው የሚሉ አሉ። ነገር ግን ርኩስ ነው እንጂ ንጹሕ አይደለም" ይላል (ዲድስ.32፥46)። በዚህም ምክንያት አሳማ አይበላም የሚሉ አሉ። የምግብ ጉዳይ ቀኖናዊ ስለሆነ ከዘመን ዘመን ይለዋወጣል። በብሉይ የተከለከሉ በሐዲስ የተፈቀዱ አሉ። በሐዋርያት ዘመን ተከልክለው የኋላ ሊቃውንት የፈቀዷቸው አሉ። አሳማ ከዚህ ይመደባል። ሐዋርያት በዘመናቸው እንዳይበላ ሥርዓት ሠርተው ነበር። ሠለስቱ ምእት ደግሞ የቅዱስ ጳውሎስን ቃል ጠቅሰው ከደም፣ ለጣዖት ከታረደ፣ ሞቶ ካደረ ውጭ መብላት እንደሚቻል በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ላይ ገልጸዋል። መጽሐፈ ሐዊ ባህል 14 ላይም ይህንኑ አጠንክሮ ተናግሯል። ሥርዓት ከዘመን ዘመን ስለሚለወጥ የዘመኑን መያዝ ነው።

፻፶፩. የሥላሴ ምስጢር ሦስት አካላት ግን አንድ አምላክ የሚለው ትምህርት በሰው አእምሮ እንዴት ሊረዳ ይችላል?

መልስ፦ እንኳን ምሥጢረ ሥላሴ ከፍጥረታት እንኳን ከእኛ መረዳት በላይ የሆነ ብዙ ነገር አለ። ፈጣሪን በአእምሯችን ልክ ለመስፋት መጣር ራሱ ደካማነት ነው። በእኛ አእምሮ ልክ ተወስኖ የሚታወቅ ከሆነ ግን ይህ ራሱ አምላክ አይደለም። ሦስት በምልአት ያሉ አካላት አሉ። እነዚህ አካላት በከዊን ተገንዘብ አንድ ፈቃድ፣ አንድ ሥልጣን ስላላቸው አንድ መለኮት ይባላሉ። ከዚህ ከፍ ብለን አእምሯችን ሊደርስበት ያልቻለ ጉዳይ ካለ ወሰነ አእምሯችንን ተረድተን ማድነቅ ነው።

፻፶፪. ቅባት የሚባል እምነት አስተምህሮው ስሕተት መሆኑ ይታወቃል። አንዳንዶች በልጅነታቸው የተጠመቁ ቅባት ነን በሚሉት ሰዎች ነው። አሁን ወደ ተዋሕዶ ቢመለሱ እንደገና መጠመቅ ነው ወይስ እንዴት ነው?

መልስ፦ በመሠረቱ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ክህነትን የተቀበለ ሰው ክህነቱ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ነው። አንዳንዶች ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጳጳስ ክህነትን ተሹመው ቅባት ነን ካሉ ግን ስለካዱ ክህነታቸው ይሻራል። ስለዚህ በትክክል የቅባት እምነት ተከታይ ከሆነ ሰው መጠመቅ አይገባም። አሁን ወደ ተዋሕዶ ከተመለሱ ምን መደረግ አለበት ለሚለው በቅርቡ ሲኖዶስ እንዲሁ በንስሓ ብቻ ይመለሱ የሚል ውሳኔ ወስኖ አይቻለሁ። [በዚህ የሲኖዶስ ውሳኔ ቅሬታ አለኝ። እንደእኔ የቅባት አስተምህሮ ክሕደት እንደመሆኑ የመጀመሪያ ጥምቀቱ አይቆጠርም ስለዚህ እንደገና መጠመቅ አለበት የሚል ሐሳብ አለኝ]። እንግዲህ ሲኖዶስ ከወሰነ ግን ፍዳው በራሱ ይሁንበት። ምእመናን ባለመጠራጠር በተባለው መልኩ ማስኬድ ይችላሉ።

፻፶፫. ካህን ቀድሶ ከወጣ በኋላ የለበሰውን ነጠላ ወይም ጋቢ ጥሎ መሄድ ይችላል?

መልስ፦ ለዚህ የተጻፈ መጽሐፋዊ ማስረጃ አላገኘሁም አላውቀውም። መጽሐፈ ቅዳሴ ትርጓሜ ላይ ከቍርባን በኋላ ከልብስ መራቆት አይገባም ይላል። ከዚህ የተጠቀሰው ልብስ ነጠላ ይሁን ወይም ደግሞ ሲቀድስም ያላወለቀውን ልብሱን የትኛውን እንደሆነ አልተገለጸም።

፻፶፬. እግዚአብሔር ለምን ክፉ ነገር እንዲኖር ፈቀደ? ሁሉን ቻይ ከሆነ ሰይጣንና ክፋት በዓለም ላይ እንዲሰለጥኑ ለምን ፈቀደ?

መልስ፦ እግዚአብሔር ክፉ ነገር እንዲኖር አልፈቀደም። ክፉ ነገርን በራሳችን ፈቃድ የፈጠርነው እኛ ሰዎችና ሰይጣን ነን። በነገራችን ላይ ክፋት ራሱን ችሎ ህልውና ያለው ፍጥረት አይደለም። ክፋት የተባለ የሰዎች አለመታዘዝ ነው። የሰዎች አለመታዘዝ ደግሞ ራሳቸው የፈጠሩት ነው። ክፋትንና ሰይጣንን በዓለም ላይ ፈቅደን ያስለጠንናቸው

እኛ ሰዎች ነን። እግዚአብሔር ደግሞ ነጻ ፈቃድ ስለሰጠን ነጻ ፈቃዳችንን ሳይጋፋ ዝም አለን። ለምን ዝም አለን ከተባለ የነጻነት አምላክ ስለሆነ ነው።

**፻፶፱. በኢያሱ የቆመችው ፀሐይ? ኢያሱ ፀሐይ እንድትቆም ሲያዝዝ መሬት መሽከርከር አቆመች ማለት ነው? ይህ በምድር የስበት ኃይል ላይ ምንም ችግር አልፈጠረም?**

መልስ፦ የፀሐይ መቆም እኛ ከለመድነው የተፈጥሮ ሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ስለተደረገ ተአምር እንለዋለን። እንዴት ሆነ ከተባለ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ስለሚችል ነው። እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገር ሲያደርግ ያለምንም ችግር ነው።

**፻፷. ዮናስ በዓሣ ሆድ ወስጥ እንዴት ሦስት ቀን ኖረ? ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ አንድ ሰው በትልቅ ዓሣ ሆድ ውስጥ ያለ አየርና በጨጓራ አሲድ ሳይጎዳ እንዴት ሊቆይ ይችላል?**

መልስ፦ በሳይንስ ይህ ነገር አይፈጸምም ተብሎ ሊነገር ይችል ይሆናል። በእርግጥ ሳይንስ ከድንገት አንድ ሁለት ሰዎች በዚህ መልኩ ድነው ቢወጡ እንኳ ከሚልዮን አንድ ሊደረግ ይችላል ብሎም የመደረጉን ምክንያት ሳይገልጽ ማምለጫ ሊያዘጋጅ ይችል ይሆናል። ዙሮ ዙሮ የፍጥረታት ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ይህችን ዓለም ከምንም እንደፈጠራት ሁሉ ማናቸውንም ፍጥረት ለእርሱ ዓላማ መጠቀምና ማናቸውንም ነገር ሊያደርግበት ሥልጣን አለው። ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰው ጉዳይ በሳይንሱ ባይቻል እንኳ ለእግዚአብሔር ግን የሚሳነው ነገር ስለሌለ ይቻላል ተችሏልም።

**፻፷፩. አንድ ካህን ለቤተሰቦቹ ንስሓ አባት መሆን ይችላል ወይስ አይችልም?**

መልስ፦ ይችላል። የንስሓ አባት አባትነት የክህነት ነው። የካህን ክህነቱ ደግሞ ለሁሉ ያገለግላል እንጂ ከቤተሰቦቹ ውጭ ላሉት ብቻ የሚያገለግል አይደለም። ነገር ግን በነጻነት ንስሓ ለመግባትና ላለመተፋፈር ብዙ ጊዜ ሌላ ካህንን ንስሓ አባት ማድረግ የተለመደ ነው።

**፻፷፪. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የሚባለው ለምንድን ነው?**

መልስ፦ ፓትርያርክ የሚሆን ሰው በተለየ የአክሱም ሀገረ ስብከትን ጳጳስነት ደርቦ ስለሚይዝና በተጨማሪም የደብረ ሊባኖስን የእጨጌነት ሥልጣን የሚይዝ ስለሆነ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ይባላል።

**፻፷፫. የኢትዮጵያ ቅዱሳኖች ግልጽ ቁጥር ይታወቃል?**

መልስ፦ የቅዱሳንን ቁጥር የሚያውቀው ራሱ እግዚአብሔር ነው። አንዳንድ ቅዱሳን ዜናቸው፣ ገድላቸው ተጽፎ ሲታወቁ ብዙ ቅዱሳን ግን በዋሻ በፍሩክታ ራሳቸውን

ደብቀው ኖረው በዚያው ከእግዚአብሔር ውጭ ማንም ሳያውቃቸው ያርፋሉ። ስለዚህ ብዛታቸው ይህንን ያህል ነው ተብሎ አይገለጽም። ራሱ እግዚአብሔር ያውቃቸዋል እንጂ።

**፻፳፬. ቤተክርስቲያን በምሄድበት ጊዜ ሐሳቤ ወዴሌላ እየሄደ አስቸገረኝ። ምን ላድርግ?**

መልስ፦ ይህ የብዙዎቻችን ፈተና ነው። ይህም የሚመነጭ ከእግዚአብሔር ቤት ይልቅ ለኀላፊዋ ዓለም የሰጠነው ትኵረት ከፍተኛ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ሐሳባችን ወደሌላ እንዳይሄድ ከዓለሙ ሁሉ ምርጥ ከሆነችው ቦታ እንዳለን ማስታዎስ፣ ከፈጣሪያችን ጋር እንደምንነጋገር ልብ ማድረግ ነው። ይህ የጓጓንለት ዓለም ሁሉ ኀላፊ እንደሆነ ማስተዋል። አንድ ቀን በሞት ይህንን ዓለም እስከመጨረሻው እንደምንሰናበተው ማሰብ ነው።

**፻፳፭. ክርስትና በሚነሣበት ወቅት ሰዎች ለታቦት ይሰጣሉ። በዚህ ጊዜ ዲያቆናት ቤተክርስቲያንን ወክለው ያነሣሉ። ይህ ተገቢ ነው?**

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 3 ላይ እንደተገለጸው ሴቶች ሴቶችን፣ ወንዶች ወንዶችን ክርስትና ያነሣሉ። ነገር ግን ልጁን ክርስትና የሚያነሣ ሰው ከጠፋ ዲያቆናት ቤተክርስቲያንን ወክለው ልጁ ክርስትና እንዲነሣ ያደርጉታል። የክርስትና መሠረታዊ ዓላማ ልጁን ማስተማር ስለሆነ ከዚያ በኋላ ልጁን ማስተማር የሁሉም ካህናት ኀላፊነት ይሆናል። ክርስትና የሚያነሣ እያለ ልጄን ለታቦት ሰጥቻለሁ እያሉ ክርስትናን ሌሎች እንዳያነሡት ማድረግ ግን አይገባም።

**፻፳፮. አብ ያለ ወልድ ቃልነት መናገር አይችልም። ወልድ ያለ አብ ልብነት ማሰብ አይችልም። እንዲሁም አብና ወልድ ያለ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስነት መኖር አይችሉም እንላለን። እና እንዲህ ስንል እነዚህ ሦስቱ አካላት የማይችሉት ነገር አለ አያስብልም?**

መልስ፦ ይህ ጥያቄና ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም የሚለው አባባል የሚተረጎመው በፍጡራን ላይ ከፍጡራን አንጻር ነው እንጂ ከራሱ ባሕርይ ጋር አይደለም። ለምሳሌ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ሁሉን ይችላል የሚለውን ሐሳብ ይዘን እግዚአብሔር አለመኖር ይችላል ወይ ብንባል መልሳችን አይችልም የሚል ይሆናል። ታዲያ የሚሳነው ነገር አለ ማለት አይደለም ወይ ከተባለ የሚሳነው ነገር የለም የተባለ በፍጡራን ላይ እንጂ በራሱ ላይ አይደለም የሚል መልስ አለን። እግዚአብሔር አለመኖር አይችልም። ምክንያቱም መኖር የባሕርዩ ነውና (ዘፀ.3፥14)። እግዚአብሔር መለወጥ አይችልም። ምክንያቱም አለመለወጥ የባሕርዩ ነውና (ሚል.3፥6)። ለእግዚአብሔር ያለው ነገር ሁሉ የባሕርይ ስለሆነ በዘመን ብዛት ወይም በማናቸውም ምክንያት አይለወጥም። ሦስቱ አካላት የማይችሉት ነገር የለም። አብ ቃልነትን ከወልድ እስትንፋስነትን ከመንፈስ ቅዱስ ገንዘብ ማድረጉ ከወልድ ከመንፈስ

ቅዱስ ጋር አንድ መሆኑን ይገልጽልናል እንጂ አለመቻሉን አይገልጽልንም። ሲጀምር አለመቻል ለሦስቱ አካላት መነገር አይችልም። ሳይችሉ የኖሩበት ዘመን ወይም ሳይችሉ የሚኖሩበት ቅጽበት አይኖርምና።

**፻፷፪. ቀሲስ ዶ/ር መብራቱ ኪሮስ ያጠኑት አኮቴተ ቁርባን በሚለው መጽሐፋቸው ላይ የብዙዎች ፍሬ ቅዳሴ ደራሲዎች የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንደሆኑ ከነ ማስረጀው ባቀረቡት መሠረት በእኔ እይታ በጣም አሳምኖኛል። በሊቃውንት ትርጓሜ ቤት ምን ይባላል ስለ ደራሲዎች?**

መልስ፦ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትርጓሜ ቅዳሴ ማርያምን አባ ሕርያቆስ፣ ሌሎችን ቅዳሴዎች ደግሞ በዘርፉ የተጠቀሱት ሊቃውንት እንደጻፉት ይነገራል። ይህም ማለት ቅዳሴ ቄርሎስን ቄርሎስ፣ ቅዳሴ ዮሐንስን ዮሐንስ፣ ቅዳሴ ባስልዮስን ባስልዮስ፣...ወዘተ። ፕሮፌሰር ቀሲስ መብራቱ ደግሞ ታሪክን ጠቅሰው እንዲህም ይባላል ማለታቸው የሚያስመሰግን ሥራ ነው። ታሪክ አንድ ጊዜ ተጠንቶ የሚቆም ሳይሆን በየዘመናቱ ሊጠና በማስረጃዎች መሠረትም ሊሻሻል የሚችል ነውና። ለምሳሌ ሃይማኖተ አበው ምዕራፍ ሰባት ሃይማኖተ አበው ዘሄሬኔዎስ ይባላል። እና መተርጉማን የዚህ የሄሬኔዎስ ዜና ገድሉ አልመጣልንም ብለው ጽፈዋል። ሌላ ሰው ማስረጃ አግኝቶ ቢጽፈው ይመሰገናል እንጂ አይናቅም። ታሪካዊ ሁኔታዎችን መተርጕማን በመጣላቸው መረጃ መሠረት ይጽፋሉ። አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ መረጃዎች ሲገጥማቸው ሁለቱንም ሐሳብ ጽፈው እነርሱ ያመኑበትን ገልጸው ያልፋሉ። ለምሳሌ ስለሰብአ ሰገል ሲገልጹ አንድም ጌታ በተወለደበት ቀን ደርሰዋል፣ አንድም ጌታ በተወለደ በሁለት ዓመቱ ደርሰዋል ብለው ጽፈዋል። ይህንን የመሰለ በትርጓሜ ብዙ አለ።

**፻፷፫. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ንጽሕት ሆና የተመረጠችው ከሐና ማሕፀን ወይስ ከሔዋን ለምን? ማለት ንጹሕ ሁና እየተቀዳች መጣች ወይስ ከሐና ላይ ንጹሕ ሆነች?**

መልስ፦ እየተቀዳች መጣች የሚለው አስተምህሮ ተቀባይነት የለውም። የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ህልውና የሚጀምር ከኢያቄም ዘርና ከሐና ደም ስትከፈል ጀምሮ ነው። ስለዚህ ከሐና ማሕፀን ጀምሮ ንጽሕት ናት እንላለን እንጂ ውሃ በቦይ እንደሚሄድ ከአዳም ጀምሮ ስትቀዳ መጥታለች የሚለው አስተያየት ተቀባይነት የለውም። ቅዱስ ያሬድ ማርያምሰ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሡ ለአዳም ከመ ባሕርይ ጸዓዳ ይል የለምን ካሉ ከአዳም ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚነሡ ሰዎች በባሕርይ አንድ ስለሆኑ ከአዳም ባሕርይ የምትወለድ ንጽሕት ድንግል ማርያም እንደምትወለድ ያሳውቃል እንጂ ከአዳም አካል ውስጥ ንጹሕና ንጹሕ ያልሆነ ሁለት አካል ነበረ ማለት አይደለም። እሾኻም ከሆነ ጽጌረዳ እሾህ የሌላት ለዓይን ደስ የምታሰኝ የጽጌረዳ አበባ እንድትገኝ በመርገም ከነበሩ ሰዎች መርገም የሌለባት ድንግል ማርያም ተወለደች ማለት ነው።

፻፳፱. አንድ ሰው በሌላ እምነት የነበረ፣ ንጽሕና /ድንግልና/ የሌለው ቢሆንና ወደ እኛ ሃይማኖት ንስሓ ገብቶ ቢመለስ እና በሥርዓተ ተክሊል ለማግባት ቢፈልግ ይቻላል ወይስ አይቻልም?

መልስ፦ አይችልም። ምክንያቱም ተክሊል የሚፈጸምለት የሥጋ ድንግልና ላለው እንጂ የሥጋ ድንግልና ለሌለው አይደለምና (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24)።

፻፴. አንድ ዲያቆን ለሌላ የታጨች ወይም የተዳረች ነገር ግን ምንም ዓይነት ግንኙነት ያላደረገች ሴትን ማግባት አይቻልም ይባላልና እንዴት ነው? በድንግልና ለሚያገቡ ምዕመናንስ ያቺን (የተዳረች) በተክሊል ማግባት ይቻላል?

መልስ፦ አንዲት ሴት ታጭታ ስትኖር በተለያዩ ምክንያቶች እጮኝነቱ ቢፈርስ እና እንደገና ሌላ ሰው አጭቶ ሊያገባት ቢፈልግ አጭቶ ማግባት ይችላል። በተክሊል አግብታ የነበረችን ሴት ግን ምንም እንኳ ግንኙነት ሳታደርግ ብትፋታ ተክሊሉ ከጋብቻ ስለሚቆጠር ዲያቆን ሊያገባት አይገባም። ያለተክሊል ከነበረና ምንም ግንኙነት ካልነበረ ግን ድሮም ከጋብቻ ስለማይቆጠር በተክሊል ማግባት ትችላለች።

፻፴፩. ሥዕለ አድኅኖ ሲሣል ራሱን የቻለ ትርጉም ይሰጠናል። ይሁን እንጅ የእመቤታችን ሥዕለ አድኅኖ ልጇን ታቅፋ የምናየው አብዛኛው የጌታችን አክሊል የተቀዳጀለት ነው። አክሊል መቀዳጀቱ አያሳንሰውም?

መልስ፦ አያሳንሰውም። የማይታዩ ሥላሴን ለሰው ማስተማሪያ በሚታይ ሥዕል ማቅረባችን ለማስተማሪያነት እስከሆነ ድረስ ምንም ችግር አይፈጥርም። ሥዕለ ክርስቶስን በተመለከተም አንዳንድ ሠዓልያን አክሊል አቀዳጅተው ሲሥሉት ሌሎቹ ደግሞ ያለአክሊል ይሥሉታል። በሁለቱም በኩል ለማስተማር እስከሆነ ድረስ በራሱ ችግር የለውም። አክሊል አለመኖሩና ሌሎች ቅዱሳን ላይ አክሊል መኖሩ አክሊልን ክብርን የሚሰጣቸው አምላክ እንዳለ ለማሳወቅ ነው። አክሊል መኖሩ ደግሞ ለምእመናን የሚሰጣቸው የጸጋ ክብር የእርሱ የባሕርይ መሆኑን ይገልጻል። በራእየ ዮሐንስ "ወመጽአት ደመና ብርህት ወውስተ ይእቲ ደመና ይነብር ወልደ እጓለ እመሕያው ወአክሊለ ወርቅ ዲበ ርእሱ፤ እነሆም ነጭ ደመና፥ በደመናውም ላይ የሰውን ልጅ የሚመስል ተቀምጧል። በራሱም ላይ የወርቅ አክሊል ነበረው" ይላል (ራእ.14፥14)። ክርስቶስ ለዮሐንስ የወርቅ አክሊል በራሱ አድርጎ ተገልጾለታል።

፻፴፪. ቤተክርስቲያን ዶግማ ቀኖና ሥርዓት አላት። ቢሆንም ስድስቱ አኃት አብያተ ክርስቲያን የቀኖና የሥርዓት ልዩነት አላቸው። ልዩነቱ ከየት መጣ?

መልስ፦ ቀኖና እንደ ሀገሩ ነባራዊ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል። ቀኖናን የየሀገሩ ሲኖዶስ ከሀገሩ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሊያሻሽለው፣ ሊለውጠው፣ ሊቀንሰው፣ ሊጨምረው

ይችላል። ልዩነቱ የመጣው ካለመገናኘት፣ ካለመነጋገር፣ የየሀገሩ ሁኔታ የተለያየ ስለሆነና በመሳሰለው ምክንያት ነው።

**፻፹፫. ከቤተክርስቲያን የተወገዘ ግለሰብ/ቡድን ጋር በአንድ መኖር፣ መሥራት፣ መጸለይ፣ መዓድ መብላት ይቻላል?**

መልስ፡- ከተወገዘ ሰው ጋር በአንድ መጸለይ አይገባም። ክሕደቱ ተጽእኖ የማያደርስበት ከሆነ በአንድ ቤት መኖር፣ በአንድ ላይ መሥራት ይቻላል። በምግቡ ላይ ስንጸልይበት የማይቆጣ ከሆነ በራሳችን ጸሎት ጸልየን ልንበላ እንችላለን። እርሱም ስመ ጣዖትን የሚጠራ ከሆነ ግን የየራሳችንን መዓድ ይዘን መብላት ነው።

**፻፹፬. ሴቶች እርድ ማረድ ይችላሉ?**

መልስ፡- በሀገራችን ባህል ብዙ ጊዜ ወንድ ያርዳል። በሃይማኖት ሴቶች ቢያርዱ ኃጢአትነት ይኑረው ወይም አይኑረው ግን እስካሁን መጽሐፍ ላይ አላገኘሁም አላውቀውም።

**፻፹፭. ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን የደረሱ ወይም ዕድሜያቸው ዐሥራ አምስትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሴት ወይም ወንድ ንስሐ ገብተው ሁልጊዜ ቁርባን መቁረብ ይችላሉ?**

መልስ፡- አዎ ይችላሉ። ለመቊረብ የዕድሜ ገደብ የለም። በእርግጥ ገጠር አካባቢ አንዳንድ ካህናት ባለማወቅ አናስቆርብም ሊሉ ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን አለማወቅ እንጂ ማንኛውም ክርስቲያን ንስሓ እየገባ በየጊዜው መቊረብ ይችላል።

**፻፹፮. አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ስማቸው፤ ልብ ቃል እስትንፋስ ኩነታዊ ስማቸው መሆኑ ይታወቃል።ነገር ግን ለምሳሌ የአብ ምልዐተ አካሉ ምልዐተ ልብ፤ ልብ ደግሞ ስንል ራሱ ምልዐተ አካል ይባላልን?**

መልስ፡- አዎ ይባላል። ሲባል ግን አረዳዱን በትክክል መለየት ያስፈልጋል። ጉዳዩን ለማስረዳት ምንም እንኳ ሕፀፁ ቢጎላም በምሳሌ ዘየሐፅፅ ልግለጸው። ለምሳሌ ማር አካል አለው፣ ጣዕም አለው፣ መልክ አለው። የማር አካል የሚባለው በመዳሰስ የሚታወቅ፣ በመታየት የሚወሰን ነው። መልክ የምንለው በማየት ብቻ የምንለየው ነው። ጣዕም የሚባለው ደግሞ በምላስ የሚታወቀው ነው። እነዚህ ነገሮች አንዱ ከአንዱ ለየብቻ ተለይተው አይገኙም። ማርን ጣፋጭ ነው ስንለው ምልአተ አካሉ ጣፋጭ መሆኑን ያመለክታል። ጣዕምና አካል ልዩ ልዩ መሆናቸውን ግን ሳንዘነጋ ነው። አካለ ወልድ ምልአተ አካሉ ቃል ነው ስንል ከዊኑ ቃል መሆኑን ያመለክታል እንጂ ከዊኑ አካል ነው ማለታችን አይደለም። ከዊን አካላዊ ነው እንጂ አካል አይደለምና።

**፻፹፯. አንዲት ሴት ነፍሰ ጡር ከሆነች በኋላ ከስንተኛው ወር ጀምሮ ነው ግንኙነት ማቆም ያለባት?**

መልስ፦ ተለይቶ የተቀመጠ ወር አላገኘሁም። ነገር ግን ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ትርጓሜ ላይ ሆዷ ከሰፋ፣ ፅንሷ ከገፋ በኋላ ግንኙነት እንደማይገባ ተገልጿል። ከዚህ ሐተታ በመነሣት ከሦስት ወር በኋላ አይቻልም ማለት ነው።

፻፸፫. በዝሙት ሐሳብ የሚፈተን ሰው ከጸሎት ሌላ ሐሳቡን ሊያሸንፍበት የሚችል መንገድ አለ ወይ? ሐሳቡስ የራሱ ወይስ ከሰይጣን መሆኑ እንዴት ይታወቃል? ይህ ሰው በዝሙት ብቻ እንጂ ደግ ልብ ያለው ከሆነ ቤተክርስቲያንን የሚወድ ከሆነ ለመዳን ይደርሳል?

መልስ፦ መጽሐፈ መነኰሳት አረጋዊ መንፈሳዊ ላይ ሰው የዝሙትን ፈተና ለማሸነፍ ውሃ አብዝቶ እንዳይጠጣ፣ ምግብ አብዝቶ እንዳይበላ፣ እንቅልፍ እንዲቀንስ ተነግሯል (ድርሳን 7)። መንፈስ ጸሪፍ የተባለ ሰይጣን ክፉ ክፉ ሐሳቦችን ወደ አእምሯችን እንደሚልቅና የእኛ ሐሳቦች መስለውን እንድንጨነቅ እንደሚያደርግ ተገልጿል (ድርሳን 8)። በዚህ ጊዜ ሐሳቡን ተቀብለን ወደ ገቢር ካደረስው ኃጢአት ይሆንብናል። አንድን ክፉ ሐሳብ እኛ ራሳችን እናመንጨው ወይንም ሰይጣነ ጸሪፍ ያመንጨው የምናውቀው በቅድስና ስንበቃ ነው። በየትኛውም መልኩ ይሁን ክፉ ሐሳብ ሲታሰበን ሐሳቡን ለማራቅ ምረረ ገሀነመ እሳትን፣ ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን፣ ስለእኛ ክርስቶስ በመስቀል መሰቀሉን በማሰብ ለማራቅ መታገል አለብን። ለመዳን ከዝሙት መራቅም ደግ ልብም ያስፈልጋል።

፻፸፬. ክርስቶስ ሞታችንን በሞቱ ሽሮልናል። ኃጢአት ብንሠራም አይኮንነንም። ምክንያቱም የደም ዋጋ የተከፈለልን ልጆቹ ስለሆንን የሚሉ አሉ። በዚህ ጉዳይ ምን ይላሉ?

መልስ፦ ሞታችንን በሞቱ ሽሮልናል ማለት በአዳም ምክንያት ከመጣብን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ አድኖናል፣ ሞተን ከመቅረት በትንሣኤው አድኖናል ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ኃጢአት ብንሠራ ግን በሠራነው ኃጢአት ምክንያት እንሞታለን እንጂ አንዴ ስለሞተልን አንኮነንም ማለት አይደለም። ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ ማለት ብቻ አያድንም። መልካም ሥራን መሥራትም ይገባል እንጂ (ማቴ.7፥21)። ማመን ያለሥራ እንደማይጠቅም ቅዱስ ያዕቆብ "ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" ብሎ ገልጾታልና (ያዕ.2፥26)።

፻፸፭. ሰው ኃጢአቱን ወይም የሠራውን በደል ለንስሓ አባቱ አንድም ሳይቀር መናዘዝ እንዳለበት እና የንስሓ አባቱ የሰጠውን ቀኖና በአግባቡ መጨረስ እንዳለበት በግሌ እስማማለሁ። ግን ከአንዳንድ ጓደኞች ጋር ስናወራ ለንስሓ አባት በደልን ስንናገር ተዘንግቶ የሚቀር ኃጢአት አለ። እናም ቊርባን ከተቀበሉ በኋላ ኃጢአቱን መናዘዝ ይቻላል?

መልስ፦ በተቻለን መጠን ያስታወስነውን ኃጢአት ሁሉ ለንስሓ አባታችን መንገር ይገባናል። የረሳነው ኃጢአት ካለ ደግሞ እግዚአብሔር ባወቀ ይቅር እንዲለን አስበን መቊረብ ይገባናል። ካህኑ በማወቅም ባለማወቅም የተሠራውን ኃጢአት እግዚአብሔር

ይቅር ይበላችሁ ማለቱ ስለዚህ ነው፡፡ ከቆረብን በኋላ ያስታወስነው በደል ካለ ደግሞ ይህንን ረስቼው ከቆረብኩ በኋላ አስታወስኩት ብሎ መንገር ነው፡፡

**፻፹፮. አንድ ሰው በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ዲያቆን ሆኖ አገልግሎት ሲያገለግል ከቆየ በኋላ ወደ ሌላ እምነት (ተሓድሶ) ቢሄድ፣ ከዓመታት በኋላ ደግሞ ቢመለስ፣ እንደገና ወደ ክህነት ማዕረግ መመለስ ይችላልን?**

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 46 ላይ "በፈቃዳቸውም ቢሆን በግድም ቢሆን ክደው በኋላ ወደ ሃይማኖታቸው የተመለሱ ሰዎች ቀድሞ ከነበራቸው መዓርግ ዝቅ ባለ መዓርግ ይኑሩ" ተብሏል፡፡ ይህም ማለት ቄስ ከነበረ ዝቅ ባለ መዓርግ በዲቁና ይኑር፣ ዲያቆን ከነበረ ከዲያቆን ባነሠ መዓርግ ይኑር ማለት ነው፡፡ በእሳት በስለት ሰዎች አስፈራርተዋቸው እምነታቸውን ቀይረው መከራው ሲያልፍ ንስሓ ቢገቡ እስከሰባት ዓመት ምንም የክህነት ሥራ አይሥሩ ተብሏል፡፡

**፻፹፯. በአንዳንድ አካባቢዎች ዘመድ ሲሞት የአንገት ማተብ ይወለቅና ፈትል ይደረጋል፡፡ ይህ ልክ ነው?**

መልስ፦ ማተብ በሀገራችን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ለመሆናችን ምልክት ነው፡፡ ይህን ምልክታችንን ደግሞ በኀዘን ጊዜም፣ በደስታ ጊዜም ልናወልቀው አይገባም፡፡ በማናቸውም ጊዜ ሃይማኖታችንን የምንመሰክርበት ስለሆነ ማውለቅ የለብንም፡፡

**፻፹፰. ባልና ሚስት በተክሊል ከተጋቡ በኋላ ከግንኙነት ለስንት ቀን መቆጠብ አለባቸው?**

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ትርጓሜ ላይ የተገለጸው ተክሊል ፈጽመው፣ ሥጋውን ደሙን ከተቀበሉ በኋላ ሙሽራይትም ወደ ቤተሰቦቿ፣ ሙሽራውም ወደ ቤተሰቦቹ ይሄዳል፡፡ ከዚያ ለአርባ ቀናት ያህል በሚመቻቸው ሰዓት ቤተክርስቲያን እየመጡ ይቆርባሉ፡፡ በአርባኛው ቀን ሰርግ ይደረጋል ይላል፡፡ ስለዚህ ግንኙነት ከዚያ በኋላ ነው፡፡ አሁን ግን ይህ ሥርዓት ሲፈጸም አይተን አናውቅም፡፡

**፻፹፱. እመቤታችን ከጌታችን ጋር በተሰደደችበት ጊዜ ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ካረፉባቸው ቦታዎች የረር በአታ፣ ጣና ቅዱስ ቂርቆስና የመሳሰሉት ቦታዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ጣና ደሴት ላይ የእመቤታችን የእግሯ አሻራ አለ፡፡ ቀደምት የቤተክርስቲያን የታሪክ ጸሐፊዎች ይህን ነገር ጽፈውታል? የቤተክርስቲያን አባቶችስ ይህን ነገር ተናግረዋል? ይህን ነገር አለመቀበልስ ይቻላል? መተቸት ሳይሆን ይሄ ነገር አላሳመነኝም ብሎ መናገር ይቻላል?**

መልስ፦ የየትኛውም ሀገር ታሪክ ምንጩ በሀገሩ ከነበሩ የመረጃ ምንጮች በመነሣት የተጻፈ ነው፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኢትዮጵያ መጥታ እንደነበር ከትውፊት በተጨማሪ በነገረ ማርያም መጽሐፍ፣ በድርሳናት፣ በገድላት ተጽፏል፡፡ የእኛን እውነት ለመቀበል የውጭ ጸሓፊ ይሁንታ አያስፈልግም፡፡ የገድል፣ የድርሳን

ጸሓፊዎችኮ የቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሓፊዎች ናቸው። እንዲህ ዓይነት ሐሳብ ውስጥ መግባት የባርነት ሥነ ልቡና ውጤት ነው። ከእንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ወጥተን የራሳችንን ታሪክ በእኛው ምንጭ ማረጋገጥ ይገባናል። አላሳመነኝም ብለን ለመጠራጠር የሚያበቃ ምንም በሌለበት ራሳችንን ባንጎዳ መልካም ነው።

፻፹፫. በበዓለ ኀምሳው ጊዜ አባቶች ካህናትን ግብረ ሰላም ማብላት/ መጋበዝ እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ለምዕመኑ የሚያስገኘው በረከት ምንድን ነው?

መልስ፦ በተአምረ ኢየሱስ ካህናትን ጠርቶ ማብላት ሰማያዊ ዋጋ እንዳለው፤ ኃጢአትን እንደሚያስተሠርይ ተገልጿል። "ብፁዓን እለ ያበውእዎሙ ለካህናትየ ውስተ አብያቲሆሙ አሐተ ዕለተ ለለኵሉ አርብዓ መዋዕል እስመ አነሂ እሠሪ ሎሙ ኃጢአቶሙ" እንዲል (ተአምረ ኢየሱስ)።

፻፹፬. ዮሐንስ ዘደማስቆ ስንክሳር ታኅሣሥ 8 በዘመኑ ብዙ ድርሳናትን የደረሰ እንዲሁም በዘመኑ ተነሥተው ስለነበሩ ለቅዱሳት ሥዕላት መስገድ አይገባም ያሉትን ከሓድያንን እንደተቃወመ እመቤታችንም እንደተገለጸችለት በመመዝገብ ቅዱስ ብሎ ይጠራዋል። ይህ ዮሐንስ ዘደማስቆ ኬልቄዶናዊ አይደለም እንዴ? እነ ቅዱስ ሳዊሮስን አታላይ እያለ ቅዱስ ዲዮስቆሮስን ክፉ እያለ የተናገረ አይደለም እንዴ? እንዴት በእኛ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ተባለ?

መልስ፦ በእርግጥ ስንክሳር ላይ ብዙ ታሪኮች ይኖራሉ። አንዳንድ ታሪኮች በቅርብ በተደረጉ የሲኖዶስ ጉባኤያት እንዲወጡ የተደረጉ አሉ። ብዙው የተጻፈው ቀድሞ በነበረው መረጃ ነው። ይህ መረጃ ደግሞ በልዩ ልዩ መረጃዎች እየተመሳከረ ምናልባት በተቃራኒው ሆኖ ሊገኝ ይችላል። የብዙ ቅዱሳንን ሙሉ ታሪክ የምናውቀው በምጽአት ነው። ስለዚህ ይህንን እውነታ ለራሱ ለእግዚአብሔር እንተውለት። እኛ ግን ከተጻፈልን መልካሙን ፍሬ እየወሰድን እንጠቀም እላለሁ።

፻፹፭. በመጽሐፈ ስንክሳር ስማቸው የገባ ነገር ግን ቅዱስ የማይባሉ አሉ እንዴ? ማለትም ስንክሳር ላይ መቀመጣቸው ለዝክረ ስም እንጂ የቅድስና ያልሆነ ማለቴ ነው። ለምሳሌ አሁን አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ጳጉሜን 3 የዕረፍቱ መታሰቢያ ይላል። ሌሎችም ነገሥታት አሉ በስንክሳር ስማቸው የተቀመጠ እነ አጼ ልብነ ድንግል አጼ በእደ ማርያም አጼ ዳዊት አጼ ናዖድ ወዘተ። እነዚህ ቅዱስ ሊባሉ አይችሉም?

መልስ፦ በእርግጥ ከላይ የተጠቀሱ ነገሥታት ለቤተክርስቲያን ያበረከቷቸው ልዩ ልዩ ነገሮች እንዳሉ በታሪኮቻቸው ተዘግቧል። ቤተክርስቲያንም ለእነዚያ አበርክቶዎች እውቅና በመስጠት መታሰቢያ ዕለታቸውን ትናገራለች። ቅዱሳን ናቸው ብላ የሠየመቻቸውን ደግሞ "ቅዱስ" የሚል ቅጽል ሰጥታ ታከብራቸዋለች። መታሰቢያቸው ብቻ የተጻፈ ቅድስናቸው ግን ያልተገለጹ ሰዎች በስንክሳር ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ነገሥታትም መታሰቢያቸው ተጻፈ እንጂ ቅዱስ ናቸው የሚል አላገኘሁም። የቅድስናን ጉዳይ ለጊዜው

በተጻፈልን ልክ ብቻ ብናስብ፣ ለፍጻሜው ደግሞ በምጽአት ሁሉን ስለምናውቅ ብዙ አያስጨንቅም። ከእኛ የሚጠበቀው ሁሉንም ማክበር ነው።

፻፹፰. አንድ ነፍሰ ጡር እናት ጾም መጾም አለባት? ካልጾመችስ ጾም እንደ ሻረች ይቆጠራል? ቀኖናስ ይሰጣታል? መጾም የለባትም ከተባለ ደግሞ ከወለደች ከስንት ቀን ወይም ወር በኋላ ነው ጾም መጀመር ያለባት?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 9 ላይ ጽኑ ደዌ ሳያመው ዓርብና ረቡዕን የማይጾም ካህን ቢኖር ከክህነቱ ይሻር፣ ጨዋ ቢሆን ከምእመናን ይለይ ይላል። "ጽኑ ደዌ" ያለበት ሰው ግን ከንስሓ አባቱ ጋር ተመካክሮ ላይጾም ይችል ይሆናል። የወለደች ሴትና ያረገዘች ሴትም የምትችል ከሆነ ጾም የበረከት ምንጭ ስለሆነ መጾም ይገባታል። ብዙ ደም ከፈሰሳትና ሰውነቷ የሚጎዳ ከሆነ ግን ንስሓ አባት ሁኔታውን አይቶ ሊፈቅድላት ይችላል።

፻፹፱. ካህናት ከሕማማት በኋላ መቼ ነው መስቀል ማሳለም የሚችሉት?

መልስ፦ በትውፊት ካህናት ቅዳሜ ለእሑድ በትንሣኤ ሌሊት ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ከተባለበት ጊዜ ጀምረው ያሳልማሉ።

፻፺. ከሲኦል የነበሩ ነፍሳት በዕለተ ዓርብ ነው ወይስ በዕለተ ትንሣኤ ነው ከሲኦል የወጡት?

መልስ፦ ነፍሳት ከሲኦል የወጡት በዕለተ ዓርብ ነው። ነገር ግን ከሲኦል ለመውጣታቸው መታሰቢያ በዓል ይሆን ዘንድ ደግሞ በትንሣኤ ማግሥት ሰኞ በማዕዶት ይታሰባሉ። "ፋሲካ ብሂል ማዕዶት ብሂል" እንዳለ ቅዱስ ያሬድ።

፻፺፩. በሰሙነ ሕማማት ጊዜ ማማተብ ይቻላል?

መልስ፦ አዎ ይቻላል። ምግብ ስንመገብ፣ ቤተክርስቲያን ስንገባ፣ ክፉ ነገር ሲያጋጥመን፣ በጠቅላላው በማናቸውም ሁኔታ ማማተብ ይፈቀዳል። ሥርዓተ ሰሙነ ሕማማት ማማተብን አይከለክልም። የሚከለክል ፍትሐትን፣ የካህናት መስቀል ማሳለምን፣ ክርስትና ማንሣትንና የመሳሰሉትን ነው።

፻፺፪. በዐቢይ ጾም ጊዜ የሚነግሡ ዓመታዊ ክብረ በዓላት መደረግ አለባቸው ወይ?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15 ትርጓሜ ላይ በዐቢይ ጾም መካከል ስለሚመጡ በዓላት ይናገራል። ሰኞና ማክሰኞ ከዋሉ ካለፈው ቅዳሜ ወይም እሑድ ይከበሩ፣ ኀሙስና ዓርብ ከዋሉ በሚመጣው ቅዳሜ ወይም እሑድ ይከበሩ ካለ በኋላ ረቡዕ ቢውል ተመካክረው በወደዱት ያድርጉት ተብሏል። ይህ ግን በሀገራችን እየተተገበረ አይደለም። ያው ዕለቱ በዋለበት ይከበራል።

፻፺፫. በዲያቆናት ጋብቻ ብዙውን ጊዜ የሚያገቡ ዲያቆናት ራሳቸው ሠራዒ ዲያቆን በመሆን ሲያገቡ ይስተዋላል፡፡ ሆኖም ግን አይፈቀድም የሚሉ መምህራንም አሉና እርስዎ ምን ይላሉ?

> መልስ፦ አንድን ነገር ይፈቀዳል ወይም አይፈቀድም ለማለት መለኪያ ሚዛን ያስፈልጋል፡፡ መለኪያ ሚዛን በሌለበት ሁለቱንም መናገር አይቻልም፡፡ ዲያቆን ሲያገባ ሠራዒ ዲያቆን ሆኖ አይቀድስ የሚልም የለም፣ ይቀድስ የሚልም የለም፡፡ አንዳንዶች አንድነታቸውን ለማጽናት ከሙሽሪት ጋር ይሁን የሚል አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ቅዳሴ የሚገባው ሥርዓተ ተክሊሉ ከተፈጸመ በኋላ ስለሆነ ችግር የለውም ይላሉ፡፡ ይህ መከራከሪያ መሆን የለበትም፡፡ እንደ ትልቅ ጉዳይ ታይቶ ክርክር የሚያስነሣ ከሆነ ደግሞ ሲኖዶስ በአንዱ ቢወስን መልካም ነው፡፡

፻፺፬. የሰንበት ትምህርት ቤት አባል ነኝ፡፡ ነገር ግን ከአባላት ውስጥ የፍቅር ጥያቄ ቀረበልኝ እና እዚህ ግንኙነት ውስጥ እንዳልገባ እኅትና ወንድም ማለት ነን ብየ አሰብኩኝ፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝና ግንኙነታችን እስከ ምን ድረስ እንደሆነ ቢነግሩኝ?

> መልስ፦ ታዲያ ከሰንበት ትምህርት ቤት ካላገባህ/ሽ ከየት ልታገባ/ቢ ነው?!! ሌላ ዝምድና ከሌላችሁ በስተቀር የአንድ የንስሓ አባት ልጆች፣ የአንድ ሰንበት ትምህርት ቤት አባላት፣ የአንድ መምህር ተማሪዎች መጋባት ትችላላችሁ፡፡

፻፺፭. የእንስሳት እርድ በሚፈጸምበት ጊዜ በአንዳንድ አካባቢ አንገታቸውን አርዶ ጨርሶ ቆርጦ መጣል አይፈቀድም፡፡ ችግሩ ምንድን ነው?

> መልስ፦ አላውቀውም፡፡

፻፺፮. በሥርዓተ ተክሊል ዙሪያ ከአንዳንድ ባለጌዎች ጋር ቤተሰብም ሳይቀር እየተጣላሁ ነው፡፡ ጉዳዩ በሥርዓተ ቁርባን የሚፈጸም ጋብቻ ነው፡፡ ልጁ ተክሊል አያደርግም እሷ ትችል ነበር፡፡ ከማሳቅቀው ልተወው ብላ ሁለቱም በቁርባን ይሁን ተባለ፡፡ ቀኑ ደረሰና ሁለት ቀን ሲቀረው የወር አበባዋ መጣ፡፡ በሞዴስ ትግባ አትግባ ይቻላል አይቻልም ብለው ጠየቁኝ፡፡ ከዘመኑ ጋር እንደ ቤተክርስቲያን ምን ቢሆን ይሻላል?

> መልስ፦ የወር አበባዋ ከመጣ የቊርባኑን ቀን ሌላ ጊዜ ማድረግ ነው፡፡ ከወር አበባዋ ሳትነጻ ሴትን ወደ ቤተክርስቲያን ያስገባና እንድትቆርብ ያደረገ ካህን ከክህነቱ ይሻር ተብሏልና (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24)፡፡

፻፺፯. ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ እያስተማረ እያለ ከስሙ ላይ ቅጽል ስም አልነበረውም፡፡ ነገር ግን ዛሬ የቤተክርስቲያን መምህራኖች የተለያየ ቅጽል ስም አላቸው ምሳሌ፦ ሊቀ ምሁራን፣ ሊቀ ሊቃውንት፣ ሊቀ ጠበብት፣ ርዕሰ ሊቃውንት፣ አራት አይና፣ ሊቀ መምህራን ወዘተ የመሳሰሉት ስም እንዴት ለእነሱ ሊጨመር ቻለ?

መልስ፦ በእርግጥ ከሐዋርያት በኋላ ለነበሩ ቅዱሳን ሊቃውንትም ከአገልግሎታቸው አንጻር ልዩ ልዩ ስምን መስጠት የተለመደ ነው። ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቄርሎስ መምህረ ዓለም፣ ናጣሊስ ማኅቶት ብሩህ፣ ኤፍሬም አፈ በረከት እንዲል። አሁን አሁን ያለው ስም ግን የተጋነነና መሬት ላይ ያለውን እውነታ የማይገልጽ ነው። እስከዛሬ ለተሰጡት እንደተሰጠ ከዚህ በኋላ እንዳይሰጥ ሲኖዶስ ቢወስን መልካም ነበር።

**፻፺፰. የጌታን ሥጋና ደም ስንቀበል የምንቀበለው መለኮት የተዋሐደውን ነፍስ የተለየውን ነው ስንል ምን እያልን ነው?**

መልስ፦ ዕብ.11፥28 አንድምታ ትርጓሜ ላይ እንደተገለጸው የምንቀበለው ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው። ነፍስ የተለየው ማለታችን በየጊዜው ሥጋውን ስንበላ እንደማይሰማው ያመለክታል። ለንጊኖስ ነፍሱ ከሥጋው ከተለየ በኋላ ጎኑን ቢወጋው ውሃና ደም ወጥቶታል። በውሃው ተጠምቀን ልጅነትን እናገኛለን። ደሙን ጠጥተን የዘለዓለም ሕይወትን እናገኛለን።

**፻፺፱. ወንድ ልጅ የዘር ፍሬ ፈሳሽ ሳያይም ካዬም ጀምሮ ከእንስሳት ጋር የሚደረግ ሩካቤ እና የዘር ፍሬ ፈሳሽ ሳያይ ከሴት ልጅ ጋር የሚደረግ ሩካቤ ድንግልናን ያሳጣል ወይ? ክህነትስ መቀበል ይችላል ወይ?**

መልስ፦ አዎ ድንግልናን ያሳጣል። በብሉይ ኪዳን "ከእንስሳ ጋር የሚረክስ ፈጽሞ ይገደል" ተብሎ ፍርዱ መገደል ነበር (ዘፀ.22፥19)። በሐዲስ ኪዳንም ይህ ድርጊት ፍጹም ክፉ ሥራ ነው። ስለዚህ ቁጥሩ ከከባድ ዝሙት ስለሆነ ክህነት ያስሽራል። ወንዱ ዘር ለማመንጨት ዘመኑ ባይደርስም ግንኙነት ካደረገ ድንግልናውን አጥቷል።

**፪፻. ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ውጭ ያሉ ሰዎች በሕይወታቸው ድንግልናቸውን ቢያጡ እና በትምህርት ወደ ትክክለኛው ሃይማኖት አምነው ተጠምቀው ቢመለሱ ክህነት ማግኘት ይችላሉ? ክህነት ተቀበለ ማለት በተክሊል ያገባል ማለት አይደለም ወይ?**

መልስ፦ ድንግልናውን ካጣ ክህነት አይቀበልም፣ በተክሊልም አያገባም። ነገር ግን ድንግል ከሆነ ክህነትም፣ ተክሊልም ይገባዋል (ዘሌ.21፥13፤ መጽሐፈ ሐዊ ባህል 14)።

**፪፻፩. ባለእጅ ወይም ቡዳ የሚባሉት ሰዎች መቀደስ አይችሉም ቤተ መቅደስም አይገቡም ይባላል። ዲያቆንስ ከእነርሱ ቢጋባ ክህነቱ ላይ ችግር አለው? ወንዶቹስ ካህን መሆን ይችላሉ?**

መልስ፦ በመሠረቱ ቡዳ የሚባል ሰው ወይም ማኅበረሰብ የለም። ይህ ጠንካራ የነበረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በእርስ ለማለያየት ሰይጣን የፈበረከው ክፉ ቃል ነው። ባለእጅ፣ ሸማኔ፣ ባሪያ፣ ቡዳ፣ ቀጥቃጭ እያልን ክቡሩን የሰው ልጅ እያገለልን አንድነታችንን መሸርሸር አይገባም። ካህን ከሆነ ከየትኛውም ዘር ይወለድ፣ ምንም ይባል መቀደስ ይችላል። ዲያቆንም ክርስቲያን እስከሆኑ ድረስ ከየትኛውም ጎሣ ወይም ማሕበረሰብ

ማግባት ይችላል። "አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" እንዲል (ገላ.3፥28)።

፪፻፪. ፍትሐ ነገሥት የአጎት ልጅ 4ተኛ ትውልድ እደሆነ ይናገራል። አንድ ሰው የአያቱን አክስት ልጅ ልጅ ልጅ ልጅ ማግባት ይችላልን?

መልስ፦ በግብጻውያን አቆጣጠር የአጎት ልጅ አራት ነው። ይህም አባቴ እኔን ወለደ አንድ፣ አያቴ አባቴን ወለደ ሁለት፣ አያቴ አጎቴን ወለደ ሦስት፣ አጎቴ የአጎቴን ልጅ ወለደ አራት ይላል። በሀገራችን ያለው የጋብቻ አቆጣጠር ግን በአንድ ጎን ስድስት በአንድ ጎን ስድስት ተቆጥሮ በሰባተኛው መጋባት ነው። አንዳንዱ ግን በወንዱ ስምንተኛ ደርሶ በሴቷ አራተኛ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። እንዲህ ሲያጋጥም የሥርዓት ባለቤቶች ጳጳሳትን አማክሮ መፈጸም ነው።

፪፻፫. በ12 ቅዱስ ሚካኤል፣ በ19 ቅዱስ ገብርኤል፣ በ21 እመቤታችን እና ሌሎችም ቅዱሳን የእየራሳቸው ቀን ተመድቦላቸው እንዲከበሩ የተሠራው ሥርዓት መቼ እና በማን ነው?

መልስ፦ በዓላተ እግዝእትነ ማርያምን ሠላሳ ሦስቱን እንድናከብር በተአምረ ማርያም ተገልጿል። በተጨማሪ በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የነበሩ የኢትዮጵያ ሊቃውንት እንዲከበሩ መወሰናቸውን ሰምቻለሁ። በትውፊትም የአጥቢያችን ታቦት የሚውልበትን ቀን ማክበር የተለመደ ነው። ከመቼ ጀምሮ እንደተጀመረ ግን ምንም ማስረጃ የለኝም። ማክበሩ ግን ነገራተ እግዚአብሔር መነገሪያ ስለሆነ እጅግ በጣም መልካም ነገር መሆኑን መገንዘብ አለብን።

፪፻፬. በዓለማዊ አስተምህሮ አፄ ቴወድሮስ የቀዳስያንን ብዛት ሁለት ቀስና ሦስት ዲያቆን በቂ ነው ብሎ የወሰነው እርሱ ነው ይባላልና ከመወሰኑ በፊት የቀዳሲያን ብዛት ስንት ነበር?

መልስ፦ አፄ ቴዎድሮስ በአንዲት ቤተክርስቲያን ሊኖሩ የሚገባቸውን የአገልጋዮች ብዛት ቅንሰው ሊሆን ይችላል እንጂ የቅዳሴውን ሥርዓት እርሳቸው አላሻሻሉትም። ላሻሽልም ቢሉ ሥልጣን የላቸውም። ከቤተክርስቲያን ቀዳስያን አምስት ይሆኑ እንደነበረ ከአፄ ቴዎድሮስ በፊት የተዘጋጁ የትርጓሜ መጻሕፍት ይገልጻሉና። ለምሳሌ ቅዳሴ ሐዋርያት ትርጓሜ ላይ የሠራዊተ መላእክቲሁን ሐተታ ሲያትት ንፍ*ቅ ቄስ፣ ንፍ*ቅ ዲያቆን በአፍኣ፤ ሠራዒው ቄስ፣ ሠራዒው ዲያቆን፣ አብሪው ቄስ ከውስጥ ሆነው ይሉታል ብሏል። ሥርዓተ ቅዳሴውንም ስንመለከት ትእዛዛቱ በዚህ መሠረት የተዘጋጁ ናቸው። ይ.ካ፣ ይ.ዲ፣ ይ.ካ.ንፍ*ቅ፣ ይ.ዲ.ንፍ*ቅ እያለ ያዝዛልና።

፪፻፭. አንድ ባል እና ሚስት በአንድ እየኖሩ አንደኛው አብሮ ለመኖር ባይችል ማለትም አቅም ማጣት (ማብሰል፣ግንኙነት ማድረግ፣ ጤና) ቢኖር ትዳራቸውን እንዴት ማስቀጠል ይቻላል?

መልስ፦ ሥርዓተ ተክሊል ሲፈጸም ሰነፈች፣ መከነች ብዬ ላልተዋት በእግዚአብሔር ፊት ቃል እገባለሁ እንላለን። ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ቢያጋጥሙም ታግሠን በፍቅር መኖር ይገባናል። ፍቺ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ግን አሉ ለምሳሌ በሞት፣ አንዱ ሃይማኖቱን ከቀየረ፣ ከሌላ ሲያመነዝር ከተገኘ፣ በስምምነት ከመነኮሱ፣ ለግንኙነት የሚከለክል አካል ካለ (ለምሳሌ በትርጓሜ የአባ ባይሉ ልጆች የሽንብራ አፍንጫ የምታህል ለመሽኛ ብቻ የምትሆን መሽኛ ነበረቻቸው ይባላል። እነዚህ ቢያገቡ ከሴቷ ፍትወትን ማራቅ ስለማይችሉ ልጅ መውለድ ስለማይችሉ ሦስት ዓመት ቆይተው ይፋታሉ። ሴቷም ግንኙነትን የሚከለክል አጥንት መሳይ በአፈ ማኅፀኗ አካባቢ ካለ ሦስት ዓመት ቆይተው ሊፋቱ ይችላሉ)። ይህ ሁሉ በምክረ ካህን የሚፈጸም ነው (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24)።

፪፻፮. አንድ ዲያቆን ምስጢር ሳያይ ሚስት ማግባት ይችላል ወይስ አይችልም?

መልስ፦ ምሥጢር ማየቱኮ ለቀጣይ አገልግሎት ሥርዓት መማሪያ እንጂ ሌላ ነገር የለውም። ስለዚህ ከማግባት አይከለክለውም።

፪፻፯. ሰሙነ ሕማማት ውስጥ መልክአ መልክ አይደገምም አይታደልም ምክንያቱ ምንድን ነው?

መልስ፦ በቤተክርስቲያን በሰሙነ ሕማማት መልክአ ሕማማት የሚባለው መልክእ ከሕማማቱ ጋር በምሥጢር ስለሚገናኝ ግብረ ሕማማቱ ጋር እየተስማማ ይባላል። ይህ ራሱ ሰፊ ስለሆነ ቤተክርስቲያን መልክአ ሕማማት ብቻ እንዲባል ሥርዓት ስለተሠራ ነው። በግል ጸሎታችን ግን መልክአ መልክ መድገም ይቻላል አልተከለከለም።

፪፻፰. በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም እንደማይቻል ይነገራል። ነገር ግን አንድ በጤና እክል ምክንያት (ብታረግዝ ለሞት የሚያበቃት ነገር ቢኖርባት) የወሊድ መቆጣጠርያ መጠቀም ትችላለችን?

መልስ፦ የወሊድ መቆጣጠሪያን መጠቀም በቤተክርስቲያን አስተምህሮ የተፈቀደ አይደለም። ፅንስ እንዳይፀነስ ለማድረግ ወይም የተፀነሰውን ለማስወረድ መድኀኒት መጠቀም እንደማይገባ ፍትሐ ነገሥት ገልጿል (አንቀጽ 24)። ከዚህ ከፍ ያሉ ህክምናው በመሰልጠኑ የመጡ ጉዳዮችን ግን ሲኖዶስ ከዘመኑ ጋር አይቶ ብያኔ ቢሰጥባቸው ባይ ነኝ።

፪፻፱. አንድ ዲያቆን ከእጮኛው ጋር ተደጋጋሚ ግንኙነት ቢያደርግ እና ንስሓ ቢገባ አብረውም ቢጋቡ (እርሱ ወደሌላ እርሷም ወደ ሌላ ሳይሄዱ ሁለቱም ንስሐ ገብተው ቢጋቡ) ዲቁናው ሊቀጥል ይችላል?

መልስ፦ አይችልም። ከጋብቻ በፊት ግንኙነት ካደረገ ምንም እንኳን የሚያገባት እርሷኑ ቢሆንም ክህነቱም ፈርሷል። ስለዚህ ዲቁናው አይቀጥልም። ከጋብቻ በፊት ግንኙነት ፈጽሞ አይፈቀድም።

**፪፻፲. አካል ስንል ለሥላሴ ምን ማለታችን ነው? እግዚአብሔር በአካል ፍጹም ገጽ፣ መልክ፣ አካል አለው ስንል እንዴት ነው? ለእግዚአብሔር የሰውነት ክፍሎች አሉት ማለት ነው?**

መልስ፦ ለሥላሴ አካል ሲነገር ወሰን የሌለበት ረቂቅ አካል ነው። ያ ወሰን የሌለበት ረቂቀ አካል ረቂቅ መልክ፣ ረቂቅ ገጽ አለው። ለእግዚአብሔር የሰውነት ክፍሎች አሉት ወይ የሚለው ጥያቄው ራሱ የተሳሳተ ነው። የሰውነት ክፍልኮ የሚነገር ለሰው ነው። የሰውነት ክፍል ነው ያለ። ለእግዚአብሔር ከተነገረ የእግዚአብሔርነት ክፍል ነው ሊባል የሚችል። ለእግዚአብሔር ዓይን፣ እጅ፣ እግርና የመሳሰሉት አካላት እንዳሉት መጻሕፍት ይናገራሉ። እንዴት እንደሆነ ግን አይታወቅም። እንደ ሰው ዓይኑ ከሆነ ቦታ፣ ጆሮው ከሆነ ቦታ ነው ያለ እያልን ሰብኣዊ ፍልስፍና አንናገርም። እንዳለው ቢነገርም እንዴት እንደሆነ አይታወቅም ብሏል ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ አትናቴዎስ (ሃይ.አበ.28፥30)።

**፪፻፲፩. በዶርም ስንዘክር ጸሎት በሚደረግ ጊዜ ወይኑ ያለበትን ወይም የሚጠጣው ያለበትን ክዳኑን ለምን እንከፍተዋለን እንደተገጠመ ቢጸለይ መንፈስ ቅዱስ አይባርከውም ወይስ ሌላ ነገር?**

መልስ፦ ይኼ ትውፊት ስለሆነ ነው እንጂ ባይከፈት መንፈስ ቅዱስ የማያይ፣ ሲከፈት የሚያይ ነው ለማለት አይደለም። ተከድኖም ቢጸለይበት፣ ተከፍቶም ቢጸለይበት መንፈስ ቅዱስ ይባርከዋል።

**፪፻፲፪. ዲያቆን ነኝ። ከእጮኛዬ ጋር ለመጋባት ቀጥሮ ይዘን ሳለ አንድ ቀን ምንም እንኳ ግንኙነት ባናደርግም ራቁቷን አፈ ማሕፀኗን በማየትና በመሳሳም በመካከል ምንም አካላዊ ግንኙነት ሳይኖር ዘር ፈሰሰኝ። በኋላ ልጅቱ ፀነሰች። ስትመረመር ድንግል ናት። ግን ፀንሳለች። ታዲያ በተክሊል መጋባት እንችላለን? እኔስ ዲቁናዬ ይቀጥላል?**

መልስ፦ በእውነቱ ከጋብቻ በፊት ራቁትን መተያየት፣ መሳሳም ፈጽሞ የተከለከለ ሆኖ ሳለ መጀመሪያ ይህንን ለምን አደረጋችሁ?! የወንድ ዘር በተለያዩ ምክንያቶች የሴቲቱ ማኅተመ ድንግልና ሳይፈርስ ወደ ማሕፀን የመግባትና ፅንስ የመፈጠር አጋጣሚ እንዳለ ከዶክተሮች አንዱ ነግሮኛል። ዙሮ ዙሮ የሁለታችሁ መራቢያ አካል ባይገናኝም የወንዱ ዘር ግን ወደሴቲቷ ገብቶ ፀንሳለች። አሁን ፅንሱ የአንተና የእርሷ ነው። ስለዚህ ዲቁናህም ፈርሷል በተክሊልም አታገባም። ጎበዝ ፈሪሀ እግዚአብሔር ይኑረን። ከጋብቻ በፊት መሳሳም፣ ራቁትን መተያየት ከየት የመጣ ባህል ነው???? ስለዚህ ላጠፋችሁት ጥፋት ንስሓ ግቡበት። ተስፋ መቁረጥም አይገባም። መጀመሪያ ይህንን ክፉ ሥራ

ባትሠሩ መልካም ነበር። ከሠራችሁ ደግሞ ምንም እንኳ ክህነታችሁ ቢፈርስ ጨዋ ሆናችሁ ቀሪ ሕይወታችሁን እግዚአብሔርን በምእመንነት እያገለገላችሁ ኑሩ።

**፪፻፲፫. በኢትዮጵያ ሀገራችን እና ከጎረቤት ሀገራት ጀምሮ የአውሮፓ ሀገራት ሌሎችም ሩቅ ምሥራቅ ሀገራት ያለው የቀን እና የሌሊት መፈራረቅ በእጅጉ ይለያያል። እንዲያውም ኖርዌይ የምትባል ሀገር ጨለማ የሌለባት ሀገር ትባላለች። ለዚህ ጉዳይ ሳይንስ በርካታ ምክንያቶችን ይደረድራል rotation of the earth on its axis, revolution o the earth around the sun etc ሌሎችንም ይጠቅሳል። በሃይማኖታዊ ትምህርት የሚሰጠው ማብራሪያ ምንድን ነው?**

መልስ፦ የተፈጥሮ ባለቤት እግዚአብሔር ነው። ፍጥረታትንና ዑደታቸውን አጥንተን አልጨረስንም። ሳይንሱ ለዚህ ጉዳይ ልዩ ልዩ ሐሳቦችን መሰንዘሩ መልካም ነው። ሳይንስ እንደመሆኑ ግን ወደፊት በሚደረጉ ሌሎች ጥናቶች ውድቅ ሊደረግም ስለሚችል ሙሉ በሙሉ የሳይንሱን ሐሳብ እንቀበል ማለት አይቻልም። ፀሐይ ከአንዱ ሀገር በርታ ከሌላው መጨለሟና የመሳሰለው ጉዳይ ሃይማኖትን አይቃወምም። ምክንያቱም ሃይማኖት ይህንን ሁሉ ያደረገ እግዚአብሔር ነው ብሎ የድርጊቱን ባለቤት ይገልጻል እንጂ ድርጊቱ የተደረገበትን ንኡስ ምክንያት አይጠቅስምና። ከአንዱ በርቶ ከሌላው የጨለመ እግዚአብሔር እንዲህ ስላደረገው ነው የሚል ጥቅል መልስ ነው ያለኝ።

**፪፻፲፬. ንስሓችንን ከጨርስን በኋላ ወደ ቅዱስ ቁርባን እንቀርባለን እና ፍትሐት ዘወልድ ተደግሞልን እስክንቆርብ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ ሆነን መቆየት አንችልም። እና ይሄንን በተመለከተ በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚያጋጥሙንን ውድቀቶች ደግመን እንናዘዛቸዋለን ወይስ በምን ዓይነት መንገድ ነው ወደ ቅዱስ ቁርባን መቅረብ የምንችለው?**

መልስ፦ አዎ ደግመን እንናዘዛቸዋለን። በተቻለን አቅም አንደበታችንን ተቆጣጥረን ከነቢብና ከገቢር ኃጢአት ርቀን መቆየት አለብን። ከቆረብን በኋላም ይህንን መለማመድ አለብን። እስክንቆርብ ሐሳባዊ በደሎች ካሉ በከመ ምሕረትከ እያልን መቊረብ እንችላለን። ቊርባን ልንቆርብ ቤተክርስቲያን ውስጥ ቆመን ራሱ መንፈሰ ጽርፈት ጥርጣሬን፣ ክፉ ሐሳብን ሊዘራብን ይችላል። በዚህ ጊዜ ይህ ሐሳብ የእኛ አይደለም ብሎ ሐሳቡን በመቃወም ትግል እያደረግን መቅረብ ነው (አረጋዊ መንፈሳዊ ድርሳን 8)።

**፪፻፲፭. ሳይንሱ የምንኖርባት መሬት ፀሐይን ትዞራለች ይላል ብዙ ማስረጃዎችንም ያቀርባል። ሃይማኖታዊ አስተምህሮው ምንድን ነው የሚለው? ፀሐይ ናት የምትዞር ወይስ መሬት?**

መልስ፦ ስለፀሐይና መሬት መዞር ወይም አለመዞር የሃይማኖት መሠረታዊ ጉዳይ አይደለም። መሠረታዊው ጉዳይ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር መሆኑን አምኖ መኖር ነው። ፀሐይም የምትንቀሳቀስ እንጂ አንድ ቦታ ብቻ ጉብ ብላ የምትኖር እንዳልሆነች ግን ሄኖ.11፥13 ላይ ተገልጿል። በሳይንስ በኩል ያለው ጉዳዩ ጥልቅ

ጥናትን የሚጠይቅ በመሆኑ ከscientific prediction እንጂ ከPure science የሚቆጠር አይደለም።

**፪፻፲፮. ድርሳነ ሚካኤል ዘወርኃ ኅዳር ላይ ያሉ አንዳንድ ኅቡዕ ስሞች ለምሳሌ ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ ጸ እነዚህ ትርጉማቸው ምንድን ነው? አንዳንድ ሰዎች መተት የሚጠቀሙ ሰዎች ለመደበቂያ ድርሳኑ ላይ አስገብተዋቸው ነው ይላሉ። ይህን እንዴት ይታያል?**

መልስ፦ ጸ ስመ አምላክ እንደሆነ በቅኔ ትምህርትም የታወቀ ነው። ስለዚህ መተት የሚጠቀሙ ሰዎች ለመደበቂያ ከድርሳኑ አስገቡት የሚለው ግልብ እይታ ስለሆነ አንቀበለውም። ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ጥርጥራዊ ሳይሆን አዎንታዊ አቀባበል (Positive approach) ቢኖረን መልካም ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተጻፈውን ሁሉ በትችት መንፈስ ሳይሆን በአዎንታዊ መንፈስ ብናነበው መልካም ነው።

**፪፻፲፯. ጡት የሚጠባ ሕፃን ለመቍረብ እስከ ምን ያህል ሰዓት ነው የሚጾመው?**

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተጻፈ አላገኘሁም። በቤተክርስቲያን በትውፊት ግን ቅዳሴ ከጀመረበት ሰዓት ጀምሮ ጡት መከልከል እንደሚገባ ይነገራል።

**፪፻፲፰. "ያለ ድንግል ማርያም አማላጅነት ዓለም አይድንም" የሚለው ሐሳብ እንዴት ይታያል?**

መልስ፦ እንደ አነጋገራችን ይወስነዋል። የድንግል ማርያምን አማላጅነት የማያምን ሰው አይድንም ከሆነ አዎ አይድንም። የቅዱሳንን አማላጅነት አለማመን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጸጋ መካድ ነውና። ይህን አለማመን በራሱ ፕሮቴስታንታዊነት ነውና። ክርስቶስ ያለእርሷ ማዳን አይችልም የሚል እይታ ከሆነ ግን ስሕተት ነው። ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደመሆኑ በምልጃ ምክንያትም ያለምልጃም በሌሎች ምግበራት ማዳን ይቻለዋልና።

**፪፻፲፱. በቤተክርስቲያናችን የክርስትና እናት እና አባት የሚባል እንዳለ ይታወቃል። ሆኖም ክርስትና የምታነሣዋ የክርስትና እናት በወቅቱ የወር አበባ ቢመጣባት ክርስትና ማንሣት ትችላለች ወይ ካልቻለችስ ማን ነው ክርስትናውን ሊያነሣላት የሚችል?**

መልስ፦ በወቅቱ ቤተክርስቲያን መግባት ስለማትችል ከቤተክርስቲያን ገብታ ማንሣት አትችልም። ታዲያ ምን መሆን አለበት ከተባለ አላውቀውም። የተሠራ ሥርዓትም አላውቅም።

**፪፻፳. ለአራስ ሴት በአጠገቧ ዘነዘና ወይም ቢላዋ ማስቀመጥ ከአእምሮ ሰላም ባለፈ፣ በሕክምናው ዓለም ለማይታወቁ መናፍስታዊ ጥቃቶች መከላከያ ሊሆን ይችላል ብለው የሚያምኑ አሉ። ልክ ናቸው?**

መልስ፦ ይህ እንኳ የተሳሳተ እምነት ነው። ምክንያቱም ሰይጣን ዘነዘና፣ ቢላዋ፣ ፌሮ፣ ማጭድና የመሳሰሉትን አይፈራም። ስለዚህ ይህ ልማዳዊ ድርጊት እንጂ ሃይማኖታዊ መሠረት የለውም። አነር ድመት፣ ነብርና የመሳሰሉት አራዊት እንዳይተናኮሏትና ራሷን ለመከላከል ተደርጎ ከሆነ መልካም ነው።

**፪፻፳፭. ቀዳም ሥዑር የሞተ ሰው ሥርዓተ ፍትሐት ይደርስለታል?**

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15 ላይ በቀዳም ሥዑር ፍትሐት መፈጸም እንደሚችል ይናገራል።

**፪፻፳፮. ገሃነም ለዘላለም የሚያቃጥል እውነተኛ የእሳት ቦታ ነው ወይስ ከእግዚአብሔር ተለይቶ የመኖር ሥነ ልቡናዊ ስቃይ?**

መልስ፦ ገሃነም የሚባል ቦታ እንዳለ መጻሕፍት ተናግረዋል። "በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ሂዱ" እንዲል (ማቴ.25፥41)። ከዘጠኙ ዓለማተ እሳት አንዱም ገሃነም እንደሆነና ፍጥረት እንደሆነ ተገልጿል (መጽሐፈ አክሲማሮስ ዘእሑድ)።

**፪፻፳፯. የአሁኗ የእስራኤል መንግሥት የምታደርጋቸው ጦርነቶችና የፖለቲካ ውሳኔዎች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጋር ይያያዛሉ?**

መልስ፦ ይህ ጦርነት ሥጋዊ ጦርነት ነው። ከመንፈሳዊ ሕይወት ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም። ሁለት በእግዚአብሔር የማያምኑ አካላት እርስ በእርስ የሚያደርጉት ፖለቲካዊ ጦርነት ነው።

**፪፻፳፰. በጸሎተ ኀሙስ ሕዝበ ክርስቲያኑ ጉልባን አዘጋይቶ የሚበላበት ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የለውም። ታዲያ ለምን መከልከል አልተቻለም?**

መልስ፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈ ነገርን ሁሉ አትቀበሉ የሚል ነገርኮ የለም። አብዛኛው ነገርኮ አልተጻፈም። በትውፊት የተቀበልነው አለ። ተጽፎ የተቀበልነው አለ። ጉልባን መዘጋጀቱ ተያያዥ ሌላ አምልኮ እስከሌለው ድረስ የሚከለከልበት አግባብ የለውም። የቤተክርስቲያንን አስተምህሮ የማይቃረን ባህል እስከሆነ ድረስ መከልከል አይገባም።

**፪፻፳፱. ሰይፈ ሥላሴ የአስማት መጽሐፍ ነው ብለው መምህር አስተማሩን። አገልጋዩም ምእመኑም በብዛት የሚጸልየው መጽሐፍ ነው እርሶ ምን ይላሉ?**

መልስ፦ በመሠረቱ አስማት ማለት ስሞች ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ባለማወቅ ምትሐታዊ የሰይጣን አሠራርን አስማት እያሉ መጥራት ተለምዶ ነው እንጂ። ሰይፈ ሥላሴ የያዘው

የእግዚአብሔርን ስሞች ከሆነ ችግር የለውም። የያዘው አጋንንታዊ ስሞችን ከሆነ ግን ችግር ይኖረዋል። እኔ መጽሐፉን አንብቤው ስለማላውቅ ምንም ማለት አልችልም።

፪፻፳፮. ተአምረ ማርያም ላይ ተአምሪሃ ለእግዝእትነ ማርያም ለእመ ሰምዐ በአሚን ይከውኖ ከመ ቊርባን የሚለው ሥጋዬን ያልበላና ደሜን ያልጠጣ ሕይወት የለውም ከሚለው ጋር እንዴት ይታረቃል?

መልስ፦ ተአምረ ማርያምን መስማት ሥጋውን ደሙን እንደተቀበለ ይሆንለታል የሚለው "እንደ" በሚል ማንጻሪያ የቀረበ እንጂ ተአምሯን መስማት ሥጋውን ደሙን ከመቀበል ጋር አቻ ነው ማለት አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔና አንተ (አብ) አንድ እንደሆንን እነርሱም (ሐዋርያትም) እንደእኛ ይሆኑ ዘንድ ሲል በአብና በወልድ መካከል እንዳለው ያለ የባሕርይ አንድነት በሐዋርያት መካከልም አለ ለማለት አይደለም። እንደዚህ ሁሉ የላይኛው ተአምረ ማርያምን መስማት ጥቅም እንዳለው ለመግለጽ ብቻ የቀረበ አንጻር ነው።

፪፻፳፯. ለእግዚአብሔር መጠሪያ የሆኑ ስሞች ለምሳሌ አማኑኤል፣ አዶናይ፣ ኤልሻዳይ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ስሞች ለፍጡራን መሰየም አይቻልም ይባላል። ማስረጃ አለው?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ እስካሁን ካነበብኳቸው መጻሕፍት አላገኘሁም። በመጻሕፍት የእግዚአብሔር ስም ዘርፍ አድርጎ መናገር ነው የተለመደ። ይኸውም ገብረ እግዚአብሔር፣ ወልደ እግዚአብሔር እንደማለት ያለ ዳንኤል፣ ሚካኤል ሲል ነው የሚገኝ። በእግዚአብሔር ስም የተጠራ ሰው አላስታውስም። [ግላዊ አስተያየት፦ የእግዚአብሔር ስም የተከበረ ስለሆነ እርሱ ብቻ ቢጠራበት የሚል ሐሳብ አለኝ]

፪፻፳፰. The problem of evil ጋር ተያይዞ የሆነች ጥያቄ አለችኝ። ከኢሳይያስ 45 ጋር ተያይዞ የሚያነሱትን፣ ክፋትን እግዚአብሔር ነው የፈጠረው ብሎ atheistioch ያነሳሉ። ነገር ግን ትንሽ ግር ያለኝ evil ወይንም ክፋት ምንጩ ከየት ነው? ክፋት የተፈጠረ አይደለም? አይደለም ካልን ከየት የመጣ ነገር ነው? ወይንስ ክፋት ማለት መልካሙን አለማድረግ outcome ነው ልንል እንችላለን? መልካምን አለማድረግ by default ክፋትን ያመጣል እንደማለት? እንደዛም ብንል የሌለ፣ ያልተፈጠረ ነገር ከየት ይከሰታል የሚል ጥያቄ ያነሳል ውስጤ። ወይስ free will ተጠቅመን ትዕዛዝ ስናፈርስ የሚመጣ ነገር? እንደዛም ብሆን ደግሞ ከየት መጣ? ወይንስ እንዴት ነው? እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የፈጠረ ከሆነ ደግሞ ክፋትንም ፈጥሯል ብሎ እንደ claim ያነሳሉ። ክፋት የተፈጠረ ካልሆነ ከየት የመጣ ነው? ምንጩ?

መልስ፦ እግዚአብሔር ክፋትን አልፈጠረም። ክፋት አካል ያለው፣ ቦታ የሚይዝ ፍጥረት አይደለም። ሲጀምር ክፋት ወይም ኃጢአት የሚባለው ለሰው የሰው አለመታዘዙ ራሱ ነው። የሰይጣንም ከእውነታው በተቃራኒ መቆሙ ነው ክፋት የሚባለው። ኢሳ.45፥7 ላይ

"ክፋትን እፈጥራለሁ" ይላል እግዚአብሔር የተባለው ክፋት የሚለው መከራ ማምጣትን ነው። እግዚአብሔር በሰዎች ላይ መከራ ማምጣቱን በሰውኛ ለመግለጽ ክፋት ብሎታል እንጂ አለመታዘዝን ፈጠረ ማለት አይደለም። ባለመታዘዛቸው ምክንያት የመጣባቸውን መከራ አደረሰ ተብሎ ይተረጎማል እንጂ። ክፋትን የሰዎች አለመታዘዝ ነው ካልን የሰዎች አለመታዘዝ ራሱ ከምን የመነጨ ነው ከተባለ ነጻ ፈቃዳቸውን በአግባቡ ካለመጠቀማቸው የመነጨ ነው።

፪፻፷፱. ብዙ ሰዎች ሥጋ ወደሙ ተቀበሉ ወይም በሥርዓተ ቤተ ክርስቲዩን ተጋቡ ሲባሉ ገና ወጣት ነኝ ኃጢአት ብሠራስ ወይም ብትፈታኝሽ/ቢፈታኝስ፣ ብሳሳትስ ይላሉ። ይህ ነገር ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ አንጻር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ማንኛውም ጋብቻውን በሥጋሁ ወበደሙ ለክርስቶስ አማካኝነት መፈጸም አለበት። ሲጀምር ብትፈታኝስ ብሎ ጋብቻ የለም። ጋብቻ በፍቅር ሊኖሩበት ታስቦ ነው መደረግ ያለበት። የሆነ ሆኖ ያለቍረባን ማግባት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በደሉን ከፍ ያደርገዋል እንጂ አይቀንሰውም። ስለዚህ ሰው በተቻለው መጠን የጽጽቅን ሥራ ለመሥራት በኅሊናው ወስኖ በቍርባን ጋብቻውን መፈጸም አለበት። ከቆረበ በኋላ ከባሕርይ ድካም የተነሣ ኃጢአት ሊሠራ ይችል ይሆናል። ቢሆንም በየጊዜው ንስሓ እየገባ መኖር ይገባዋል።

፪፻፸. በሐዲስ ኪዳን ጽላት መቀረጽ የተጀመረው ዓመተ ምሕረቱ መቼ ነው? የጀመረውስ ማን ነው?

መልስ፦ መቼ እንደተጀመረ ምንም የማውቀው ታሪካዊ መረጃም ማስረጃም የለኝም። ክቡር ጠያቂ የቤተክርስቲያንን ታሪክ ያጠኑ የታሪክ ምሁራንን ጠይቀው እንዲረዱ ልጠቁምዎ።

፪፻፸፩. በበዓለ ኀምሳ እና በዕለተ እሑድ ሰርግ መደረግ የለበትም የሚሉ አሉ። ይህ ሐሳብ ልክ ነው?

መልስ፦ ጋብቻ እንዳይደረግ በፍትሐ ነገሥት የተከለከለው በዐቢይ ጾም ወቅት ነው (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15)። ከዚያ ውጭ በበዓለ ኀምሳ፣ በዕለተ እሑድ መደረግ የለበትም የሚል ሥርዓት የለም።

፪፻፸፪. በድጅታል መታወቂ ብዙዎች ተደናግረናል። ምክንያቱም በራእየ ዮሐንስ ምዕራፍ 13 ላይ ሁሉም ሰው በግንባሩ ወይም በእጁ ምልክቱን ይቀበላል። ያለምልክቱም መገበያየት እንዳይቻል ይደረጋል ይልና በምዕራፍ 14 ደግሞ ምልክቱን የሚቀበል ወደ ገሃነም እንደሚጣል ስለሚል ነው። ድጅታል መታወቂያን ደግሞ በግንባራችን ማለትም በዓይንና በፊት አሻራ (eye print and face print/face recognition) እና በእጅ አሻራ (Finge rprint) ነው እየተቀበልን

ያለነው። ያለ ድጅታል መታወቂያ ደግሞ ብዙ ነገሮች እየተከለከሉ ነው በተለይም የባንክ ጉዳይ። ድጅታል አይዲ የአውሬው ምልክት ነው ወይስ አይደለም?

መልስ፦ ዲጂታል መታዎቂያ ሥራን ለማቅለል ሰዎች የሠሩት የቴክኖሎጂ ውጤት ነው። ሰዎች እግዚአብሔር በሰጣቸው አእምሮ ብዙ ነገሮችን ተመራምረው ስልክን፣ ሞባይልን፣ አውሮፕላንን፣ ሌሎችንም ታላላቅ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አበርክተዋል። ስለዚህ ይህንን እውቀት የገለጠ እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን። ሰይጣን በነገራችን ላይ ምንም የሌለው ድኻ ነው። ስለዚህ የእርሱ ነው ብለን ለእርሱ የምንሰጠው ምንም ነገር የለም። ራእየ ዮሐንስ ምዕራፍ 13 ላይ የተነገረው ስለሐሳዊ መሚሕ ነው። ይህ ደግሞ እግዚአብሔርንና ቅዱሳንን የሚሳደብ እንደሆነ ተገልጿል። ይህም ሐሳዊ መሚሕ (ሐሳዊ መሚሕ) ምስሉን እንደሚያቆምና ለእርሱ ለመገዛታቸው ማስረጃ በቀኝ እጅና በግንባር ምልክት እንደሚያደርግ ተገልጿል። ይህ ከNational ID ጋር የሚያመሳስለው ነገር ቢኖርም ነገር ግን ይህንን ያወጡ አካላት ከእግዚአብሔር አምልኮ አልተለዩም። National ID የእኛን ማንነት የሚገልጽ መታወቂያ እንጂ ባዕድ ምልክት አይደለም። እና ቴክኖሎጂ በመጣ ቁጥር ከሰይጣን ጋር ባናያይዘው። የሐሳዊ መሚሕ ምልክት ሰዎች በፈቃዳቸው እግዚአብሔርን ክደው የሚያደርጉት ምልክት እንጂ በድብብቆሽ የሚሆን አይደለም።

፸፻፴፫. ገደል የገባ፣ ውሃ ውስጥ የሞተ ሰው፣ ውጭ ሀገር የሞተ ሰው ፍትሐት አይፈታለትም ይባላል። ይህን ሐሳብ እንዴት ያዩታል?

መልስ፦ ለማንኛውም ክርስቲያን በምንም ዓይነት መንገድ ቢሞት ፍትሐት ማድረግ ይገባል። እኛ እግዚአብሔር እንዲምርልን መሐራ እግዚኦ ለነፍሰ እገሌ እያልን እንጸልያለን። መማር አለመማር ደግሞ የእግዚአብሔር ፈንታ ነው። ፍትሐት ማድረግ እንደሚገባና ፍትሐት ለሚያደርጉም ለሚደረግላቸውም ጥቅም እንደሚያሰጥ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 22 ተገልጿል።